
# ሁለተኛው አስደናቂ ታሪኮች



NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

ከጳውሎስ ኞኞ

# ማውጫ

የጁሴፔ መንፈስ ........ 5
ተመሳሳይነት ........ 9
የተቀበረ ሰው ይነሳል? ........ 11
የሚዘንብ ውሃ ብቻ ነው? ........ 12
ሌላው ዮናስ ........ 16
አዲሱ ነቢይ ........ 17
ሰው ሳር ይሆናል? ........ 28
መንፈሳውያን ሰዎች ........ 29
እጀቢሱ ልብ ........ 30
ጣት እንደ ዓይን ........ 31
መንትዮቹ ........ 31
መሬት ትመሰክራለች? ........ 32
የማስታወስ ችሎታ ........ 32
ወፋፍራሞቹ ........ 33
እንስሳት ምን ያውቃሉ? ........ 36
አሮጊቷ ........ 38
ልጅቷ ........ 39
ድንክዬዎች ........ 40
አስደናቂ ጠንቋይ ........ 43
የዝንቧ ጣጣ ........ 44
ደማሚቱ ልጅ ........ 45
ዝሆን ........ 46
የማየት ኃይል ........ 48

ያፏጨው ሬሳ ..... 50
ጡንቻ ..... 51
በመቃብር ውስጥ የሞተች ሴት ..... 53
እባብ ..... 54
ሹፌር ነዎት? ..... 57
ነብዩ ሮበርት ..... 58
የውሀ ጠብታ ..... 61
ታምረኛው ቀዳጅ ..... 61
መሬት ውስጥ ምን አለ? ..... 62
ሌላዎቹ ፍጡራን ..... 65
የተጣበቁት ልጆች ..... 71
ሌላዎቹ ተጣባቂዎች ..... 75
ቅስና ..... 78
የሚቹ አሻራ ..... 78
ስለደራሲው በጥቂቱ ..... 81

# የተላከ ከጳውሎስ ኞኞ

## ይድረስ ከመጽሐፌ አንባቢዎች፤

እንዴት ከረማችሁ?

ደኅና መሆናችን ደኅና ነገር ነው።

ይሄን ሁለተኛውን የአስደናቂ ታሪኮች መጽሐፍቶቼን ተከታይ አቀረብኩላችሁ ባለፉት በአንዱ አስደናቂ ታሪክ መጽሐፍቶች መቅድም ውስጥ ብዙውን ነገር ተናግሬ ስለጨረስኩት አሁን በዚህኛው መጽሐፌ የምጽፍላችሁ ብዙ የመግቢያ ንግግር የለኝም በዚሁ በቃኝ።

የማትረሱት ነገር አሁንም ቢሆን በዚህ መጽሐፌ ውስጥ ያለውን ዘመን አቆጣጠር እንደሌላዎቹ መጽሐፍቶቼ ሁሉ በዚህም የተጻፈው ዘመን በሙሉ እንደ ኤሮፓ ዘመን አቆጣጠር ነው፤ ለምን እንደማደርግም ከዚህ በፊት በወጡት መጽሐፍቶቼ ገልጫለሁ።

እግዚአብሔር ተርፎ ከሚቀር ዕድሜ ካልነፈገን በአምሰኛው የዚህ ተከታይ መጽሐፍ እስትንገናኝ እስከዚያው ደህና ሁኑ።

# የጁሴፔ መንፈስ

በኢጣሊያ አገር እና በካታንዛሮ መሐል ባለው ወንዝ ድልድይ ሥር የካቲት 13 ቀን 1936 ዓ.ም የ19 ዓመቱ ወታት ጁሴፔ ቬራልዲ ሞቶ ተገኘ።

ፖሊሶች የጁሴፔን አሟሟት መመርመር ጀመሩ። ጁሴፔን ማን ከድልድዩ ሥር እንደወረወረው ወይም ና ገድሎ እንደጣለው ምርመራው በሰፊው ቀጠለ። በፖሊስ በኩል ምርመራው ምንም ፍንጭ ስላላስገኘ በገዛ እጁ ከድልድዩ ላይ ወድቆ ነው የሞተው ተባለና በፖሊስ በኩል ያለው ምርመራ ተዘጋ።

የሟቹ የጁሴፔ ቤተሰቦች እንደ ገና ፋይሉን አንቀሳቅሰው ከጁሴፔ ጋር ከመሞቱ በፊት አብረው ያመሹት ሰዎች እንዲመረመሩ ጠየቁ። አብረው አምሽተዋል የተባሉት ሰዎች አቶ ቶቶ፥ አቶ ዲያሚኖስ፥ አቶ አቤልና አቶ ሮሳሪዮ ተይዘው ለምርመራ ቀረቡ።

«እርግጥ ያንለታ ማታ ጁሴፔን አይተነዋል ጁሶ፤ ከተባለው መጠጥ ቤት እኛ አራታችን ካርታ እንጫወት ነበር ጁሴፔ እኛ ካለንበት ክፍል ገባ፤ ወደኛ ሳይጠጋ ግድግዳውን ተደግፎ ቆመና ቢኖ እንዲቀዳለት አዘዘ። እስከ እኩለ ለሊት ድረስ ሲጠጣ ቆየና ሔደ፤ በጣም ሰክሮ ነበርና እስከ ድልድዩ አቅራቢያ ሸኘነውና በየቤታችን ሔድን» ብለው አራቱም ተመሳሳይ ቃል ተናገሩ።

በተጠራጣሪዎቹም በኩል ምንም ዓይነት የወንጀለኛነት ፍንጭ ስላልተገኘ እንደ ገና የጁሴፔ ፋይል ተዘጋ። ታሪኩ ተረሳ። ጁሴፔ ከሞተ ሦስት ዓመት ሆነው።

ማርያ ታላሪኮ የተባለች የ14 ዓመት ልጅ የካቲት 5 ቀን 1939 ዓ.ም ከሴት አያትዋ ጋር እናትዋን ለመጠየቅ በዚያ ጁሴፔ በሞተበት ድልድይ ላይ አቋርጠው ሔዱ የማርያ እናት በካታንዛሮ ከተማ በተቋቋመው የሞሶሎኒ ፋሺስታዊ ድርጅት ከሚባለው ትሠራ ነበር።

ማርያና አያትዋ የማርያን እናት ጠይቀው ሲመለሱ ጁሴፔ ከወደቀበት ድልድይ ላይ ሲደርሱ ማርያ ከድልድዩ ላይ በድንገት ወደቀች። ጉልበትዋ ላይም ክፉኛ ታመመች። አንድ ጁሴፔ ታራፓዞ የተባለ ሰው ደርሶ ማርያን ከቤትዋ ወስዶ አስተኙዋት።

ማርያ ከተኛች ከአንድ ሰዓት በኋላ አእምሮዋ ተለወጠ። ቀጭን የነበረው ድምፅዋ ጎርናና ሆነ። «አሁኑኑ እናቴን አምጡልኝ» አለች። አንድ የጎረቤት ልጅ ተልኮ ወይዘሮ ታላሪኮ ከምትሠራበት ከሙሶሎኒ ድርጅት ተጠርታ መጣች። ማርያ ወላጅ እናትዋን ስታይ ራስዋን ነቀነቀች። ወዲያው «አንቺ የኔ እናት አይደለሽም፤ ምናልባት የዚህ ቤት ጌታ ትሆኛለሽ እንጂ እናቴስ አይደለሽም። እናቴ የምትኖረው በካታንዛሮ

አምባ ባራኬ በሚባለው መንገድ ነው። ስምዋም ካቴሪና ቬራልጂ ነው። እኔም ልጅዋ ጁሴፔ ቬራልዲ እባለለሁ። አለች።

የማርያ ቤተሰቦች ማርያ ስለምትለው ነገር ምንም አያውቁም። ጎረቤቶች ተጠርተው ተሰበሰቡ። ማርያ በጎርናና የወንድ ድምፅዋ የምትናገረውን ሰምተው በማርያ ላይ ተዋኅዶ የሚናገረው ከሦስት ዓመት በፊት ከድልድይ ሥር ሞቶ የተገኘው የጁሴፔ ቬራልዲ መንፈስ መሆኑን አወቁ።

ጉዳዩ ከከተማው ባለሥልጣኖች ዘንድ ደረሰ። ሐኪሞችም ያቺን ልጅ ለመመርመር ተሰበሰቡ። ዶክተር ጆቫኒ እስካምቢያ የተባሉት ሐኪም እየተመላለሱ 14 ጊዜ መረመሩዋት። ዶክተር ፍራጉላ፤ ዶክተር ፔሪ፣ ዶክተር ማንዚ ካርሌ የአእምሮ ሐኪሞች ትምህርት ቤት ዲሬክተር ማንዚ ካርሌ የካቶላኖ እነኚህ በትጋትና በጥንቃቄ የማሪያ ትላሪኩን ሁኔታ መረመሩ። በሳይንስ በኩል የሚጨበጥና የሚታመን ነገር ይሄ ነው የሚሉትን አጡ።

በመጨረሻ የጁሴፔ እናት ትጠራ ተባለና የጁሴፔ መንፈስ ላደረባት ለማሪያ ወረቀትና እርሳስ ሰጥተው። «ለእናትህ ደብዳቤ ጻፍላት» ተባለ። ማርያ ልጃገረድ ናት። ግን የምትናገረው እንደ ወንዱ እንደ ጁሴፔ ሆና በመሆኑ አነጋጋሮችዋም እንደ ወንድ አንተ እያሉ ነው የሚያነጋግሩዋት።

ማሪያ ወረቀትና እርሳሱን ተቀብላ «የምወድሽ እናቴ ልታይኝ ከፈለግሽ ድህው ልጅሽ አለሁልሽ። ፔፔ» ብላ ጻፈች። ፔፔ የጁሴፔ የቁልምጫ ስሙ ነው። ይህን ጁሴፔ የጻፈውን ደብዳቤ ለጁሴፔ እናት በመስጠት ፈንታ የከተማው ፖሊስ አዛዥ ሰልቫቶሪ ማሎርጂዎ ጥብቅ ቁልፍ ባለው ሳጥን ውስጥ አስቀመጡት። (በመጨረሻ ጊዜ ደብዳቤው በዶክተር እስካምቢያ አላፊነት ለሳይንስ ሊቃውንት ተሰጥቶ በተደረገው ጥናት ጁሴፔ ከመሞቱ በፊት ከጻፈው የብዕር አጣጣል ትክክለኛው የጁሴፔ የብዕር አጣጣል ሆኖ ተገኝቷል።)

በዚያው ዕለት ማታ ማሪያ ከተኛችበት ተነሳች። ከተሰበሰቡት መሐል አራት ወንዶችን መርጣ ለብቻ አቆመቻቸው። የመጫወቻ ካርታ አምጡልኝ አለች። አራቱን ሰዎች በጠረጴዛ ዙርያ አስቀመጠችና «አንተ እንደ ሮሳሪዮ ነህ አንተ እንደ ቶቶ ሁን አንተ ደግሞ እንደ አቤል ሁን፤ አንተ አንደ ዳሚአኖ ሁን።» ብላ አራቱንም ሰዎች በነኛ ጁሴፔን ገድለዋል ተብለው በጥርጣሬ ተይዘው በተለቀቁት ሰዎች ስም ሰየመቻቸውና «በሉ ካራታ ተጫወቱ» አለቻቸው።

እነኚህ የተሰየሙት ሰዎች የካርታ ጨዋታ እንደያዙ ማርያ ካግድግዳው አጠገብ ሔዳ ግድግዳውን ተደግፈው ቆመች ሲጃራ ለኩሳ አንዴ አጨሰችና ቪኖ ቅዱና

ስጡኝ አለች። እዚህ ላይ አንባቢዎች እንዲገባችሁ ያህል ማርያ ይህን ላይዋ ላይ አድሮ ነው። በአጭሩ በአገራችን ዛር ወጣ እንደሚባለው ነው።

ማርያ ቪኖው ተቀድቶ እንደ ተሰጣት «ለምን እንደዚያ ዕለቱ ማታ በቪኖው ውስጥ ስኳር፤ ጨውና የፓፒ ፍሬ (መርዝነት ያለው የአበባ ፍሬ ነው) ጨምራችሁ አልሰጣችሁኝም? አለች። «እንደዚያ አድርጋችሁ ካልሰጣችሁኝማ እንዴት ልትገድሉኝ ትችላላችሁ?» አለች። ከዚህ በኋላ ቪኖውን ደጋግማ ጠጣች።

ማርያ ሞቅ እንዳላት የጠብ መነሳቱንና ለመከላከል የምታደርገውን ሙከራ በግብር ታሳይ ጀመር። ባፍዋም መለፍለፍ ጀመረች። «አቤል፤ ቶቶ፤ ተውኝ እንጂ...... ልቀቁኝ እንጂ..... አትምቱኝ፤ ለምን ትደበድቡኛላችሁ?» አለች። ከዚህ በኋላ ቪኖውን ደጋግማ ጠጣች።

ማርያ ሞቅ እንዳላት የጠብ መነሳሳቱንና ለመከላከል የምታደርገውን ሙከራ በግብር ታሳይ ጀመር። ባፍዋም መለፍለፍ ጀመረች። «አቤል፤ ትቶ ተዉኝ እንጂ.....ልቀቁኝ እንጂ.....አትምቱኝ፤ ለምን ትደበድቡኛላችሁ? እርዱኝ እርዱኝ፤ ኧረ የሰው ያለህ፤...... ከድልድይ ውስጥ ጨምረው ሊገድሉኝ ነውና አስጥሉኝ......» ትል ጀመር። ወዲያው ከመሬት ላይ ዘፍ ብላ ወደቀችና በዚያው እንቅልፍ አሸለባት። ለሊቱን እንደተወራጨች አሳለፈችው።

በማግስቱ ማለዳ ማርያ ከእንቅልፍዋ ነቃች። ወዲያውኑ «እናቴና ቤተሰቦቼ አሁን በአንድ ሰዓት ከዚህ ይደርሳሉ ከዚያም የሚመጡት በትእዛዝ ነው።» አለች ልክ እንዳለችው የሟቹ የጁሴፔ እናት ካቴሪና ቬራልዲ ከጧቱ በአንድ ሰዓት ማርያ ካለችበት ደረሱ።

የጁሴፔ እናት ወይዘሮ ካቴሪና ገና ከበሩ ሲደርሱ የሟቹ የጁሴፔ መንፈስ ያደረባት ማርያ ከአልጋዋ ላይ ዘላ ሔዳ በወይዘሮ ካቴሪና አንገት ላይ ተጠመጠመች። እያለቀሰችም «እናቴ ደኅ፤ እናቴ» እያለች ታለቅ ጀመር።

ለወይዘሮ ካቴሪና ወንበር ካቀረበች በኋላ ግራ የገባቸው ሴትዮ በወንበሩ ላይ ቁጭ ሲሉላት ማርያ ሔዳ ከአልጋዋ ላይ ቁጭ አለች። ከዚያም ወሬ ቀጠለች። «እምዬ ካየሁሽ ሦስት ዓመት ሆነኝ።» አለች። እናትዮዋ ሲመጡ አንዳንድ ነገር ተነግሮአቸው ነበርና ሟቹን ልጃቸውን በቁልምጫ ስሙ ጠርተው «ፔፔ? እንዴት ነው የተገደልከው?» ብለው ጠየቁ።

በማርያ ላይ የተዋኀደው የጁሴፔ መንፈስ ለእናቱ ጥያቄ ሲመልስ «ከጂኦሶ መጠጥ ቤት ነበርን። ከዚያ መጠጥ ቤት ትቶ፤ ዳሚያኖ፤ አቤል፤ ሮሳሪዮ እና እኔ ነበርን። እነሱ ካርታ ይጫወቱ ነበር። እኔ ቪኖ ጠጣሁ። ከጠጣሁ በኋላ በድጋሚው

ቪኖዬ ውስጥ አንዳንድ ነገሮችን ጨመሩበት። እከዚያም ወደ ድልድዩ አጠገብ ወሰዱኝ።

«ቶቶና አቤል በድልድዩ ድንጋይ ላይ አሹኝ። ከዚያ በኋላ ሮሳሪዮ መጣና ራሴ ላይ መታኝ። ቶቶ ዓይነስቤ ላይ ደገመኝ። አቤል ትልቅ ድንጋይ አንስቶ ጥርሴን አወለቀው። ከዚያ በኋላ ልብሴን አወላለቀብኝና ተሸክመው ከድልድዩ ሥር ይዘውኝ ገቡ። ቶቶ በብረት ቁራጭ እጄን ሲመታኝ እጄ ከቁርጭምጭሚቱ ላይ ተሰበረ። ልብሴን ከድልድዩ ባሻገር ወረወሩትና ከራሲ ሥር ድንጋይ አድርገው አስተኙኝ።

«እይው እማዬ፤ እኔ እብድ አልነበርኩም፤ እንዴት አድርጌ ከዚያ ትልቅ ድልድይ ላይ እዘላለሁ? ያን ዕለት ራሴን መርዳት አልቻልኩም። ሰክሬ ነበር። የጠጣሁትም 24 ብርጭቆ ቪኖ ነበር።..... እማዬ? ከጓደኞቼ አንደኛው በሆስፒታል ውስጥ መሞቱን አልሰማሽም?» አለ።

ወይዘሮ ካቴሪና ቬራልዲ እንደሞተ አውያውቁም። ግን በተደረገው ጥናትና መከታተል አቤል በመስከረም ወር 1938 ዓ.ም በልብ ድካም በሆስፒታል ውስጥ መሞቱ ተረጋገጠ።

በማሪያ ላይ ያደረገው የጁሴፔ መንፈስ ወሬውን ቀጠለ «.....ቶቶ በገዛ ፈቃዱ በምሥራቅ አፍሪካ ወደ ኤርትራ ዘምቶ ከጠላት በተተኮሰበት ጥይት ከፉኛ ቆስሏል። ከገዳዮቼ አንደኛው ዲያሚኖ ግን ወደዚህ ቤት ለመምጣት በመንገድ ላይ ነው።» ጋለ። ይህን በተናገረች በአምስት ደቂቃ ውስጥ ዲያሚኖ ከዚያ ልጅቷ ካለችበት ቤት ውስጥ ገባ። የቶቶም ጉዳይ ተጠንቶ ልጅቷ ካለችበት ቤት ውስጥ ገባ። የቶቶም ስለጁሴፔ አገዳደል ቢጠየቅ ከመደንገጡ የተነሳ ራሱን ብቻ በመነቅነቅ ገዳይ ያለ መሆኑን አሳወቀ።

ልጅቱ ማሪያ እነዚህን ሁሉ ሰዎች ለአንድ ቀን እንኳን አይታቸው የማታውቅ ነች። የጁሴፔ ወንድም አቶ ራፋኤልና ጆቫኒ ራቫልዲ ከዚያ ቤት ገና ሲገቡ በስማቸው እየጠራች አነጋግራቸዋለች። ጆቫኒ እናታቸውን ስለማይረዳ እንደማትወደም ተናግራለች።

በኢጣልያ ጦር ሠራዊት ውስጥ ብርጋዲየር ጉግሌምሲታ ከዚያው ቤት ተቀምጠው ይህን ታሪክ ይመለከቱ ስለነበር ማሪያ እንደ ጁሴፒ ሆና «እስተምልክቱ ብርጋዲየር ሲታ በመስኮት ቆመው ሲመለከቱ እኔ ሲጃራዬን እያጨስኩ ባጠገብዎ ሳልፍ በቁልምጫ ሲመለከቱ እኔ ሲጃራዬን እያጨስኩ ባጠገብዎ ሳልፍ በቁልምጫ ስሜ ፔፔ ብለው ጠርተውኝ ወዴት ነው የምትሔደው? አላሉኝም?» ቢላቸው ብርጋዲየር ሲታ ደንግጠው «ማለቱንስ ብያለሁ፤ ግን ይቺ ልጅ እንዴት ስሜን ልታውቅ ቻለች?» ብለው ተገረሙ።

በማሪያ ላይ ተዋኅዶ የሚናገረው የጁሴፔ መንፈስ ታሪክ ብዙ ነው። ታሪኩን የጻፉት ዶክተር እስካምቢያ ሁሏንም ነገር ተንትነዋታል። እኔ ግን ባጭሩ አወራሁላችሁ። መጨረሻው ምን ሆነ?

የካቲት 9 1939 ዓ.ም ማሪያ ከመኝታዋ ተነስታ አራት ሰዎች ተከትለዋት ከድልድዩ እንዲሄዱ ጠየቀች አራት ሰዎች ተመርጠው እንዲከተሉዋት ተደረጉና ወደ ድልድዩ ሔደች። ራቅ ብሎ ግን ብዙ ሕዝብ ይከተል ነበር።

ከድልድዩ ሥር ገባች። እነኛ አራቱ ሰዎች በራስዋ ላይ ጉዳት እንዳታመጣ ሲጠብቋት በድንገት ተወርውራ ጁሴፔ ከወደቀበት ድንጋይ ላይ ወደቀች። ጁሴፔ ተንተርሷት የነበረችውን ድንጋይ ተንገርሳ ተኛች። የጁሴፔ ሬሳ ሲገኝ እንደነበረው የቀኝ እግሯን ራቁት አድርጋ አጥፋው ተኛች።

ማሪያ በዚያ ቀዝቃዛ ድንጋይ ላይ ለአሥር ደቂቃ ያህል ተኝታ ከቆየች በኋላ ነቃች። ከመኝታዋም ተነስታ በዓይንዋ ሁሉን ነገር መቃኘት ጀመረች። የጁሴፔ መንፈስ እንደተለያየ ታወቀ። ለቀረበላትም ጥያቄ «ምን እንደሆንኩ አላውቅም፤ ብቻ በሕልሜ ከድልድይ ውስጥ ገብቶ የሞተውን ጁሴፔን አየሁት። ከእሱ ልጅ ጋር ምንም ንግግርና እውቀት አልነበረንም፤ ለምን እንዳየሁት አላውቅም» አለች።

በእስፔይን ውስጥ የኩሩና ሐውልት የሚባል የአደባባይ ቦታ አለ። በአደባባዩ ባለው ረጅም የድንጋይ ሐውልት ላይ በአራቱ መአዘን አራትስ ሰዓቶች አሉበት። አራቱም ሰዓቶች የሚያሳዩት የጊዜ ልክ የተለያየ ነው። ይህም የተደረገበት ምክንያት በዚያ ቦታ የሚቃጠሩ ሰዎች ልክ በተቃጠሩበት ሰዓት እንዲገናኙና በቀጠሮ ምክንያት እንዳይጣሉ ለማስማማት ተብሎ ነው። በአንደኛው ሰዓት ቀጠሮውን ያሳለፈ ሰው ቢኖር በሌላው ሰዓት ልክ መድረሱን ያስመሰክራል።

# ተመሳሳይነት

በ1900 ዓ.ም ሐምሌ 28 ቀን የኢጣልያው ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኡምቤርቶ ወደ አንዲት ሞንዛ ወደምትባል መንደር ሔዱ። ከንጉሥ ነገሥቱ ጋር ጄኔራል ፖንዚዮ ቫልያ አንዲት ሆቴል ቤት ገቡ። ከዚያም አንድ የሸበተ ረጅም የከንፈር ጢም ያለውን ሰው ንጉሥ ነገሥቱ ተመለከቱና «ይሄን ሰውዬ የማውቀው ይመስለኛል፤ የዚህን ዓይነት ፊት ከዚህ ቀደም አይቻለሁ፤ እስቲ አስጠራውና የት እንዳየሁት ላነጋግረው» ብለው ጄኔራሉን አዘዙ። ያ የሸበተ ረጅም ጢም ያለው ሰው ተጠርቶ ከንጉሥ ነገሥቱ ፊት ሲቀርብ ለጥ ብሎ እጅ ነሳ። ንጉሥ ነገሥቱም «ከዚህ በፊት ብዙ ጊዜ ያየሁህ ይመስለኛል፤ የት ነው ያየሁህ?» ብለው ጠየቁት። ስዎስ ሁልጊዜ ያዩኛል፤ ምክንያቱም መልካችን ተመሳሳይ በመሆኑ መልክዎ መልኬ ስለሆነ ነው» አላቸው።

«እውነትህን ነው» አሉት ንጉሡ «በእርግጥ መልክህ መልኬን ይመስላል፤ ጢምህ፤ ቁመናህ ፊትህ የኔን ይመስላል። ለመሆኑ ስምህ ማነው?» ቢሉት «እኔ አገልጋይዎ ኡምቤርቶ እባላለሁ፤ ይህም ስም የወጣልኝ በ1844 ዓ.ም መጋቢት 14 ቀን ከለሊቱ አሥር ሰዓት ላይ ስወለድ ነው» አላቸው። ንጉሡ ተገርመው «ይሄማ ልክ እኔ የተወለድኩበት ቀን ነው። ለመሆኑ የት ነው የተወለድከው?» አሉት። ሽማግሌውም «ቶሪኖ ነው» አላቸው። ንጉሡም «ቶሪኖማ የትውልድ አገሬ ናት፤ ለመሆኑ አግብተሃል?» አሉት። «አዎ፤ ያገባሁትም በ1866 ዓ.ም ሚያዝያ 2 ቀን ነው፤ የሚስቴ ስምም ማርግሬት ነው፤» አላቸው። አሁንም ንጉሡ ተገርመው «እኔም ሚስቴን ያገባሁት በዚያው ቀን ነው፤ ማርግሬትም የሚስቴ የክርስትና ስም ነው፤» ብለው ተከዙ። ይህ እንደሆነ ጄኔራል ቫልያ ጣልቃ ገብቶ «ልጆች አሉህን» ብሎ ሽማግሌውን ጠየቀ። ሽማግሌውም «አንድ ወንድ ልጅ አለኝ፤ ስሙንም ቪቶሪዮ ብየዋለሁ» አለ። ንጉሡም ቀና ብለው ጄኔራሉን እያዩ «ይሄማ የልጅ የሂሪዲቴሪያ መስፍን ስም ነው፤» አሉና «ይህ አስደናቂ ነገር ነው፤ ለመሆኑ ሥራ ከጀመርክ ስንት ጊዜ ይሆንሃል?» አሉት። ሽማግሌው የሆቴሉ ባለቤት «ይህቺን ሆቴል ቤት የከፈትኳት በ1878 ዓ.ም የካቲት ዘጠኝ ቀን ነው፤» አላቸው። ንጉሡ በዚህም መልስከ ተገርመው «ይሄ አንተ የምትለው ዘመንና ቀን እኔ የኢጣልያ ንጉሥ የሆንኩበት ጊዜ ነው» ብለው ጥቂት ከተጫወቱ በኋላ ንጉሡ ያን ሽማግሌ በማግስቱ ከቤት መንግሥት እንዲመጣ ነግረውት ተለያዩ።

በነጋታው ንጉሥ ኡምቤርቶ ከቤተመንግሥታቸው ሆነው፤ የሽማልጌውን ኡምቤርቶ መምጣት ሲጠባበቁ ጄነራል ቫልያ ከንጉሡ አዳራሽ ገብተው «ግርማዊ ሆይ፤ አዝናለሁ፤ ያ ሽማግሌ ሰውዬ ዛሬ ጧት ሞተ፤ ፖሊሶች ወንጀለኛ መስሎአቸው በጥይት ተኩሰው ገደሉት» አላቸው። ንጉሡም በጣም የሚያሳዝን ነገር ነው፤ የቀብሩ ሥፍራ የት እንደሆነ ጠይቅና በቀብሩ ሥርዓት ላይ እገኛለሁ» ብለው እንዳዘዙ ካልታወቀ ሥፍራ ሦስት ጥይቶች ተተኮሱ። ሦስቱም ጥይቶች በቀዳማዊ ኡምቤርቶ ደረት ገቡ። ንጉሡም ወዲያው ሞተ።

በ1543 ዓ.ም በእንግሊዝ አገር አሣ ነባሪ የንጉሣውያን ዘር አሣ ነው ተብሎ ታውጆ ነበር። በዚያም አዋጅ ውስጥ ማንኛውንም አሣ ነባሪ የሚይዝ አሣ አጥማጅ፤ አሣ ነበሪውን እንደያዘ የአሣ ነበሪውን ራስ ለንጉሡ፤ ጭራውን ደግሞ ለንግሥቲቱ መላክ ነበረበት።

ለደም ባንክ ደምዎን ሰጥተዋል? ያልተሰጡ ደሜ ያልቃል ብለው ፈርተው ነው? ወይስ ደግሞ «ደም የሰጠ ሰው ዕድሜው አጭር ነው» የሚለውን ወሬ ሰምተው ነው? የዊልሔልምን አጭር ታሪክ ልንገርዎት። የሞትወ በ73 ዓመት ዕድሜው ነው። ለደም ባንክ በየጊዜው የሰጠው የደሙ ብዛት 870 ሊትር ነው። ዊልሔልም ክሌን ሲያወራ «......ዕድሜዬ 45 ዓመት ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ደሜን ለደም ባንክ ሰጥቻለሁ። ደሜን በሰጠሁ በ12 ሰዓት ውስጥ የወጣው ደሜ ተመልሶ ይሞላል። በደሜ በደም እጦት ሊሞቱ የደረሱ ወገኖቼ እንደሚድኑበት እየተሰማኝ እደሰታለሁ.....» ብሏል። ዊልሔልም ክሌን ጀርመናዊ ነው። የብዙ መድኃኒቶችም ፈልሳፊ ነበር። በፍራንክ ፈርት ከተማ በነበረበት ዘመኑ የታወቀ ታላቅ ሰው ነበር።

# የተቀበረ ሰው ይነሳል?

ማክስ ሁፍማን የተባለ የአምስት አመት ልጅ በ1865 ዓ.ም በኮሌራ በሽታ ተያዘ። ወላጆቹ ከዊስ ኩንሲን ከተማ ሐኪም አስጠርተው አስመረመሩት። ሐኪሙ «ተስፋ የለውምና አትድከሙ» ብሏቸው ሔደ። ማክስ በሕመሙ ሦስት ቀናት ከተሰቃየ በኋላ ሞተ። ተቀበረ።

ማክስ በተቀበረ በሁለተኛው ዕለት ለሊቱን የማክስ እናት ሕልም አየች። በሕልምዋ ልጅዋ በመቃብር ውስጥ እንዳለ በጎኑ ተገልብጦ ከሳጥኑ ውስጥ ለመውጣት ሲታገልና መውጣት አቅቶት ቀኝ ጉንጮቹን በእጆቹ ተንተርሶ ተመልሶ ሲተኛ አየችው።

ባጠገብዋ ተኝቶ የነበረውን የማክስ አባት ቀስቀሳ መቃብሩን ቆፍሮ የልጅዋን ሬሳ ከነሳጥኑ እንዲያወጣላት ጠየቀችው። አባትዮው ቅዠት ነው ብሎ እምቢ አላት። ተኝተው አደሩ።

እንደገና በቀጠለው ምሽት የማክስ እናት አሁንም በሕልምዋ ልጅዋን አየችው። እንደባነነች ከመኝታዋ ተነስታ መቃብሩ እንዲቆፈርላት ባልዋን አቶ ሁፍማንን ወተወተች። አቶ ሁፍማን ትልቁን ልጃቸውን ቀስቅሰው ጎረቤቶች እንዲጠራላት አደረገ። ጎረቤቶቹ እንደተሰበሰቡ የእናቲቱ ልብ እንዲረጋ ብለው መቃብሩን ለመቆፈር ተስማሙ። መቃብሩ ለሊቱን ሲቆፈር አደረ። ከንጋቱ አንድ ሰዓት ሲሆን የሬሳ ሳጥኑ ወጣ። የሬሳ ሳጥኑ መክደኛ ቢከፈት የማክስ ሬሳ በቀኝ ጎኑ ተገላብጦ ተኝቶ የቀኝ ጉንጨን በእጁ አንተርሶ ልክ እናቲቱ በሕልምዋ እንዳየችው ሆኖ አገኙት።

ማክስ ሕይወት ያለበት ይመስላል፤ ግን ፍጹም እንደሞተ ሰው ቅልስልስ ስለነበረ አባቱ አቶ ሁፍማን የማክስን ሬሳ በፈረስ ይዞ ወደ ሐኪም ዘንድ ወስደው። ሐኪሞቹ ልጁን መርዳት ጀመሩ። በተቀበረ በሁለት ቀኑ ከመቃብር የወጣው ማክስ ሕክምና በተደረገለት በሁለት ሰዓት ውስጥ ዓይኑን መግለጥ ጀመረ። እየቆየም ፍጹም ጤነኛ ሆኖ ተነሳ።

ማክስ በአሜሪካ አገር በኢኦዋ አውራጃ በክሊቶን ቀበሌ ኖሮ በተወለደ በሰማንያ ዓመቱ ሞተ።

አቶ ጀሮሜ ሞኤርማን ቢለጂጋዊ ነው። አቶ ጀሮሜ በፒያኖ ሙዚቃ ጨዋታ ጎበዝ ነው።

ጀሮሜ ፒያኖ መጫወት የጀመረው ገና በልጅነቱ ነው። በፒያኖ ጨዋታ ያሳጨውም የእያንዳንዱ እጁ ጣቶች ስድስት በመሆናቸው ነው። የሌላዎቹ ሰዎች የእጅ ጣቶች አሥር ሲሆኑ የጀሮሜ ግን አሥራ ሁለት ናቸው። አሥራ ጣቶች ያሉዋቸው እጆች ብቻ አይደሉም። የእግሮቹም ጣቶች እንደ እጆቹ ሁሉ አሥራ ሁለት ናቸው። ጀሮሜ በአንድ እጁ ጣቶች አምስት አራት ጠርሙሶች ወይም ብርሌዎች ብቻ ነው። አቶ ጀሮሜ በቤልጂግ ውስጥ በምትገኝ አልሰን በተባለች ከተማ በአንድ ፋብሪካ ውስጥ ይሠራል።

***

# የሚዘንብ ውሃ ብቻ ነው?

ደሱይት ጋስፓር ስኮት የተባሉ ሰው በ1667 ዓ.ም በጻፉት መጽሐፋቸው ከሁለት ሺ ዓመታት በፊት በአቴንስ ከተማ አሣ ዘንቦ እንደ ነበረ ጽፈዋል። አቶ ሉቃስ ጃኮብሰን ዴቢስ የተባሉ ሰውድ እግሞ ፋይሮይ አይላንድ በተባለው መጽሐፋቸው በ1673 ዓ.ም ፋይሮይ በተባለችው ደሴት አሣ መዝነቡን አትተው ጽፈዋል። በ1918 ዓ.ም በእንግሊዝ አገር በዌልስ ከተማ ስለዘነበው አሣ አቶ ዮሐንስ ሊውስ የተባሉ ሰው ሲገልጡ «.....በሁለመናዬ ላይ አንዳንድ ነገር ሲወድቅብኝ ተሰማኝ። ራሴን፤ ጀርባዬን፤ አንገቴን ሁሉ ይመታኝ ጀመር። በእጄ አንገቴን ብዳብሰው የሚፍለከለኩ ነገሮችን አገኘሁ። ባያቸው ከዝናቡ ጋር የወረዱብኝ ትንንሽ አሣዎች ናቸው። ባርኔጣዬን ባወልቀው መዓት አሣ ሰፍሮበት አየሁ።

«መሬቱን ባየው ከሰማይ የሚወርደው አሣ በብዛት ሲፍተእልከለክ አየሁ.....» ብለዋል። በ1824 ዓ.ም በበጋው ወራት በኒዮርክ ዓ.ም ከተማ 1841 ዓ.ም ሰኔ 30 ቀን

በቦስተን፤ 1900 ዓ.ም ሰኔ 27 ቀን ፌሪ በተባለ ከተማ ሣ ዘንቧል። በ1861 ዓ.ም በሲንጋፑር የዘነበው አሣ በአንድ ጋሻ ተኩል መሬት ላይ ጢም ብሎ ተቆልሎ ነበር።

ከሰማይ የሚዘንበው አሣ ብቻ አይደለም፤ ጓጉንቸርና እንቁራሪቶች፤ ሌሎችም አልፎ አልፎ ይዘንባሉ። 1804 ዓ.ም በአሜሪካ አገር በዊንድሀም ቀበሌ እንቁራሪት ዘንቧል (ወርዷል)። በ1901 ዓ.ም በኒውዮርክ ከተማ፤ በ1933 ዓ.ም ሐምሌ 21 ቀን በማሣቹሴትስ አውራጃ በቸልዋስፎርድ ቀበሌ እንቁራሪት ዘንቧል።

በ1939 ዓ.ም ሰኔ 17 ቀን በወጣው ዘታይምስ በተባለ ጋዜጣ አቶ ዌልስ የተባሉ ሰው በጻፉት ጽሑፍ «.....በለንደን ከተማ ዝናቡን ለመሸሽ ስሮጥ ከወደኋላዬ እምቦፍ፤ እምቦፍ የሚል ድምፅ ሰማሁ። ዞር ብዬ ባይ እንቁራሪቶች ከአስፋልቱ ላይ ሲፈጥረው አየሁ። ከእነሱም ጥቂቶቹን ከኪሴ ከትቼ ከቤት ገባሁ» ብለዋል።

ሞንትሪያል ዊክሊ ጋዜት የሚባለው ጋዜጣ እንዳተተው ከ1857 ዓ.ም በሞንትሪያል ከተማ ገበሎ ዘንቦ እንደነበረ ገልጧል። በ1873 ዓ.ም በሜኒሶታ ከተማ እንሽላሊት ዘንቧል። በአሜሪካ በቴኒሲ አውራጃ ሜሞፊስ በተባለ ቀበሌ በ1877 ዓ.ም የካቲት 15 ቀን እባብ መዝነቡ (መውረዱ) ተጽፏል። በ1901 ዓ.ም ነሐሴ 14 ቀን በሐንጋሪ ውስጥ ፃንቴስ በተባለ ቀበሌ የዘነበው በረሮ (ክንፍ ያለው አውሬ) በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ መሬቱን ያንድ ጫማ ያህል ውፍረት በመከመር አልብሶታል።

በ1895 ዓ.ም ሜኒቶባ በተባለ አገር ትልልቅ ጉንዳን ዘንቧል። በ1869 ዓ.ም ጥቅምት 12 ቀን በእንግሊዝ አገር ቴቨርተን በተባለ ቀበሌ ሸረሪት ዘንቧል። እነኚህ ሸረሪቶች ግማሽ ቀን ሙሉ በመዝነባቸው ሜዳዎችንና ቤቶችን ልብሰዋቸው ሰውንም መላወሻ አሳጥተውት ነበር።

የደምም ዝናብ አለ። ሆሜርና ቪርጊል እንደጻፉት ግብፅ አገር የደም ዝናብ ዘንቧል። ተዘዋዋሪው ታሪክ ጸሐፊ ግሪጎሪ እንዳለው ደግሞ በ582 ዓ.ም በፓሪስ ከተማ ቀይ ውሀ (ደም) መዝነቡን ገልጿል። እንዲያውም በ1903 ዓ.ም በላው ኤሮፓ ቀይ ዝናብ ዘንቧል። አንድ የኢጣልያ ጋዜጣ ስለዚያን ዘመኑ ዝናብ እንደጻፈው «.....ከተማይቱ በሞላ በቀይ ቀለም የተነከረች ትመስላለች። ከባዱ የሚወርደው ገናብ ደም ይመስላል። ሰማዩ ፍጹም የጠራ ቢጫ ይመስል ነበር። እየቆየ ግን ቢጫ የነበረው ሰማይ ፍጹም ቀይ ሆኖ ታየን......» ብሏል።

ጥቁር ዝናብም ዘንቧል። በአሜሪካ አገር በካሊፎርኒያ አውራጃ ፍሬስና በተባለ ቀበሌ በ1926 ዓ.ም ጥቁር ዝናብ ዘንቧል። በዝናቡ ውስጥ ይሄዱ የነበሩት ሰዎች ማንኛውም ዓይነት ልብሳቸው ወደ ጥቁርነት ተለውጧል።

ይህን ከሰማይ የሚወርደውን ነገር የማያውቁ ብዙ ወገኖች ስላሉ እንዲያውቁት ያህል ሌላ ጥቂት ልጨምር ድንጋይ፤ መስትዋትና ብረትም ይወርዳል።

ይህ በፎቶ ግራፉ ላይ የምታዩት ከሰማይ የወረደ ብረት ነው። ብረታማው ድንጋይ ከሰማይ ወርዶ ከመሬት ሲያርፍ አራት ቦታ ተከፍሎ ነበር። ይህ ብረታማ ድንጋይ ሎንግ አይስላንድ በተባለ ቦታ ወረደ። የዚህ ብረታማ ድንጋይ ክብደት 440 ኪሎ ነው። ይህ ብረታማ ድንጋይ አሁን በቺጋጎ ኔቸራል ሂስትሪ ሙዚየም ውስጥ ይገኛል።

ይህ ሞሪቶ በተባለ ቦታ ከሰማይ የወረደ ብረት ነው የዚህ ብረት ነው የዚህ ብረት ክብደት 6900 ኪሎ ነው በለንደን፤ ብሪትሽ ሙዚየም ኔችራል ሂስትሪ (ሙዚየም) ዲፓርትሜንት ውስጥ ይገኛል። በብዙ ቦታዎች ብዙ ድንጋዮችና ብረታማ ተፈጥሮዎች ወርደዋል። ዛሬ በዓለም ላይ በየሙዚየሞቹ ካልቱ ጥቂቶችን አስገብቻቸዋለሁ።

በኒውዮርክ፤ አሜሪካን ሙዚየም ኔቸራል ሂስትሪ ሙዝየም ውስጥ ሊቅ የሆኑ ዶክተር ክሎይድ ፊሽር በዚያው ሙዚየም ቆመው የማያጠኑት ከሰማይ የወረደ ብረት ነው። ይህ ብረት የተገኘው አህኒጊቶ በተባለ ቦታ ነው። ክብደቱም 27.200 ኪሎ ነው።

እነዚህ ድንጋዮች ወይም ብረቶች ከየት እንደሚመጡ አይታወቅም። ሊቃውንት እንደሚያምኑትና እንደሚናገሩት ከሆነ፤ «ከተወርዋሪ ኮከብ እንደሚመጣ እንገምታለን» ይላሉ። ብረቱ ወይም ድንጋዩ እንደወረደ ወይም ከመሬት እንዳረፈ የጋለ ነው። በጥቂት ጊዜ ውስጥ ግን ተመልሶ ይቀዘቅዛል።

የዚህ ነገር አወራረድ በቅርብ ጊዜ የጀመረ ሳይሆን ታሪክ ከመጻፉ በፊት ጀምሮ ወደ መሬት ይወርዳል። እብብዙ አገሮችም ለብዙ አምልኮት ውሏል። የጥንት ሰዎች ከእግዚአብሔር የተላከ ነው በማለት ያመልኩት ነበር። የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 19 ቁጥር 35 ቢመለከቱም ያገኙታል። ስለዚህ ጉዳይ ሰፋ ያለ ሐተታ ቢኖርም ያን ልተወውና እንዲያው ወደ አጫጭሩ ጉዳይ ልመለስ።

በ1947 ዓ.ም 1400 ያህል ብረትና ድንጋይ ከሰማይ ወደ መሬት ወርደዋል። ድንጋዩ ወይም ብረቱ ከሰማይ በሚወርድበት ጊዜ እንደ ከፍታው መጠን ከፍተኛ ድምፅ ያሰማል።

ጊዜው ጨለማ ከሆነ ነበልባል ያሳያል። ከመሬት አየር ክልል ውስጥ ከገባ በኋላ ያለው ፍጥነት ከተመሳሳዩ ቦታ ተመሳሳይ ድንጋይ ከመወርወር እኩል ነው ይላሉ ሊቃውንቱ።

በ1769 ዓ.ም የታተመ አንድ የጀርመንኛ እትም ያንን የእጅ ስዕል አውጥቶ ከስዕሉ ሥር በጻፈው መግለጫ «በ1768 ዓ.ም ኅዳር 20 ቀን ማርኪርቸን አጠገብ ከሰማይ የወረደው ድንጋይ አወዳደቅ» ብሎታል።

እነዚህ ድንጋዮች ወይም ብረቶች ብዙ ጊዜ በብዙ ቦታዎች ወርደዋል በአርካንሳስ ውስጥ ፓራጉልድ በተባለ ቦታ 352 ኪሎ፤ በፊላንድ ውስጥ ቡጅርቦሌ በተባለ ቦታ 292 ኪሎ ቼኮዝሎቫኪያ ውስጥ ኪንያሂንያ በተባለ ቦታ 257 ኪሎ ክብደት ያላቸው አንድ ወጥ ድንጋዮች ወርደዋል። ማሰልቸት ይሆናል እንጂ ብዙዎቹን መዘርዘር ይቻል ነበር። በተለይ በደቡብ አፍሪካ ሆባ በተባለ ሥፍራ በ1917 ዓ.ም የወረደው ድንጋይ 52.800 ኪሎ ክብደት እንዳለው ሊታውንት ገምተዋል። ሌላው ታላቅ ድንጋይ ደግሞ በግሪንላንድ ምዕራባዊ ጠረፍ ኬፕዮርክ በተባለ ቦታ የወረደው ነው። የዚያ ድንጋይ ክብደት ሰላሳ አንድ ሺ ስድስት መቶ ሰማንያ ኪሎ ነው።

በአነስተኛ ቅርጽም ተበታትኖ ይወርዳል። ለምሳሌ ያህል ጥቂቶቹን ላምጣቸው። በ1886 ዓ.ም በፖላንድ ውስጥ ፑልቱስክ በተባለ ቦታ ከዘነበው 100.000 ጠጠሮች ተለቅመዋል። በ1912 ዓ.ም በአሪዞና ውስጥ ሆሌብሮክ በተባለ ቦታ ከዘነበው 14.000 ጠጠሮች በ1883 ዓ.ም በፈረንሳይ አገር ለኤግል በተባለ ቦታ 3000 ጠጠሮች ተለቅመዋል። ከእነዚህ ጠጠሮች መሐል አብዛኞዎቹ ብረትማዎች ናቸው። ሊቃውንት እንደሚሉት «ሲመጣ አንድ ድፍን ሆኖ ይመጣና ከመሬት አካባቢ አየር ውስጥ በሚያደርገው ከፍተኛ ግጭት ይበታተናል» ይላሉ።

ይህ በፎቶ ግራፉ የምታዩት ዛሬ በለንደን በብሪትሽ ሙዚየም ኔቸራል የሚገኘው ተንሐም በተባለ ቦታ ከወደው ኮረት ጥቂቱ ነው።

የአገር ወይም የባቄላ ፍሬ የሚያህልም ይወርዳል። እንደ አቧራ ሆኖ እየበነነ የሚወርድም አለ። በተለይ በኤሮፓና በአሜሪካ ክረምት በሚሆንበት ጊዜ ይህ አቧራ ሆኖ የሚወርደው በበረዶው ክምር ላይ እየተነጠፈ ይገኛል።

በአውስትራሊያ ከዘነበው ብረት መሐል ለዓይነት ያህል ከተለቀመው ጥቂት ነው።

ከሰማይ የሚወርደው ድንጋይ በሚያጎላ መነጥር ሃያ ጊዜ አድጎ ስታይ ይህን ይመስላል።

እነዚህ ከሰማይ የሚወርዱ ድንጋዮች ወይም ብረቶች ከመሬት ሲያርፉ ትልልቆቹ መሬቱን ደህና አድርገው ይቦድሱታል። ለምሳሌ በአሪዞና ውስጥ ከዊንስሎው ምዕራባዊ ደቡብ የወደቀው ድንጋይ መሬቱን 1200 ዲያሜትር ቦድሶታል። ቡደሳውም ይሄ ነው።

# ሌላው ዮናስ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ዮናስ ሦስት ቀን በአሣነባሪ ሆድ ውስጥ ማደሩን ይናገራል። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ብለው የማያምኑ ብዙዎች ናቸው። እንዲያ ዓይነቱ ነገር በሌላም ጊዜ ቢሆን ደርሷል። ፈረንሳዊው ሳይንቲስ ደ ፓርቪል 1914 ዓ.ም ዡርናል ደ ዴቤትስ በሚባለው ጋዜጣ ላይ ከዚህ የሚከተለውን ጽፏል። በየካቲት ወር 1891 ዓ.ም የምሥራቅ ኮከብ የተባለች መርከብ ፎክላንድ ደሴት አቅራቢያ መንሳፈፍ ጀመረች። ይህቺ የአሣ ማጥመጃ ጀልባ ከደሴቲቱ ሦስት ማይል ያህል ርቃ ሔደች። በዚያም ቦታ ከአንዲት ሌላ አሣ አጥማጅ ጀልባ ጋር ተገናኝተው የማጥመድ ሥራቸውን ቀጠሉ። ወዲያውኑ ብዙ አሣ ነባሪዎች ስላዩ በአንደኛይቱ ጀልባ ላይ ያሉት አጥማጆች የአሣ ነባሪ መውጊያ ጦራቸውን አንደኛው ድንጋይ ላይ ወረወሩ። ጦሩ አሣ ነባሪውን በሚገባ ሳይወጋው ከወደ ጭራው ላይ ተሰካ። ይህ የቆሰለ አሣነባሪ ያቺን ጀልባ ገለበጣት። በጀልባዋ ላይ የነበሩት ሰዎች ሁሉ ከባሕሩ ውስጥ ወደቁ። ከሰዎቹ መሐል ሁለት ሰዎች ሰጠሙ። ሰው ፈጽሞ ሊገኝ ስላልቻለ ፍለጋውን ተዉት። ከጥቂት ድካምም በኋላ ያን አቁስለውት የነበረውን አሣነባሪ ገደሉት። ሰብስበው የአሣ ነባሪውን ገላ መሸንሸን ጀመሩ። በመጥረቢያ በፋስ የተቻላቸውን ያህል መገነጣጠሉን ሠርተው ጊዜው ስለመሸ ሥራቸውን አቆሙ። በነጋታው የተረፈ ሥራቸውን ሲያከናውኑ ወደ አሣነባሪው ሆድ ገደማ እንደ ደረሱ አንድ የሚላአወስ ነገር ተሰማቸው። ቶሎ ቶሎ ብለው ያን የሚላወሰውን ነገር ቢያወጡት ትናንት ጧት ከባሕር ሰጥሞ የጠፋው ጓደኛቸው ጀምስ ሆኖ አገኙት። ከዚያም የመርከቢቱ አዛዥ፤ ጀምስን ወደ ክፍሉ አስገብቶ አስተኛው። ጀምስ አልሞተም እንጂ ምንም ነገር አያውቅም። ከዚያም የመርከቢቱ ሠራተኞችና ካፒቴኑ ሆነው ጀምስን ሁለት ሳምንት ሙሉ በሚገባ ተንከባክበው አሳከሙት። ሁለተኛው ሳምንት እንዳለቀ ጀምስ እየተሻለው ሔደ። አንዱን ሳምንት አገግሞ ሦስተኛው ሳምንት ሲያልቅ ጀምስ ሥራውን ጀመረ። ሆኖም ጀምስ በአሣነባሪው ሆድ ውስጥ በመጠኑ ተጎድቶ ስለነበር እጆቹ፤ ፊቱና አንዳንድ አካሉ እንደወትሮው አልነበሩም። ጀምስ ስላለፈው ታሪክ ሲያወራ «በአሣነባሪው ጭራ አንዲ መመታቴ ትዝ ይለኛል፤ ከዚያ በኋላ አንድ ጭለማ ወደ ሆነ ትልቅ አዳራሽ ውስጥ መግባቴን አውቃለሁ፤ ወደዚያ ቦታ የገባሁበት መንገድ ሁሉ ልስልስና የሚያሟልጭ ነበር። በዚህ ምክንያት ይመስለኛል በቀጥታ እየተገፋሁ ወደ ፊት ሔድሁ፤ ከማርፍበት ቦታ ደርሼ ሳርፍ በእጆቹ አንዳንድ ነገሮንች መነካካት ጀመርሁ። እነዚህም የምነካካቸው ነገሮች አንዳንዶቹ ሸካራ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ በጣም ልስልስ ነገሮች ናቸው። እንደ ወትሮው በሚገባ መተንፈስ አልችልም ነበር። የምተነፍሰው በትንሹ ነበር። ከሁሉም ደግሞ ያስቸገረኝ ሙቀቱ ነበር። በጣም አስጨናቂ ሙቀት ነበረበት። ብዙ በመቆየቴ ይመስለኛል ከሙቀቱ ኃይልና ትንፋሽ

ከማጣቴ የተነሳ እየደከምኩ ሄድኩ። ከዚያ በኋላ የማውቀው ነገር ከካፒቴናችን አልጋ ላይ ተኝቼ መገኘቴን ነው» ብሏል።

***

ወደው ያውቃሉ? የፍቅርስ ደብዳቤ ጽፈዋል? ስንት ደብዳቤ? 10 – 20 – 30 ደብዳቤዎች? ወይስ አንድ መቶ ደብዳቤዎች? መቶ ደብዳቤዎች ጽፈው ከሆነ ጎበዝ ነዎት። በስዊድን አገር ካርል መንሰን የተባለ አትክልተኛ ግን በስድስት ወር ውስጥ ለእመቤቱ 600 የፍቅር ደብዳቤዎች ጽፏል። በዚህ ብቻ አይደነቁ። የሩሲያው የሙዚቃ ሊቅ ትቼይኮቭስኪ በ13 ዓመት ጊዜ ውስጥ ባልዋ ለሞተባት ለወይዘሮ ናዴዣ ቮን ሜክ 5000 ደብዳቤዎች ጽፏል። በዚህም ብቻ አይገረሙ። ጁሌት ድሮኔት የተባለች አክተር ለታወቀው ሙዚቃ ደራሲ ለቪክቶር ሁጎ 15000 ደብዳቤዎች ጽፋለች። በየቀኑ ደግሞ መገናኘት ይችሉ ነበር። አስገረምዎት። አንድ አስገራሚ የፍቅር ደብዳቤ ዛሬ በብሪትሽ ሙዚየም ውስጥ ይገኛል። የተሳፈው በቀዳማዊት ንግሥት ኤልሳቤጥ ባለሟል በሆነች ሴት ነው። ይቺ ሴት ለአራቤላ ቫጓን የጻፈውችው ደብዳቤ 410000 ቃላት ይዟል።

# አዲሱ ነቢይ

አቶ ጴጥሮስ ሁርኮስ የተባለ የደች የምድር ጦር ባልደረባ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ በጀርመኖች ተማርኮ በጀርመን ወህኒ ቤት ታስሮ ነበር። ሁርኮስ ምንም ዓይነት የጅ ጥበብ ሥራ ስለማይችል በቀለም ቀቢነት እንዲያገለግል የወህኒ ቤቱ ሹማምንት መርጠውት ነበር። በዚሁ ሥራው በ1943 ዓ.ም በሰኔ ወር ወደ ጀርመን ወታደሮች መኖሪያ ሠፈር ሄዶ የቆሸሹትን ቤቶች ቀለም እንዲቀባ ተደረገ።

ሁርኮስ አንድ ቀን 36 ጫማ ርዝመት ካለው መሠላል ላይ ሆኖ ቀለም ሲቀባ እግሩን አዳልጦት ከመሠላሉ ላይ ወደቀ። ከመሬት ሲወድቅ ራሱ ተፈነከተ። ወዲያውኑ ዘይዱዋል ወደሚባል ሆስፒታል ተወሰደ።

ሁርኮስ ሦስት ቀናት ሙሉ በሆስፒታሉ ከተኛ በኋላ ሻል ሲለው ዓይኑን መግለጥ ጀመረ። የት እንዳለና ምን እንደሆነ አያውቅም ነበረና ሲነቃ ከጎኑ አንድ በሽተኛ በመተኛቱ ከሆስፒታል ውስጥ መሆኑ ተረዳ። ወዲያው አጠገቡ ያለውን በሽተኛ ትርኩ ብሎ ተመልክቶ «አንተ አርድ ካም ቤርግ አይደለህም?» ብሎ ጠየቀው። ሁርኮስ እስከዚህ አርድ ካምቤርግ ከተባለ በሽተኛ ጋር ምንም ዓይነት እውቂያና ግንኙነት አልነበረውምና ካምቤርግ ደንግጦ ዝም አለው።

ሁርኮስ ግን «አንተ መጥፎ ሰው ነህ፤ አባትህ ሲሞት በኑዛዜ የሰጠህን ወርቅ ሰዓት ሸጠህ አጨበጨብክበት። አገርህስ ሮተርዳም አይደለም? አሁንም ቁም ሣጥኑ ውስጥ በተቀመጠው ልብስህ ኪስ ውስጥ ጥቂት ገንዘብ አለ፤ እሱን ገንዘብ ከምትሠራበት ቦታ የሠረቅኸው አይደለም?» አለው።

ይህን ሲነጋገሩ አንዲት ነርስ ገባች። ሁለቱ በሽተኞች በነርስዋ ዳኝነት ተከራከሩ። ሁርኮስ አጠገቡ ያለው በሽተኛ ሌባ መሆኑን ለማስመስከር በልብሱ ኪስ ውስጥ ያለውን ገንዘብ ቁጥሩን ጭምር ተናገረ። ነርስዋ ይህን ጉዳይ ለሆስፒታሉ ሐኪም ለዶክተር ፒተርስ ተናገረች። ዶክተሩ መረመረው። በሳይንስ በኩል ይህ ነው እይሚባል ነገር አልተገኘም።

ሁርኮስ ሕመሙን ድኖ ከሆስፒታል ወደ እስር ቤቱ ተወሰደ። በእሥር ቤቱ ሆኖ ሁሉ ነገር የሚታየው በመሆኑ እሥረኞች ጓደኞቻቸው ምን እንደሆኑና ጦርነቱም እድነኢት እንደሚካሔድ እየጠየቁት ትክክለኛውን ይነግራቸው ጀመር።

የሁርኮስ ዝና በጀርመን ባለሥልጣኞች ዘንድ በመታወቁ ሁርኮስ ጀርመን ባለሥልጣኖችን የትና እምን ሥፍራ እንደሚገኙ ይጠቁም ጀመር። ሁለተኛው የዓለም ጦርነት እንደተፈጸመም ሁርኮስ ወደ አገሩ ወደ ዳች ተመልሶ ከፖሊሶች ጋር ተባብሮ እንዲሠራ ተደረገ።

በ1948 ዓ.ም በስዊድን አገር ሔልገም በተባለች ከተማ ቪኦላ ዊዴግሬን የተባለች ነርስ ጠፋች። መጥፋትዋን አባቷ ለፖሊሶች ነገረ። ፍለጋው በፖሊሶች ተከናውኖ ምንም ፍንጭ ታጣ። ፖሊሶች ሁርኮስን ወደ ጠፋችው ነርስ አባት ወደ አቶ ካርል ዊደግሬን ቤት ወሰዱት። ሁርኮስ ከዚያ እንደደረሰ አዘነ። ፖሊሶቹ ለምን እንዳዘነ ቢጠይቁት በሰው እጅ መገደልዋን ነግሮ «ከዚህ ቤት ቶሎ አስወጡኝ» ብሎ ጮኸ።

ከዚህ በኋላ ከባለሥልጣኖች ዘንድ ሁርኮስን ወሰዱት ሁርኮስ ለባለሥልጣኖቹ «ነርስዋን አርዶ የገደላት አባትዋ ነው። ሬሳዋንም ከቤቱ ውስጥ ከዋናው በር ጎን ቀብሮታል» ብሎ ተናገረ።

ቤክ ፊዚካል ሪሰርች ፋውንዴሽን የተባለው ድርጅት በ1957 ዓ.ም አቶ ጴጥሮስ ሁክስን ከነሚስቱ በገንዘብ ገዝቶ ለጥናት ወደ አሜሪካ አገር ወሰደው። በአሜሪካ አገር በብዙ ሊቃውንት የሁርኮስ ጭንቅላት ተመረመረ። የሚጨበጥ የሳይንስ ጥበብ አልተገኘበትም።

በ1959 ዓ.ም በጥር ወር በቪርጂኒያ አውራጃ አቶ ካርል ጃክሰን የተባሉ ሰው ከነቤተሰባቸው በመኪና ሲሔዱ እይደረሱበት ጠፉ። የነዚህ ሰዎች ሁኔታ ሲፈለግና ሲጠና ቆይቶ ከሁለት ወር በኋላ የአቶ ካሰንና ያንድ ሕፃን ልጃቸው ሬሳ አናፓሊስ በተባለው ቦታ ተገኙ። በጥይት መገደላቸውም ተረጋገጠ። በዚያው ዓ.ም በመጋቢት

22 ቀን ደግሞ የእናትዮዋና የስድስት ዓመት ልጃቸው ሬሳ ፍሬደሪክስበርግ በተባለ ቦታ ከቁጥቋጦ ውስጥ ተገኙ። እነሱም በሰው መገድላቸው ተረጋገጠ። ማን ገደላቸው?

የሰዎቹን ገዳዮች ለማግኘት ከፍ ያለ ፍለጋና ጥረት ተደረገ። ምንም ፍንጭና ውጤት ባለመገኘቱም የሚቾቹን ደም ለመበቀል አዳግቶ ፋይሉ ሞተው የተገኙ በሚል አርእስት በፖሊስ ተዘጋ።

በ1960 ዓ.ም በሰኔ ወር ዶክተር ፍራንሲስሬስንማን የተባሉ በዋሽንግተን ከተማ በቅድስት ኤልሳቤጥ ሆስፒታል የአእምሮ ሐኪም የሆኑት አቶ ጴጥሮስ ሁርኮስን አስጠርተው «ጎረቤቶቼ የነበሩት የአቶ ጃክሰን ቤተሰቦች በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድለዋል። የእነሱን ገዳይ እስኪታገኝ ደረስ በየቀኑ አንድ መቶ የአሜሪካ ብር እሰጥሃለሁ፤ ለምታደርገው ወጪ ደግሞ በተለይ እከፍልሃለሁና ፈልግ» አሉት።

የቨርጂኒያ አውራጃና የከተማው የፖሊስ መኮንኖች ተሰብስበው ከሚቹ ከአቶ ጃክሰን ሬሳ ላይ ያገኙትን ሸሚዝ ለሁርኮስ ሰጡት። ሁርኮስ ሸሚዙን እያየ መናገር ጀመረ። «.....ገዳዩ አንድ የማይረባ ሰው ነው፤ ሰካራም፤ ጠጉሩ የተንጨባረረ፤ ...... በትንሽ ጎጆ ውስጥ የሚኖር ነው።» ካለ በኋላ ገዳዩ የሚጠጣውን የሲጃራ ዓይነት፤ ሚስትዮዋ ሁለት የፊት ጥርሶችዋ «......አሁን መብትሄዱ ከሰባራ ወንበር ላይ ተቀምጦ ታገኙታላችሁ» አላቸው።

ፖሊሶቹ ሁርኮስ ካላቸው ቦታ ሔዱ። ልክ ሁርኮስ እንዳላቸው ሰውየው ሰባራ ወንበር ላይ ተቀምጦ አገኙት። ሚስቱም ሁለቱ የፊት ጥርሶችዋ ወላቃዎች ሆነው አገኙዋቸው። ምን እንዳወለቀው ቢጠይቋት «ባሌ ሰክሮ ደብድቦኝ ነው» አለች። ሰውዬው ሲጠየቅ እነ አቶ ጃክሰን መግደሉን አመነ።

በ1950 ዓ.ም በታኅሣሥ ወር ከዌስት ሚኒስተር አቤይ አንድ የከበረ ድንጋይ ተሰረቀ። የዚያ ድንጋይ መሠረቅ ከእንግሊዝ ጋዜጦች አልፎ በመላው ዓለም ጋዜጦች ተወራ። በለንደን ከተማ ፖሊሶችም ላይ ብዙ የመቀለጃ ጽሁፎች በመታተማቸው ፖሊሶቹ መሳቂያ ሆነው ቅስማቸው ተሰበረ።

የእንግሊዝ አገር ፖሊሶች የተሰበረ ቅሳምቻውን ለማቃናት ሰራቂውን በጥብቅ መከታተል ጀመሩ። ምንም ፍንጭ አልተገኘም። በመጨረሻው ከሁርኮስ ጋር መነጋገሩ የሚበጅ መሆኑን አመኑና ሁርኮስን ከአሜሪካ አስመጥተው ተገናኙት። ዕቃው ከጠፋበት ከዌስት ሚኒስተር አስገብተው የሁርኮስን ቃል ያዳምጡ ጀመር።

ሆርኮስ፤ ሌቦቹ የከበረውን ድንጋይ ሲሰርቁ ከዚያች ቦታ ሆነው ሲበሉ ይወዳደቁትን ፍርፋሪዎች አገኘና ፍርፋሪዎቹን መመርመር ጀመረ። «የለንደንን ከተማ ካርታ አምጡልኝ» አለ። ተሰጠው። ሁርኮስ ከዚያች ቀን በፊት የለንደንን ከተማ አይቷት አያውቅም። ሁርኮስ በካርታው ላይ ሌቦቹ የሔዱበትን መንገድ በእርሳስ

ማቅለም ጀመረ። ከዚያ በኋላ ሌቦቹ የገቡበትን ቤት፤ ሌቦቹም ሦስት ወንዶችና አንዲት ሴት መሆናቸውን ጠቅላላ ዝርዝር ሁኔታቸውን ጭምር ዘርዝሮ ነገራቸው። ፖሊሶቹ ሁርኮስ በሰጣቸው መመሪያ መሠረት እየተመሩ ሰዎቹን ማግኘት አቅቷቸው በሦስተኛው ወር ሲይዙዋቸው ሁሉም ነገር ልክ ሁርኮስ እንዳለው መፈጸሙን የለንደን ፖሊሶች መግለጫ አወጡ።

በ1951 ዓ.ም በነሐሴ ወር በሆላንድ አገር ኒዢሜገን የተባለ መንደር በእሳት ተያያዘ። ቃጠሎው እጅግ በጣም ከባድ በመሆኑ የጦር ሠራዊት ወታደሮች ቃጠሎውን ለማጥፋት ሕዝቡን እንዲረዱ ተደረገ። ቃጠሎው ሊጠፋ ባለመቻሉ የመኖሪያ ቤቶች፤ የእህል ጎተራዎችና መሸጋገሪያ ድልድዮች ሁሉ ተቃጠሉ። ብዙ ሕዝብም መጠጊያ አጣ።

ይህ ቃጠሎ በደረሰ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ሁርኮስ በዚያ ቀበሌ ከአንድ ሰው ጋር እየተጫወተ ሲሄድ በድንገት ወሬውን አቋርጦ ለጓደኛው «ደግሞ አንደገና ሌላ ትልቅ ቃጠሎ ሊነሳ ነውና ና ሮጠን ለፖሊስ እንንገርህ» ብሎ እየሮጡ ፖሊስ ጣቢያ ሲደርሱ ቃጠሎው ተነሳ። በዚያም ቃጠሎ የኒዥሜገን የጨርቃጨርቅ ፋብሪካም ተቃጠለ።

ሁርኮስ ፖሊሶቹን ለመርዳት አስቦ እሳቱን የሚያነሳውን ሰው ለማወቅ ፈለገ። ሁርኮስ ዓይኑን ጨፈነ፤ ጥቂት አሰበና የኒዢሜገንን ቀበሌ ፖሊስ አዛዥ ሻምበሉን «እስቲ ከተቃጠሉበት ቦታ ውሰዱኝ» አላቸው። አመዱን አንስቶ በእጁ ይዞ እያየ «አገኘሁት» አለ። «አንድ ልጅ ይታየኛል፤ ልጁም ገና ጎረምሳ ነው። ግን አንዴት ልለየው» አለ። ፖሊሶቹ ምን እናድርግልህ ቢሉት «እስቲ የተማሪዎቹን ደብተር አምጡልኝ» አላቸው። የቀበሌዋ ተማሪዎች ደብተርና የተማሪ ቤት ፎቶ ግራፍ ያለበት ካርዳቸው ተሰጠው ከካርዶቹ መሐል እሳት የሚለኩሰውን ልጅ ፎቶ ግራፍ መርጦ «ይሔ ነው ልናነጋግረው የምንፈልገው ልጅ» ብሎ ለፖሊሶች ካርዱን ሰጠ።

ልጁ ተይዞ ፖሊስ ጣቢያ ተወሰደ። ሁርኮስ ከዚያም ሆኖ ምርመራው ቀጠለ። ልጁ ወንጀሉን አልፈጸምኩም ሲል ካደ። ሁርኮስ ይህን መካዱን ሲሰማ ተናደደና «የግራ እግርህን ሱሪ ወደ ላይ ሰብስብና እሳቱን አቀጣጥለህ በትሸሽ የአጥር እሾሃም ሽቦ የሞነጫጨረህን ገላህን ለፖሊሶች አሳይ» አለው። ፖሊሶቹ ሱሪውን ቢገልጡ ልክ ሁኮስ እንዳለው ቡጭርጭሩ ተገኘ። ልጁም አድራጎቱን በሙሉ አመነ።

አንድ ጊዜ ደግሞ አንድ ሰው ከበራፉ ላይ ሞቶ ተገኘ። ሁርኮስ የሟቹን ኮት ደባበሰና «አንድ ሽማልጌ ሰው ነው የገደለው። ገዳዩ ሽማግሌ ነጭ መነጥር ያደርጋል፤ ከላይኛው ከንፈሩ ላይ ጢም አለው። አንድ እግሩ ተቆርጦ የእንጨት እግር ገብቶለት የሚሔድ ነው። የገደለበትንም መሣሪያ ከቤቱ ጣሪያ ላይ ደብቆታል» ብሎ ለፖሊሶች ነገረ። በሁርኮስ ምሪት ፖሊሶቹ ተከታትለው ሲይዙ የሰውየው ገዳይ ሆኖ የተገኘው

የሚቹ አማች ሆነ። ጉዳዩ ከተያዘ በኋላ የገደለበትንም መሣሪያ ከጣሪያ ላይ አውርዶ ለፖሊሶች ሰጠ መነጥሩና የባለ እንጨት እግር መሆኑም ፖሊሶችን አስደነቃቸው።

ሁርኮስ መልሱን እንዴት ለማግኘት እንደሚችል ሲጠየቅ እንዴት እንደሆነ አላውቅም ይላል። በ1958 ዓ.ም በአሜሪካ አገር ያሉ የሕክምና ሊቃውንት ተሰብስበው ሁርኮስን ከመረመሩ በኋላ ባወጡት መግለጫ «ሁርኮስ አንጎሉ እንደራዳር ነው። ከሳይንስም አባባል የተለየ ፍጡር ነው» ብለዋል። ሁርኮስ የሠራው ተአምር እጅግ ብዙ ነው። አገሮች ብዙውን ታሪኩን ጽፈውለታል። ሙሉው ዝርዝር ታሪኩ አይሁን እንጂ የሁርኮስ ታሪክ በኢትዮጵያ ጋዜጦችም ተወርቷል። በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በ52 ዓ.ም ገደማ በኢትዮጵያ ድምፅ ጋዜጣ የሁርኮስ ከፖሊሶች ጋር የመሥራት ወሬ ተጋኖ ተወርቷል።

ሁርኮስ ጥቅምት 3 ቀን 1961 ዓ.ም በአሜሪካ በቴሌቪዥን ለሕዝብ እንዲታይ ቀርቦ ነበር። ሁርኮስን በመጠየቅ ለሕዝብ እንዲያቀርብ የተመረጠው የቴሌቪዥን ሪፖርተር እንዲህ ሲል ጽፎለታል።

«.....በቴሌቪዥን እስቱዲዮ ውስጥ የተሰቀለው ትልቁ ሰዓት 8.50 (ከምሽቱ ለሦስት ሰዓት አሥር ጉዳይ) ይላል ፕሮግራሙ ሊጀመር የቀረው አሥር ደቂቃ ብቻ ነው። አሥርዋ ደቂቃ እስክትደርስ ሁርኮስ ከፊት ለፊቴ ካለው መቀመጫ፤ ላይ ተቀምጧል። 35 ዓመት ሙሉ በተናጋሪነት በሠራሁበት ዘመን ውስጥ እንደዚያች አሥር ደቂቃ ረጅምና ቶሎ የማይደርስ ጊዜ አጋጥሞኝ አያውቅም።

«.....መድረሱ አይቀርምና ሰዓቱ ደረሰ። ዝነኛውን ሁርኮስን አስተዋወቅሁ። ..... ከዚያ በኋላ በእጄ ይዤያት የነበረችውን መጽሐፍ ለሁርኮስ ሰጠሁትና «ይቺ መጽሐፍ የምትነግርህ ነገር አለን?» አልኩት። መጽሐፍዋ የአንዲት ልጃገረድ መጽሐፍ ነበረች። ልጅቷ በሰው እጅ ተገድላ ሞታለች። ገዳይዋ ማን መሆኑ ስላልታወቀ አልተያዘምና የልጅቷ ሞት ጉዳይ እንዲሁ ባክኖ የቀረ ነበር። ይኼን ሁሉ ነገር እኔ አውቃለሁ እንጂ ሁርኮስ ስለልጅቷም ሆነ ስለመጽሐፍዋ የሚያውቀው አንዳችም ነገር አልነበረም። እኔም አንዲትም ፍንጭ አልገለጽኩለትም ነበር።

«ሁርኮስ መጽሐፍዋን ከእጄ ተቀበለኝና አያት። ቀስ ብሎም ወደ ግራ እጁ አሳለፋት። ይሔ ሁሊ ሲሆን መጽሐፍዋን ገልጦ አላያትም። ወዲያውኑ «እጄን ተመልከት። «ብሎ ጮኸ። መጽሐፍዋን ከያዘበት ከግራ እጁ መዳፍ ላብ ሲወጣ አየሁ። የቀኝ እጁን ባይ ምንም ላብ የለበትም። «ሞታለች» አለ ሁርኮስ «መተንፈስ ባለመቻልዋ ነው የሞተችው» ደምዋ ጉሮሮዋን አፍኖ ነው የገደላት። የመታትም ከወደኋላዋ ነው። ልጅቱ ከሰውየው ለማምለጥ ከመኪናው ውስጥ እወጣለሁ ስትል፤ ከወደኋላዋ መታት። ከጆሮዋ ሥር ገደማ ነው የመታት። ያን ጊዜ ወደቀች። ሰውየው ስለፈራ ሬሳዋን ከድልድዩ በታች ካለው ትልቅ ጉድባ ውስጥ ጥሎ መኪናውን ነድቶ ሔደ»

ብሎ ተናገረ። ሁርኮስ ይህን ሲናገር በቴሌቪዥኑ እስቱዲዮ ውስጥ ከውጭ የተጋበዙ እንግዶቹና ቴክኒሺያኖቹ ጭምር በጠቅላላው 34 ሰዎች ነበሩ። ሁሉም ፈዘው የሁርኮስን ንግግር ያዳምጣሉ።

«ሌላስ ምን የምትጨምረው ነገር አለ? ጌታው ሁርኮስ አልኩት። አቶ ሁርኮስ መጽሐፍዋን ይዞ «ልጅቱ የሞተችው በዚያው በጉድባው ውስጥ ነው። ቦታው አገር ቤት አይደለም። በከተማም ውስጥ አይደለም። ከከተማ በሰውየው መኪና ወጡ። አንድ ድልድይ አለ። ከድልድዩ አጠገብ ደግሞ አንድ ብዙ ጊዜም ተመላልሶበታል። ሰውየው እኮ - » አለአን ሁርኮስ ዝም አለ። ቀጠለና «ከዚህ ለኢላ አልናገርም። ብናገርም እዚህ ቦታ አልናገርም። ለፖሊሶች መናገር እፈልጋለሁ» አለ።

«ልጅቷ የሞተችው ከሁለት ዓመት በፊት ነበር። ሁርኮስ የልጅቷን መጽሐፍ ብቻ በጣቱ ነክቶ የተናገረው ትክክል ነበር። ሁርኮስ የልጅቷ ገዳይ የሚኖርበትን ቤትና ዘመዶችን ሁሉ ዘርዝሮ ለፖሊስ ነገረ። ፖሊሶችም ሁርኮስ የልጅቷ ገዳይ ነው ያለውን ሰው ፎቶ ግራፍ ከሌሎች ፎቶ ግራፎች ጋር ደባልቀው ሁርኮስ ሰየውን እንዲመርጥላቸው ሰጡት። ሁርኮስ የገዳዩን ፎቶ ግራፍ መርጦ አወጣና «ይሔ ነው የገደላት። በዚህ በፎቶ ግራፉ ላይ ጥርሱን ማየት አትችሉም እንጂ ጥርሱ ፍንጭት ነው» ብሎ ለፖሊሶቹ ነገረ። ሰውየው ተይዞ ቢመረመር መግደሉን አምኖ ፍርድ ቤት ቀረበ። ይህን የሁርኮስን ታሪክ በጻፍኩበት ጊዜ የገዳዩ ፍርድ አላለቀም ነበርና። በማለት ጋዜጠኛው ያየውን ጽፏል።

በእንግሊዝ አገር በኬንት ውስጥ ሐይዝ ፓሪሽ የተባለ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እይሁለት ሺ ሰዎች አጽም አለ። እነዚህ አጽሞች፤ ሰባት መቶ ዓመት ያህል ዕድሜ እንዳላቸው ይገመታል።

የዳሌና የቅልጥም አጥንቶች በግድግዳ ጥጋት ይዘው ተከምርረዋል ይህም ክምር ሦስት ሜትር ከፍታና 15 ሜትር የጎን ርዝማኔ አላቸው።

እነዚህ አጥንቶች ከተገኙት ከአንድ ቦታ ከተገኘ ቁቆር ነው። ሰዎቹ በምን ምክንያት እንደሞቱ በትክክል አልታወቀም። ሊቃውንትም በአሳብ ተለያይተዋል። ግማሾቹ በአንድነት ያለቁ መርከበኞች ናቸው። ሲሉ ግማሾቹ ደግሞ ተስቦ በሽታ እይፈጃቸው ናቸው። ይላሉ።

በ1918 ዓ.ም የካቲት 22 ቀን በአሜሪካ አገር ኢሊኖይስ ውስጥ እይተወለደው ሮበርት ፔርኒንግ ዋድሎው ረጅም ነው ነበር። ሮበርት፤ በተወለደ በስድስት ወሩ አሥራ ሁለት ኪሎ ይመዝን ነበር። ዕድሜው 16 ዓመት ሲሆን ቁመቱ 2 ሜትር ሲሆን ቁመቱ 2 ሜትር ከ፵ ሳንቲሜትር ነበር። ክብደቱ 149 ኪሎ ተኩል ያህል ደርሶ ነበር። በ22

ዓመት ዕድሜው በዋሸንግተን ዩኒቨርሲቲ የሕክምና መምህር የሆኑት ዶክተር ቻርለስ እንድለኩት፤ ሁለት ሜትር 72 ሳንቲሜትር ሲሆን፤ ክብደቱ ደግሞ 198 ኪሎ ሆነ።

ሮበርት በዚህ ቁመቱና ውፍረቱ አይጨነቅም፤ አይሰጋምም ነበር። ብቻ ከቤቱ ወጥቶ በሚሔድበት ጊዜ በመንገድ ላይ ሕዝቡ እየከበበው አላስኬድ ስለሚለው ይቸገር ነበር። አልጋው፤ ወንበሩና ሌላው የቤት ዕቃው እንደልብሶቹና ጫማዎቹ ሁሉ በልዩ ትእዛዝ የሚሠሩ ነበሩ። ሮበርት የሚያደርገው ጫማ ርዝመቱ 47 ሳንቲ ሜትር ነበር። የጅ ጣቱ ከመዳፉ አንጓ አንስቶ የመሐከለኛው ጣቱ ጫፍ ድረስ ያለው ርዝመት 30 ሳንቲ ሜትር ነበር።

እንዲህ ያለ ረጅም ሰው ለቅርጫት ኳስ ጨዋታ ተፈላጊ ነው። ሮበርት ግን ኳስ የሚሉ ነእግር አይወድም ነበር። የማይርስበት ሰለሚያውቅ ነው። ከዚህም ሌላ የሮበርት ጡንቻዎች፤ እንደሌላዎቹ ልከኛ ሰዎች ጡንቻዎች የጠነከሩና እንደፈለገውም የሚታዘዙ አልነበሩም። የሮበርትን ታሪክ ፍሬደሪክ ፋድነር የተባሉ ሰው «ግዙፍ ጨዋ ሰው» በሚል አርእስት አንድ መጽሐፍ ጽፈዋል። ታሪኩና ጨዋታው ደስ የሚል ስለሆነ መጽሐፉ በብዛት ተሸጧል። በዚህ መጽሐፍ ግን በዚሁ በአጭሩ፤ ሐምሌ ፲፰ ቀን በ22 ዓመት ዕድሜው ሞተና በኢሊኖይስ አልተን ውስጥ አክውድ በተባለ ቦታ ተቀበረ። የሬሳው ሳጥኑ ርዝመት 3 ሜትር ከ28 ሳ. ሜ ሲሆን የጎኑ ስፋት 82 ሳ.ሜ ሆኖ ጥልቀቱ 76 ሳ.ሜ ነበር።

በስዕሉ እንደምትመለከቱት ሌላው ረጅም ሰው ባለ ጥቁር ሰው ባለ ጥቁር ከረባቱ አቶ ቴድ ኢቫንስ ነው። ቴድ የቆመው ታሪኩን ካነበቡት ከኖርበት ጋር ነው። ቴድ በእንግሊዝ አገር ሱሬይ በተባለ ከተማ ይኖር ነበር። ቴድ በከተማው ውስጥ የሚመላለሰው በተለይ በተሠራለት ብስክሌት ላይ ሆኖ ነው። የእንግሊዝ የሕክምና ጋዜጣ ሜዲካል ጄርናል መስከረም 27 ቀብ 1950 ዓ.ም ባወጣው ቁጥሩ ስለቴድ ብስክሊት እንደጻፈው «.....የብስክሊቱ ኮቻ ያንዲት ወፍራም ሴት ጭን ያህላል.....» ብሏል።

እንዲያው ታሪክን መለስ ብለን ያየን እንደሆነ በመጽሐፍ አዱስ ውስጥ የባሳን ንጉሥ ህግ የተባለው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ1450 ዓ.ም የነበረው በእብራውያን አለካክ ቁመቱ 9 ኩቢት ነበር። የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ኦሪት ዘዳግም ም. 3 ቊጥር 11 ላይ «.....ባልጋው የብረት አልጋ ነበር። እርሱ በአሞን ልጆች አገር በረባት አለ። ርዝመቱ ዘጠኝ ክንድ፤ ወርዱም አራት ክንድ በሰው ክንድ ነበር.....» ይለዋል። ግን ኩቢት የሚሉትን የእብራውያን መለኪያ ወደዘመናዊ ሜትር ስንለውጠው አራት ሜትር ይሆናል። ስለዚህ የንጉሥ ዐግ ቁመት ስምንት ክንድ ነበር ማለት ነው።

በዚያው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት ረጃጅም ሰዎች መካከል አንዱ ጎልያድ ነው። ውስጥ ካሉት ረጃጅም ሰዎች ልደት በፊት 1006 ዓ. ዓ ነው። የአማርኛው

መጽሐፍ ቅዱስ በመጽሐፈ ሣሙኤል ቀዳማዊ ምዕራፍ 17 ቁጥር ላይ ስለ ጎልያድ ሲያያት «....ቁመቱም ስድስት ክንድ ከስንዝር የሆነ.....» ይልዋል። በእብራይስጡ አለካክ 6 ኩቢት ስለሚለው ስድስቱን ኩቢት ወደ ሜትር ስንለውጠው 2 ሜትር ከዘጠና ሳ. ሜ ስለሚሆን የጎልያድ ቁመት ለስድስት ክንድ ጋት የጎደለው ነበር ማለት ነው።

የሰውን ተፈጥሮ ያጠኑ የነበሩት ፈረንሳዊው አቶ ፓውል ቶፒናርድ በጻፉት መጽሐፉቸው እንደገለጡት «.....በዓለም ላይ ረጅሙ ሰው በ1714 ዓ.ም ተወልዶ በ1749 ዓ.ም የሞተው የፊንላንዱ ሰው ዳንኤል ማይንኸር ካጃኑስ ነው።.....» ብለዋል። የዳኤንል ርዝመት 2 ሜትር ከ82 ሳ.ሜ ነበር። የዚያ ሰው የቀኝ እግሩ ወርች አጽም ዛሬ በኔዘርላንድ ውስጥ ላይደን በሚባል ሙዚየም ውስጥ ተቀምጧል።

አቶ ፔር ሌሞልት የተባሉ የፈረንሳይ አካዳሚ ባለ በ1847 ዓ.ም ለአካዳሚው በሰጡት ሪፖርት ላይ «.....በ1811 ዓ.ም ተወልዶ በ1844 ዓ.ም የሞተው የሩሲያ መንግሥት ወታደሮች ከረቦ መቼ የነበረው ኢቫን አስኖቪች ሉሽኪን ርዝመቱ 3 አርሺን 9 ተኩል ቤርሾክ በመሆኑ በዘመኑ ከነበሩት የሰው ዘሮች ሁሉ የበለጠ ርዝማኔ ነበረው.....» ብለአል። የኢቫን መለኪያው ወደ ሜትር ስንለውጠው ሁለት ሜትር ከ52 ሳንቲ ሜትር መሆኑ ነው። የኢቫን አጽም አሁን ሌኒንግራንድ ውስጥ ባለው የሳይንስ አካዳሚ ውስጥ ተቀምጧል።

በስኮትላንድ ባለች በርኔሬይ በተባለች ደሴት በ1825 ዓ.ም ከአሥራ ሦስት ጤነኛ ልጆች መሐል የተወለደው አንጉስማክ ስኪል የተባለ ሰው ቁመቱ 2 ሜትር ከ36 ሳ.ሜ ነበር ይህ ሰው ተወልዶ እስቲጎረምስ እንደማንኛውም ሕፃን አደገ ከጎረመሰ በኋላ ግን የቁመቱ ነገር እየጨመረ ሔደ። ዕድሜው 21 ዓመት ሲሆን ቁመቱ 2 ሜትር ከ36 ሳ.ሜ ደረሰ። በ1845 ዓ.ም በኒውዮርክ ከተማ ሐኪሞች ለኩትና የደረቱ ስፋት አንድ ሜትር ከ78 ሳ.ሜ ሲሆን ክብደቱ ደግሞ 162 ኪሎ ሆነ ግን በዚህ ሁሉ ሥጋው ውስጥ ምንም ስባት ወይም ጮማ እንደሌለው ሐኪሞች አረጋግጠዋል።

አንጉስ በክብደት ማንሳት በኩል እስከ ስድስት መቶ ኪሎ ድረስ መሸከም ይችል ነበርና በብዙ አገሮች እየተዘዋወረ ትርኢቱን ለሕዝብ አሳይቷል። አንጉስ ጠጪ ነበር። አንድ ጊዜ 140 ጋሎን መጠጥ ያለበትን በርሚል አንስቶ ከበርሚሉ ማንቆርቆሪያ ጠጥቷል። አንጉስ ቤተ ክርስቲያን ሳሚ ማጥፋት የማያስብ ሰው ነበር። አንጉስ እንዲህ የሆነው ጉልበት አጥቶ ሳይሆን በሰላም መኖርን የሚወድ ሰው ነበር።

አንድ ጊዜ መቶ ኪሎ ክብደት ያለው በኒውዮርክ ከተማ በከባድ ሚዛን ታጋይነቱ የታወቀው ሰው በኖቫስኮትያ፤ ከተማ አንጉስን በትግል ለመግጠም ትግሉ አበቃ። አንድ ጊዜ ደግሞ እንግሊሽታውን በተባለ ከተማ ከሁለት ሰዎች ጋር ትግል እንዲገጥም ተደረገ። ሁለቱ ሰዎች ከመታገያው ሰገነት ወጡ። አንጉስም ወጥቶ ከመሐከላቸው ቆመ። ጀምሩ የሚለው ድምፅ ሲሰማ አንጉስ በሁለት እጁ ሁለቱን

ሰዎች ይዞ ከመሬት ጣላቸው።ወዲያው ትግሉ ቆመ። አንደኛው ታጋይ እጁን ተሰብሮ ተገኘ።

አንድ ጊዜ 880 ኪሎ ክብደት ያለውን የመርከብ መልህቅ ከመሬት አንስቶ መልሶ ለማስቀመጥ እችላለሁ ብሎ በአንድ እጁ ሺ ብር ተወራረደ። ከዚያ በኋላ መልህቁን በባዶ እጁ አንስቶ መልሶ ሲያቀምጥ ትከሻውና ደንደሱ ጉዳት ደረሰበት። በዚያው ሳቢያም በ1853 ዓ.ም በኖቫስኮትያ ከተማ ሞተ።

ከረጃጅም ሰዎች አንዱ ዶን ኬህለር ነው። በአሜሪካ አገር በሞንታና ውስጥ ዴንተን በተባለ ቦታ በ1929 ዓ.ም ተወለደ። ዶን ሲወለድ ብቻውን አልነበረም። መንትያው የሆነች ሴት እህቱ አብረዋ ተወልዳለች። የዶን ቁመት ሁለት ሚትር ከ49 ሳ.ሜ ነበር። መንትያው እህቱ ግን ቁመቷ እንደሱ አልነበረም። የእሷ ቁመት አንድ ሜትር ከ75 ሳ.ሜ ነበር።

ይህም ቁመትዋ፤ ቢሆን በወንድምዋ ሁኔታ ተገምቶ ነው እንጂ እንኳን ለሴት ልጅ ለወንድም ቢሆን ረጅም የሚያሰኝ ነው ዶንና እህቱ በፎቶ ግራፉ ላይ የምታዩዋቸው ናቸው።

እንዲያው የሴትን ረጅም ጉዳይ ካነሳሁ ስለ ረጃጅም ሴቶች፤ ጥቂት ላውራላችሁ።

ሐኪሞች በሕክምና ታሪክ ውስጥ እንደጄን (አንዳንዴም ጂኒ ይሏታል) ያለች ረጅም ሴት የለችም ይላሉ። ጂኒ በእንግሊዝ አገር ባርትሌይ በተባለ ቦታ ሐምሌ 26 ቀን 1895 ዓ.ም ተወለደች። እስከ አሥራ አንድ ዓመት ዕድሜዋ ድረስ እንደማንኛውምስ እው አደገች። በአሥራ አንድ ዓመት ዕድሜዋ ራስዋን ተፈነከተች። እከዚያ በኋላ እድገቷ ተለወጠ። በአሥራ ሦስት ዓመት ዕድሜዋ ቁመትዋ አንድ ሜትር ከ95 ዓ.ም ሆነ።

ጃኒ ከሞተችበት ከሚያዝያ 1 ቀን 1922 ዓ.ም ቀደም ብሎ ተለከታ ቁመትዋ ሁለት ሜትር ከ31 ሳ.ሜ ደርሶ ነበር። የጂኒ አጽም በስተግራ በፎቶ ግራፉ ላይ የምታዩት አሁን በርሚንግሃም የሕክምና ዩኒቨርስቲ በሰው ቅርጻቅርጽ ሙዚየም ውስጥ ቆሞ ይታያል። አሁን ያለው የአጽሙ ርዝመት ሁለት ሜትር ከ23 ሳ.ሜ ነው። ከጂኒ አጽም ጋር የቆመው ሌላው አጽም፤ የደንበኛ ሴት ቁመት አጽም ነው።

የሰው ዘር አጥኚ ሊቃውንት የካቲት 10 ቀን 1972 ዓ.ም በኢጣልያ አገር ባብሩብታ ላይ በቁፋሮ አንድ አጽም አግኝተው ነበር። በዚያ የተገኘው የሴት አጽም ሁለት ሜትር ከ52 ሳ.ሜ ቁመት ነበረው በካናዳ የተገኘው በኖቫስኮትያ አንድ አጽም ተገኝቶ ነበር። በዚያ የተገኘው አጽም በ1846 ዓ.ም ተወልዳ በ1888 ዓ.ም የሞተችው የወይዘሮ አና ሐኔን ስዋን አጽም ነበር። የወይዘሮ አና አጽም ርዝመት ሁለት ሜትር

ከ47 ሳ.ሜ ርዝማኔ ነበረው። በሙዙሪ ውስጥ ጎሪንግ በትባለ ቦታ በ1875 ዓ.ም ተወልዳ በ1913 ዓ.ም የሞተችው የኢላ ዊንግም አጽም ከተቀበረበት እንዲወጣ ተደርጓል። ኢላ አሥር ዓመት ዕድሜ በነበራት ጊዜ ቁመትዋ ሁለት ሜትር ከስድስት ሳንቲ ሜትር ነበር በሃያ ሦስት ዓመት ዕድሜዋ ተለከታ ቁመትዋ ሁለት ሜትር ከሃያ አራት ሳንቲ ሜትር ደርሶ ነበር። በሞተችበት ዘመን አቅራቢያ የቁመትዋ ልክ ሁለት ሜትር ከሃያ ስምንት ሳንቲ ሜትር ደርሶ ነበር።

ሌላው ባለታሪክ ኤድ ካርሜል ነው። ኤድ ካርሜል ቁመቱ አምስት ክንድ ተኩል ነው። ከቤት ውስጥ ሲቆም ጠጉሩ ጣሪያውን ይነካል። ሲወለድ ስምንት ኪሎ ተኩል ይከብድ ነበር። አሁን ካደገ በኋላ አራት ሰዎች የሚበሉትን ምግብ ላንድ ጊዜ ይመገባል። ይህቺ አመጋገቡ ቅም ስለማትለውም ይበሳጫል።

ኤድ ኑሮው ሁሉ አያስደስተውም። በመንገድ ላይ በሚሄድበት ጊዜ መንገደኞቹ ሁሉ እየቆሙ ያዩታል። አንዳንዴም ይሰድቡታል። አንዳንዶቹም ድንጋይ ይወረውሩበታል ይህን ሁሉ ለመታገስ ቢሞክርም የሚጠጋው ጓደኛ በተለይ ደግሞ የከንፈር ወዳጅ ባለማግኘቱ ያዝናል፤ ይበሳጫል።

የሰላሳ ዓመት ዕድሜ ያለው ኤድ ሲያወራ «....ከቤተሰቦቹ በቁመቴ አንድ ሜትር ብበልጥም የሚያሰጋኝ የወደፊት እድገቴ ነው። አሁን ግን በአጋጣሚ ከአሥር ዓመት በፊት እድገቴ እንደነበረው ሳይሆን ቀስ እያልኩ ማደግ ጀምሬአለሁ። ባለፉት ሁለት ዓመቶች ያደግሁት ሦስት ኢንች ያህል ነው። ሐኪሜ ግን ከእንግዲህ ወዲያ የምታድገው በዓመት አንድ ኢንች ብቻ ነው ብሎኛል.....» ይላል።

የኤድ ጉዳይ እንደ ተጠናው ከንጉሥ ዳዊት ጋር እንደ ተጣላው በጎልያድ በ28 ኢንች ወይም በ71 ሳንቲሜትር ይበልጣል። በ1940 ዓ.ም ከሞተው ከሮበርት ፐርሺንግ በአራት ሳንቲ ሜትር ይረዝማል። ሮበርትን የሳንሉዊስ ዩኒቨርስቲ በዓለም ተወዳዳሪ የሌለው ረጅም ሰው ብሎት ነበር። ኤድ ሲጫወት እንዲህ ይላል። «.....በ19536 ዓ.ም በቴልአቪቭ ከተማ ተወለድሁ። ዕድሜዬ ስድስት ዓመት እንደሆነ ርዝማኔው ጀመረኝ። በአሥራ አንድ ዓመት ዕድሜዬ አንድ ሜትር ከሰማንያ ሳንቲ ሜትር ረዘምሁ። የማልረሳው ነገር በተማሪ ቤቱ ከአስተማሪዎቹ ሁሉ እኔ እረዝም ነበር። ደግነቱ ሕመም የሚባል ነገር እስካሁን አላውቅም።

«አንድ ጊዜ ወታደርነት እንድመለመል በሕጉ መሠረት ተጠየቅሁ፤ በደስታ ሄጄ ተመዘገብሁ። መዝጋቢዎቹ ሁኔታዬን ካዩ በኋላ ጉባኤ አድርገው የተለየ ጫማና ልብስ በተለይ የምግቡ ጉዳይ አስቸጋሪ ነውና ወንድም ወደ በኢትህ ሒድ ብለው አሰናበቱኝ።...... ይቺ ዓለም ለረጃጅሞችና ለድንክዬዎች አስቸጋሪ ናት። እንዴት ብትሉኝ ጓድ ሊያደርጋቸው የሚፈልግ ሰው የለምና ነው። ይህም ቢሆን የኔው ችግር ደግሞ ከድንክዬዎች የተለየ ነው። በዚች ዓለም ላይ ለኔ የሚስማሙ ልኬ የሚሆኑ

ሁለት ነገሮች ብቻ ናቸው፤ ምንድናቸው? ብትሉኝ ዣንጥላና መሐረብ ብቻ ናቸው። ሌሎቹ ነገሮች ልኬ ስላልሆኑ ከልክ በላይ የሆነ ገንዘብ ያስወጡኛል። ጫማዬል ሱሪዬ፤ የእግር ሹራቤና ሌሎችም በዓለም ላይ ለማንም ልክ የማይሆኑ ትልልቅ ነገሮች ናቸው።

«ሆቴል ቤት እንኳ ገብቼ አልጋ ስይዝ ሁለቱን አልጋዎች እባንድነት ያጋጥሙኛል። የሁለት አልጋ ኪራይይም እከፍላለሁ። የትም በመኪና ለመሔድ ስፈልግ ከኋላው መቀመጫ በአግድሞሽ ተጋድሜ መቀመጫውን በሙሉ ሞልቼው ነው የምሔደው ከማንም ቤት ስገባ ሥራዬ መቆም ነው። የሚሆነኝ መቀመጫ አላገኝምና ነው።

«ቁርሴ እንደተለመደው 12 እንቁላሎች፤ 14 ዳቦዎች፤ ሁለት ወይም ሦስት ኬኮች በትልቅ ብርጭቆ ሙሉ የብርቱካን ጭማቂ፤ ሦስት ሲኒ ቡና ናት። ለምሳዬም ቢሆን ይሄን ያህልም አይደለሁም። ሁለት ወይም ሦስት ዶሮዎች፤ ስድስት ደህና ደህና ድንች፤ ሩብ ኪሎ አይብ፤ አንድ ትልቅ ፍሬ እነኚህን ከቀመስሁ በኋላ ደህና ኩባያ ሙሉ ቡና እጠጣለሁ ይቺ አበላል እንዲያው ለአዘቦቱ የተለመደችዋ ናት። የሚገርማችሁ ነገር ጠግቤ መብላት የምፈልገው ራቴን ነው። ለእራቴ እንደተለመደው የምበላው አራት ኪሎ ሥጋ፤ አንድ ኪሎ ተኩል የሚመዝን እስፓጌቲ (ፓስታሹታ) እና በጣም ብዙ የሆኑ ሰላጣና ፍራፍሬዎች ሌሎች ነገሮችንም እጨማምራለሁ።

«ችግሬ የመንገድ ላይ ሰዎች ናቸው። ግራ የሚያጋቡኝ። አንዳንዶቹ እዩት ይሄን ደደብ ዕቃ ይሉኛል። አንዳንዶቹ ደግሞ ይሄውላችሁ ያ ለሮኬት ወደ እስፔስ የሚጓዘው ይሉኛል። መንገድ ቢሳሳተኝ እንኳን ማንንም ሰው የእንዲህ ያለ መንገድ በየት በኩል ነው ብዬ አልጠይቅም። ለምን መሰላችሁ? እየደነገጡ ስለሚሸሹኝ ነው። ይህን የመሳሰለው ነገር ሁሉ ቢያናድደኝም ማንንም ለመጣላት አልፈልግም። ምክንያቱም በዚህ ታላቅ መዳፌ አንዱ አናታቸውን ብለው ቀንጥሼ እንደምጥላቸው ስለማውቅ ነው። ለዚህ ብዬ እንው ሰላማዊ ሰው የሆንኩት.....» ስለማውቅ ነው። ለዚህ ብዬ ነው ሰላማዊ ሰው የሆንኩት.....» ይላል ኤድ።

ኤድ የልቡን ሚስጥር ሲያዋይ በኒውዮርክ ከተማ የወንዶችንና የሴቶችን ክበብ እየተዘዋወረ ማየቱን ይናገራል። ስለ ሴቶቹ ሲያወራም «የሚያቁኝ አይፈሩኝም፤ አንዳንዶቹ ግን ማስፈራርቾ እየመስልኳቸው ይሸሹኛል። በዚህ ምክንያት ከሴቶች ጋር ያለኝ ግንኙነት የሚያስደስተኝ አይደለም። በዚሁ ቁመቴ ምክንያትም ሥራ ለመያዝ እንኳን አልቻልኩም። ምክንያቱም የሚሠራው ሥራ ከታች ሲሆን እኔ ያለሁት ከላይ በመሆኔ ነው። መቀመጫም ቢሰናዳልኝ አልቻልኩም። አሁን ከቤቴ ቁጭ ብዬ ሥራዬ ቴምብር ማጠራቀም ብቻ ሆንዋል።» ይላል።

ነገሮቹን ለመጨረስ ያህል የእያንዳንዱን ሰው ርዝማኔ እንተወውና በዓለም ላይ ካሉ የሰው ዘር ውስጥ የየትኛው ጎሣ ወይንም ወገን ሰዎች ረጃጅም እንደሆኑ

እንዴት እስካሁን ካነበብናቸው ለየት ባለ ሁኔታ አሁን በዓለም ላይ ካሉ የሰው ዘሮች ሁሉ ረጃጅም ሰዎችን የሚበልጡ በአፍሪካ ውስጥ በሩዋንዳ የሚገኘው የባቱሲ ጎሳ ባቱሲ ጎሣ ሰዎች መሐከለኛው ቁመታቸው አንድ ሜትር ከ78 ሳንቲ ሜትር ነው።

ብዙ ውሸታም እንዳልሆኑ ይገባኛል። የውሸታሞች ማኅበር ቢኖር እርስዎ ደህና ልምምድ ካላደረጉ አባል አይሆኑም ነበር። በፈረንሳይ አገር በደቡባዊ ፈረንሳይ ማንክራቢ በተባለ ውሸታሞች የሚሠለጥኑበት አካዳሚ አለ። አካዳሚውን ያቋቋሙት አንድ መነኩሴ ናቸው። በዚያ አካዳሚ የሚሠለጥኑ በየዓመቱ ፈተና ይሰጣቸዋል። ተፈታኙ አንድ ውሸት የሆነ ረጅም ታሪክ ያወራል ውሸቱ ሲደነቅ ፈተናውን ያልፋል። ከሁሉ የበለጠ ውሸት ተናጋሪው የዓመቱ የውሸታሞች ንጉሥ ይባላል። ይህ አካዳሚ የተቋቋመው በ1749 ዓ.ም ነው። በ1974 ዓ.ም 225ኛውን ዓመቱን በታላቅ ሥነ ሥርዓትና ብዙዎች ተማሪዎች በተገኙበት አከብሯል።

# ሰው ሳር ይሆናል?

በአፍሪካ አገር በቴኒስ አውራጃ ጋላቲን የተባለች ሴት ነበረች። በዚያች አምባ አቶ ዳዊት ላንግ የተባሉ ሰው ከቤተሰቦቻቸው ይኖሩ ነበር። መስከረም 23 ቀን 1880 ዓ.ም ከወደ ኋላ ፀሐይዋ ደምቃ እንደበራች አቶ ዳዊት ከቤት ይወጣሉ። ሚስትዮዋ ከተል አሉና «ስማ ዳዊት ሳትሄድ እፈልግሃለሁና ቶሎ ተመልሰህ እንድትወስደኝ» አሉዋቸው።

አቶ ዳዊት ሠረገላቸውን ለመጫን ከፈረሶቹ ዘንድ ደርሰው ነበርና የሚስታቸውን ጥያቄስ ሲሰሙ የሚስታቸውን ጥያቄ የኪስ ሰዓታቸውን አውጥተው አዩና «በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ተመልሼ መጥቼ እወስድሻለሁ ወንዱ ልጃቸው የአሥራ አንድ ዓመት ልጃቸው ሣራ ከአባታቸው አቅራቢያ ከእናታቸው አጠገብ ቆመው ነበር።

አቶ ዳዊት ለሚስታቸው መልስ በሰጡ በአንድ ሰከንድ ጊዜ ውስጥ ተሰወሩ። እምጥ ይግቡ ስምጥ ጠፉ። ልጆቻቸውና ሚስታቸው ፈልገው በማጣታቸው ጉዳዩን ለከተማው ሹማምንት ነገሩ። ሹማምንቶቹ መጥተው መሬት ተንዶ ውጦአቸው እንደሆን፤ ወይን ደግሞ መሬት ውጣ መሬት ውጣ ተዘግታ እንደሆን በማለት መሬትዋ እየተደበደበች ፈለጉ። አቶ ዳዊት ጠፉ።

ቤተሰቦቻቸው ለሊቱን ሁሉ ጠበቁ። ጠበቁ። ሳምንት ሙሉ ጠበቁ፤ የሉም። በዚያ ቤት ውስጥ መኖር ለቤተሰቡ ችግር ስለፈጠረ ቤተሰቦቹ ቤቱን ለአምባዋ ለአቶ ፔክ አከራይተው ወጡ።

በሚያዝያ ወር 1881 ዓ.ም ወደ ማታ ገደማ የአቶ ዳዊት ሚስትና ሁለቱ ልጆቻቸው ላቶ ፔክ ወዳከራዩት ወደ ጥንቱ ቤታቸው መጡ። አቶ ፔክም እነኚህን ሰዎች ጋበቿቸውና ከውጭ ሆነው እየተጫወቱ አቶ ዳዊት የጠፉባቸውን መሬት ሲመለከቱ ዲያሜትሩ አሥራ አምስት ሜትር በሚሆን መሬት ላይ ቢጫ ሣር ሲወጣ አዩ። ወዲያውኑ ተሯሩጠው ዙርያ ክብ ከወጣው ሣር አጠገብ ቆመው ይህን ተአምር ሲመለከቱ ሴትዋ ልጅ ሣራ በድንገት «አባዬ አባይ» ብላ ተጣራች። ከዚያ በድንገት ቱግ ብሎ ከወጣው ሣር ውስጥ ድምፅ ተሰማ። «እርዱኝ! እርዱኝ! እርዱኝና ከዚህ ጭንቅ አውጡኝ!» ብሎ ቢጫው ሣር ጠፋ። ያ ድምፅ የአቶ ዳዊት ድምፅ ነበር።

***

የሴቶች ዕድሜ ከወንዶች ረዘም ይላል ይባላል

***

# መንፈሳውያን ሰዎች

እኚህ ሕንዳዊ ሽማግሌ መንፈሳዊነታቸውን ለማስመስከር ተነሱ። የሕዝብ መመላለሻ በሆነ ቦታ አማኞቻቸውን አስቀምጠው በጀርባቸው ተጋደሙ። ከመሬት አፈር ዘግነው አፈሩን በምራቃቸው ካቦኩ በኋላ ከታችኛው ከንፈራቸው ላይ አስቀመጡት። በሌላው እጃቸው የያዙትን ጥቂት ሰናፍጭ በዚያ ከንፈራቸው ላይ ባደረጉት ጭቃ ላይ ዘሩ። እነኚህም የሰናፍጭ ቅንጣቶች ታችኛው ከንፈራቸው ላይ ባለው ጭቃ በሰብሰው እስኪበቅሉ ድረስ ከዚያች ቦታ ለመነቃነቅ፤ እህል ላለመብላት እና ውሀ ላለመቅመስ ወሰኑ። ይህ ካልሆነም «የማመልከውና በጸሎት የምነዘንዘው አምላክ አያውቀኝም ማለት ነው» ብለው ዛቱ። አራት ቀናት ያለ ምንም ምልክት አለፉ። የቀኑ ሐሩር እና የለሊቱ ቁር በሽማግሌው ላይ ድካም አመጣባቸው። በዚያ ላይ እህልም አልቀመሱም። ያቺ በታችኛው ከንፈራቸው ላይ የዘሩዋት ሰናፍጭ እስክትበቅልና አምላክ አንድ ምልክት እስኪሰጥ ድረስ ቃላቸውን ጠብቀው ቆዩ ከጥቂት ቀናት በኋላ ሰናፍጭ በቀለች። በአጠገባቸው ሆነው የሰናፍጯን አበቃቀል ይቆጣጠሩ የነበሩ ሰዎች የሰናፍጯን መብቀል ካረጋገጡላቸው በኋላ ሽማግሌው ከተኙበት ተነሱ። በሕንድ አገር ያሉ ፋቂሮች ለሚያምኑበት ሃይማኖት በግብር መሠዋትን ይወዳሉ። እጅግ በጣም አውሬ የሆኑ ሰው የሚበሉ አዞዎች ባሉበት ወንዝ ዳር ለብዙ ጊዜ በመቀመጥ በአዞዎቹ ባለመባላታቸው መንፈሳዊነታቸውን ያስመሰክራሉ። አንዳንዶቹ በአንዲት ሥፍራ ተቀምጠው ከዚያች ሥፍራ ሳይዘዋወሩ ሃያ ዓመት ድረስ ይቀመጣሉ። አንዳንዶቹም ከባድ ሸክም ተሸክመው ለብዙ ጊዜያት ተኝተው ይቆያሉ። ለምሳሌ በላሆር የነበረ አንድ ፋቂር ሦስት መቶ ኪሎ ክብደት

ያለውን ሸክም በላዩ ላይ ተሸክሞ በአንዲት ሥፍራ በመተኛት አሥራ ሦስት ዓመታት አሳልፏል ይህ የሸክም ዘመን ያለቀውም በፋቂሩ መሞት ምክንያት ነው። ብዙ ተአምራዊ ነገሮችን ይሠራሉ። ለምሳሌ አሁን እኚህ ሽማግሌ ኃይለኛ መርዝ የሆነውን ኒትሪክ አሲድ የሚባለውን መርዝ በብርጭቆ ሞልተው ሲጠጡ ታዩዋቸዋላችሁ።

ይህን ዓይነቱን ተግባር የሚፈጽሙትም የሂንዱ ሃይማኖት አማኞች ናቸው። የዚህ ሃይማኖት አማኞች ፋቂር ወይም ቅዱስ ለመሆን መቻላቸውን የሚያስመሰክሩት ታላቅ የሆነ ተአምራዊ አስደናቂ ነገሮችን በማድረግ ወይም በዚያ በመፈተን ነው። ስለፋቂሮቹ ታሪክ ብዙ ሐተታ ከማብዛቴ ይልቅ አንዳንድ ፎቶ ግራፎች በሳያችሁ ይሻላልና በሚቀጥሉት ገጾች ተመልከቱዋቸው።

የዚሁ ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ በደቡብ አፍሪካ በፒተርማሪ ትስበርግ የሚኖሩ የሕንድ ሰዎች በዓመት አንድ ጊዜ የሚያከብሩት መንፈሳዊ በዓል አላቸው። በዓሉ የሚውለው የፋሲካ አርብ ወይም ስቅለት ቀን ነው። ይህ በዓል ገና አሥራ አምስት ቀን ሲቀረው ይጀምሩና በእምነታቸው መሠረት ለመፈተን የተዘጋጁ ወጣቶች ንጽሕናቸውን መጠበቅ ይጀምራሉ። ክፉ ቃል አይናገሩም፤ ከሴትም ጋር አይገናኙም። የበዓሉ ቀን ሲደርስ በዓሉ ወደሚከበርበት ቦታ ይሔዱና ከቄሱ ፊት ይቆማሉ። ከዚያም እንደመንጠቆ ሆነው በተዘጋጁ መርፌዎች ላይ ሎሚና ብርቱካን የመሳሰሉት ፍሬዎች የሰዎቹ ገላ በመንጠቆዎቹ እየተቀደደ ከላይ በፎቶ ግራፉ እንደምታዩት እየሆኑ ይሰካሉ። መርፌዎቹ በሚሰኩበት ጊዜ ከሰውየው ገላ ላይ ብዙ ደም እየተንዠረዠረ ቢወርድም ሰውየው አመመኝ ካለኝ ፊቱን ቅጭም ካደረገ በመንፈሳዊነቱ ብቁ አይደለም ተብሎ ለሌላ ጊዜ ይመለሳል።

ሰውየው በመርፌዎቹ አወጋግ ጊዜ ብዙ ሆኖ ከተገኘ ወደሌላው ፈተና ያልፋል። ሌላው ፈተና መሰንበቻውን ብዙ ግንዲላዎች በድንጋይ ላይ እየተከመሩ ሲነዱ ይቆያሉ። ያ ፈተናውን በመርፌዎች ያለፈው ጉብል ከላይ በፎቶ ግራፉ እንደምታዩት በዚያ የጋለ ድንጋይና ፍም ላይ በባዶ እግሩ እየተራመደ ያን የፍም ሜዳ ያልፋል። ከዚያ በኋላ መንፈሳዊነቱ ይመሰክርለታል። ከዚህ በታች ባለው ፎቶ ግራፍ እንደምታዩት ብዙዎቹ ያን መንፈሳዊ ፈተና የሚያልፉት ምላሳቸውን ወደ ውጪ ጎልጉለው ምላሳቸውን ከውጭ ባጌጠ ወስፌ ሰፍተው ነው። አበቃ።

# እጀቢሱ ልብ

ችግር ብላህትን ይፈጥራል፤ ይባላል። ልጁ እጅ የሌለው ሆኖ ተወለደ። እንዲህ ያለው ችግር የደረሰበት ልጅ በእጁ ምትክ በእግሩ መጠቀምን ጀመረ። እግሩን

እንደ እጅ አድርጎ ይሠራበት ጀመር። ይህ በቻይና አገር የተወለደ ልጅ እግሩን እንደ እጁ አድርጎ እንዴት እንደሚሠራበት ፎቶ ግራፉን ይመልከቱ።

# ጣት እንደ ዓይን

በሩሲያ አገር በኡራኤል ከተማ ኒዝኒ ታጊል በተባለች አምባ ሮዛ ኩልሾቭ የተባለች ሴት አንድ የፋብሪካ ውስጥ ሠራተኛ አግብታ ትኖር ነበር። ሮዛ አንዲት ሴት ልጅ አለቻት። ሮዛ ስትወለድ ጀምራ እውር ናት። ግን እንደማንኛውም ዓይናማ ሰው ማየት የምትችል ነበረች።

በምንዋ ታያለች? በጣትዋ ነበር። ሮዛ ማንኛውንም መጽሐፍ ሆነ ጋዜጣ ያለ ምንም ችግር ጣቶችዋን ወደምታነበው ነገር በማስጠጋት ታነበዋለች። የምታነበው ለእውራን የሚጻፈውን ብሬይል ሳይሆን ማንኛውንም ጽሑፍ ነው።

በሞስኩ ከተማ ያለው የሕክምና ሳይንስ አካዳሚ ድርጅት ይህችኒ የ22 ዓመት ልጅ ለመመርመር አቅርቧት ነበር ከመርማሪዎቹ ሊቃውንት አንደኛይቱ ወይዘሮ ቫሌሪያ ትሪስያቲስካያ እንደጻፉት «በራሴ ጥበብ እፈትናታለሁ ብዬ አንድ ፎቶ ግራፍ ከጠረጴዛ ላይ አነሳለሁና እስቲ ይሄን አንብቢው አልኳት፤ እስዋም ጣቶችዋን ወደ ፎቶ ግራፉ አስጠግታ «ይሔ ምን ይነበባል? የአንድ ሰው ፎቶ ግራፍ ነው። ከንፈሩ ላይ ጢም ያለው ስዕል ነው፤ ሰውየውም ሽማግሌ ነው አለችኝ። ሽማግሌ መሆኑን እንዴት አወቅሽ? ብላት የፊቱ ቆዳ ተጨማዶ የለሞይ አለችኝ» በማለት ጽፋለች።

# መንትዮቹ

በ1930 ዓ.ም ነሐሴ 19 ቀን በአሜሪካ አገር በሰሚነ ካሮሊና መንታ ልጆች ተወለዱ። መንታዎቹ ሦስት ነበሩ። ቢሊ የተባለው ልጅ ሳያድግ ሞተ። ሁለቱ ግን አደጉ። አንዷ ቦቢ ስትባል አንዱእ ደግሞ ቤቲ ተባለች።

ቦቢና ቤቲ ተማሪ ቤት ግቡ። በትምህርታቸው እኩል ይማሩ ጀመር። አንዷ ልጅ ጥርሴን አመመኝ ስትል መንትዮዋም እርሷ የታመመችውን ጥርስ ትታመማለች። አንዱእን ራስ ምታት ሲያማት አንደኛዋንም ያማታል። በተወለዱ በአሥራ አንድ ዓመታቸው ቦቢ የእንጥል በሽታ አሟት ስትታከም ቤቲ ደግሞ ወዲያውኑ እንጥልዋ ወርዳ ትሰቃይ ጀመር።

በትምህርታቸው ከከፍተኛ ደረጃ እስኪደርሱ ድረስ አንዷ እንዷን ሳትበልጥ እኩል በትምህርታቸው ገፉበት። እነኚህ እህትማማቶች አድገው በአንድ ኩባንያ ውስጥ ሥራ ያዙ።

አንድ ጊዜ ታመሙ። ሁለቱም ከተለያየ ክፍል ከሆስፒታል ተኙ። ለሁለቱም ተጠባባቂና የሚጠይቋትን ጥያቄ የሚመዘግቡ ነርሶች ተደረጉላቸው። በኋላ ከምዝገባው እንደተገኘው ሁለቱም በተመሳሳይ ጊዜ እያንዳንዳቸው ውሀ ጠማኝ ብለዋል፤ በተለያየ ክፍል ሆነው ያደረጉት የነበረው ድርጊት ሁሉ ተመሳሳይ መሆኑ ተረጋገጠ።

ረቡዕ ማታ ሕመሙ ጸናባቸው። ከምሽቱ 55 ደቂቃ ሲሆን ቦቦ ሞተሽ። ጠባቂዋ ነርስ የቦቢን ሞት ለመንገር ከ8 ቁጥር ክፍል ብቅ ስትል በ12ኛው የክፍል ቁጥር ቤቲን ትጠብቅ የነበረችው ነርስ የቤቲን መሞት ለመንገር ብቅ አለች ሐኪሞቹ የተሰበሰው የሬሳዎቹን ሁኔታ ሲመለከቱ ሁለቱም ልጆች በየአልጋቸው ላይ የሞቱት በአንድ ጎን ተኝተው አንዳንድ እግራቸውን እንደማጠፍ ብለው ነው።

***

# መሬት ትመሰክራለች?

በዌልስ በ1821 ዓ.ም ጆን ኒውተን የተባለ ሰው በሰው ግዳይ ወንጀል ተከሶ ስቅላት ተፈረደበት። ጆን የመሰቀያው ገምድ ካንገቱ ገብቶለት የመጨረሻ ቃሉን እንዲሰጥ ቢጠየቅ «የተፈረደብኝ በትክልል አይደለም፤ እኔ ከወንጀሉ ንጹህ ሰው ነኝ፤ ንጹህነቴንም መሬት ትመሰክራለች፤ የምቀበርበትም መሬት አንድ ትውልድ እስኪያልፍ ድረስ ሣር አያበቅልም» ብሎ ተናገረ።

ጆን ኒውተን በስቅላት ተገደለ። ሬሣውም ተቀበረ። በመቃብሩ ላይ እንኳን ሣር ምናምኒት ለምለም ነገር ሳይበቅል 140 ዓመታት ቆየ። በ1960 ዓ.ም ጥቂት ሣር ታየበት።

***

# የማስታወስ ችሎታ

ብዙዎች የማስታወስ ችሎታ የላቸውም። አንዳንዶች ደግሞ ከፍጡር ሁሉ የተለየ የማስታወስ ችሎታ ያላቸው አሉ። እነዚህንም ለተምሳሊት ያህል እንመለከታቸው።

በፖላንድ አገር በሊቱአኒአን አውራጃ በቪልና ነዋሪ የነበረው ራቢ ኤልያስ አንድ ጊዜ አይነበበውን መጽሐፍ እስከ ዕድሜ ልኩ አይረሳም። ራቢ ሁለት ሺ መጻሕፍት አንብቦ ሁለት ሺውንም መጻሕፍት በቃሉ ያውቃቸው ነበር። እያንዳንዱ አረፍተ ነገር በየትኛው መጽሐፍ ውስጥ እንደምትገኝ የመጽሐፉን ገጽና ፓራግራፉን ጭምር መናገር ይችል ነበር።

ፈረንሳዊው ሊዮን ጋምቤታ አንድ ጊዜ ያነበበውን መጽሐፍ ብዙ ዓመታት ከቆየም በኋላ መጽሐፉን ከዳር እስከ ዳር በቃሉ ይወጣው ነበር። ጋምቤታ መጽሐፉን በቃሉ የሚያነውበው ከመጀመሪያው አንስቶ እስከመጨረሻው፤ ከመጨረሻው ጀምሮ እስከ መቅድሙ ነበር።

ዝነኛው የግሪክ መምህር ሪቻርድ ፓርሰን አንድ ጊዜ ያነበባትን መጽሐፍ ለምንጊዜውም አንዲት ቃል ሳትጎድል ከገጽ እስከ ገጽ በቃሉ ያውቃት ነበር።

የፔርሺያው ንጉሥ ቤተ መጻሕፍት አላፊ የነበረው ማቱሪን ቬይስሬ ማንኛይቱንም የሰማትን ድምፅ ያለምንም ማሳሳት መልሶ ይናገራት ነበር። በማንኛውም ቋንቋ ማንኛውም ሰው ሲናገር ከሰማ የማያውቀውን ቋንቋ ሁሉ የለምንም ስህተት መልሶ ለመናገር በመቻሉ የተደነቀ ሰው ነበር።

# ወፋፍራሞቹ

ከወፋፍራም ሰዎች መሐል አንዱ የሚደነቀ ሮበርት ነው። ሮበርት ኧርል ሁፍስ በ1926 ዓ.ም ሞንቲቼሎ፤ በተባለ ቦታ ተወለደ። ሲወለድ አራት ኪሎ ተክሉ ያህል ይመዝን ነበር። በስድስት ዓመት ዕድሜው 81 ኪሎ ከአምሳ ግራም ክብደት ነበረው። የሮበርት ውፍረት በዚህ አላበቃም። ከአራት ዓመት በኋላ ዕድሜው አሥር ዓመት ሲሆን 151 ኪሎ ከአምሳ ግራም ክብደት ነበረው። አሁንም በዚህ አላበቃም። በአሥራ ሦስት ዓመት ዕድሜው የሮበርት ክብደት 218 ኪሎ ከ100 ግራም ሆነ። በአሥራ ስምንት ዓመት ዕድሜው ክብደቱ 277 ኪሎ ከመቶ አምሳ ግራም ሆነ። አሁንም በዚሁ አላበቃም። ዕድሜው ሃያ አምስት ዓመት ሲሞላ ክብደቱ 358 ኪሎ ከአንድ መቶ ግራም ደረሰ። ከዚህ ክብደቱ ሁለት ዓመት በኋላ ማለት በሃያ ሰባት ዓመት ዕድሜው የአካሉ ክብደት 378 ኪሎ ደፈነ።

በየካቲት ወር 1958 ዓ.ም ተመዝኖ 427 ኪሎ ከ150 ግራም ሆኖ ነበር። ከዚህ ክብደት በላይ አልወጣም። እንዲያውም ወደ ጊዜ ሞቱ አቅራቢያ ሲደርስ ክብደቱ ቀንሶ 416 ኪሎ ከመቶ ግራም ይመዝን ነበር።

ሮበርት ኸርል ሁፍስ በ32 ዓመት ዕድሜው ሞተ ብዬ ታሪኩን ከመደምደሜ በፊት ስለ ሮበርት ጥቂት ላጫውታችሁ። ጭኑ ዙርያ ክቡን በሜትር ሲለካ ሦስት ሜትር ከአሥር ሳንቲ ሜትር ነበር። ደረቱ ደግሞ ዙርያ ክቡን ሲለካ ከጭኑ፤ የላይኛው እጁ ከክንዱ በላይ ያለው ማለት ነው ዙርያውን የላይኛው እጁ ከክንዱ በላይ ያለው ማለት ነው ዙርያውን ሲለካ አንድ ሜትር ከሁለት ሳ. ሜ ነበር። የእግሩ ጉልበት ሎሚው አጠገብ ያለው ሲለካ ዙርያ ክቡ 84 ሳ. ሜ ነው። ሱሪውን ለመስፋት የሚያስፈልገው ጨርቅ ዘጠኝ ያርድ ሲሆን ለሸሚዙ ደግሞ አምስት ያርድ ርዝመት ያለው ጨርቅ ያስፈልገዋል።

ሮበርት ትምህርቱን ያቋረጠው 6ኛ ክፍል ሲደርስ ነው። ያቋረጠበትም ምክንያት በእግሩ ርቆ መሔድ ስላልቻለ፤ ነው። ብዙውን ጊዜውን የሚያሳልፈው በመቀመጥ ነበር። የሚቀመጠው በወንበር ሳይሆን በግሉ ከብረትና ሲሚንቶ በተሠራለት የድንጋይ ብርጩማ ላይ ነው። እዚያም ላይ ተጎልቶ፤ መጽሔቶችን ሲያገላብጥና ሲያነብ ይውል ነበር። ማታ እንቅልፍ ሲይዘውና ለመተኛት ሲፈልግ እንደማንኛውም ሰው የተፈጠሩት ሁለቱ ወንድሞቹ እያንዳንድ እግሩን እየተሸከሙ ከአልጋው ላይ ያወጡለትና ከዚያ እብኋላ ይፈነደሳል።

ሮበርት ቀልደኛና ተጨዋች ስለ ነበረ በሚያውቁት ሰዎች ዘንድ ሁሉ በጣም የተወደደ ነበር። ምንም ተወዳጅና ወፍራም ቢሆኑ ሞት አይቀርምና ሮበርት በ1958 ዓ.ም ሐምሌ 10 ቀን በተወለደ በ32 ዓመቱ በኢንዲያና ውስጥ ብሬሜን በተባለ አገር ሞቶ ቤንቪል በሚባል የመቀበሪያ ቦታ ተቀበረ።

እንዴት እንደ ተቀበረ ደግሞ ጥቂት ልንገራችሁ የመቃብር ሳጥኑ ፒያኖ ያህል ነበር። ሁለት ሜትር ከ13 ሳ. ሜ በ71 ሳ. ሜ የሆነ ስፋትና ቁመት ነበረውም። ያ ትልቅ ሬሳ በዚያ ትልቅ ሳጥን ውስጥ ገብቶ ከተቆለፈ በኋላ ጠቅላላ ክብደቱ 440 ኪሎ ክብደት አመጣ። ከዚያ በኋላ ማንም ሊያንቀሳቅሰው ስላልቻለ የከባድ ዕቃ ማንሻ ክሬን መጥቶ የሬሳውን ሳጥን ሊሳ ቻለ።

የሮበርት ክብደት 600 ኪሎ ደርሶ ነበር ብለው የጻፉ አሉ። ብዙዎች ሊቃውንት ባወጡት መግለጫና ደራሲዎችም በጻፉት መጻሕፍቶቻቸው እንደገለጹት 428 ኪሎ አልሞላም ነበር። እኔም ራሴ ካነበብኳቸው የሮበርት ታሪክ መጽሐፎች ውስጥ ከአብዛኛዎቹ በእኩልነት ያገኘሁት ክብደቱን በዚህ ቦታ አግብቼዋለሁ።

ሌላው በአሜሪካ አገር የታወቀው ወፍራም ሰው ጆን አሌ ነው። ጆን በ1853 ዓ.ም በሰሜን ካሮሊና የዚያን ጊዜ ካርቦን አሁን ግን ካርቦርተን በተባለው ከተማ ተወለደ። ስለ ጆን የተጻፈ ሰፊ ታሪክ የለም። ጆን 452 ኪሎ ከ200 ግራም ክብደት ነበረው። አንድ ቀን በብዙ ግንዲላዎች እንደ ፎቅ ተደርጎ ከተሠራለት ቤቱ በራፍ አጠገብ ቆም ሲል ወለሉ ተደርምሶ ጆን ሰጠመ። ሙሉ በሙሉ ወርዶ ከሥሩ ያለውን

መሬት ሳይነካ ትከሻዎቹ በግንዲላዎቹ ተይዘው ስለቀሩ ጀን በድንጋጤ በላብ ሰጠመ። ጎረቤቶቹ ተሰብስበው ለማውጣት ሲጎትቱት በዚያው ትንፋሹ አቆመና በተወለደ በ34 ዓመቱ በ1887 ዓ.ም ከዚች ዓለም በሞት ተለየ።

በ1948 ዓ.ም የተወለዱ ቢል እና ቤን ማክሬይ የተባሉ መንትያ ወንድማማቾች በሰሜን ካሮሊና ውስጥ ሔንደርሰን በተባለ መንደር በግብርና ይኖሩ ነበር። በመጋቢት ወር 1970 ዓ.ም ተመዝነው አንዱ 264 ኪሎ ሲመዝን ወንድምየው 256 ኪሎ መዝኗል። እነሱም በፎቶግራፉ የምታዩዋቸው ናቸው። የሌሎቹን ፎቶ ግራፎች ደግሞ እዩ።

እንግሊዛዊ ጄምስ ቻዝ የሚለው «አሁን የምታዩኝ ቀጥኜ ሸንቃጣ ሆኜ ነው፤ አሁን በመካከለኛ ቀበቶ ሱሪዬን ታጥቄዋለሁ። የድሮውማ ቀበቶዬ ይሄ ነበር። ልዩነቱን ታያላችሁ»

***

እነዚህ በአሜሪካ አገር ከሥፍራ ወደ ሥፍራ እየተዘዋወሩ የሚዘፍኑና ጨዋታ የሚያሳዩ ናቸው። መጠሪያቸው ቶንስ ኦፍ ፈን ይባላል።

እኒህ አዛውንት ደግሞ በብዙ ጭንቅ ከሚገቡባት መኪና ውስጥ የሚወጡትም በብዙ ጭንቅ ነው።

አቶ ጆርጅ እንደማንኛውም ሰው በሕዝብ ስልክ መነጋገር ይፈልጋሉ። ግን እንደማንኛውም ሰው ለስልክ መነጋገሪያ እንዲሆን ከተሠራው ሳጥን ውስጥ ገብተው መነጋገር አይችሉም ምክንያቱም ፎቶ ግራፏቸውን የሚያይ ሰው ሁሉ እንደሚያቀው ሆዳቸው ከስልኩ መነጋገሪያ ሳጥን ውስጥ ስለማያስገባቸው ነው።

ልጆች አቶ ጆርጅ ቤት እየሄዱ መጫወት ይወዳሉ። ምክንያቱ አንዱ የአቶ ጆርጅ ሱሪ ሁለት ልጆችን ከትቶ ስለሚያጫውት ነው።

አንድ ጊዜ አቶ ራፋኤል አፖዳካ ታመሙና አሪዞና ሆስፒታል ሄዱ። ሐኪሞቹ አቶ ራፋኤልን ከመረመሩ በኋላ በዚያው ሆስፒታል እንዲተኙ አዘዙ። ትልቁ ችግር የሚተኙበትን አልጋ ማግኘቱ ነበር። በመጨረሻው ሁለት አልጋዎች በአንድነት ተጋጥጥመው ተበየዱና በዚያ ላይ እንዲተኙ ተደረገ።

ለአንዲት ሱሪ የሚሆናቸውን ጨርቅ ብትኑን ከልብስ ሰፊው ጋር ይዘው ይደነቃሉ።

ሌላው ወፍራም ደግሞ አቶ አልቤርቶ ኩምባ ነው። አቶ አልቤርቶ ኩምባ ባለው ውፍረት ምክንያት ለሞዛምቢክ ሐኪሞች ችግር ፈጥሮ እንደተአምር የሚታይ

ነበር። ሐኪሞቹ ወገቡን ለመያዝ ወይም አካሉን ጫንጫን እያሉ ለመመርመር ያስቸግራቸው ነበር።

አቶ አልቤርቶ ሲመዘን ሁለት መቶ አምሳ ሁለት ኪሎ ክብደት አለው። አቶ አልቤርቶ ይህን ክብደቱን ይዞ የሚቀመጥበት ወንበር ስለማያገኝ የሚቀመጥበትን ወንበር የሠራው እሱው ራሱ ነው። አቶ አልቤርቶ የስድስት ልጆች አባት ነው። እንደማንኛውም ሰው ቆሞ ማንኛውንም ሥራ ለመሥራት የሚችል ሰው አይደለም። ማንኛውንም የሚሠራውን ነገር የሚሠራው ተቀምጦ ነው ተቀምጦ የሚሠራው ነገር ደግሞ እንደ ፍላጎቱ ስለማይሟላለት አቶ አልቤርቶ ሁልጊዜ ይበሳጭ ነበር። ይቺ መጽሐፍ እስከታተመችበት ጊዜ ድረስ አቶ አልቤርቶ በሞዛምቢክ ውስጥ በሕይወት ይኖር ነበር።

# እንስሳት ምን ያውቃሉ?

በጆሃንስበርግ ከተማ አንዲት ሴት ከቤታቸው ተኝተው ለሊት ውሻቸው እየጮኸ ከመኝታ ቤታቸው ገብቶ ሴትዮዋ ለብሰው የተኙትን ልብስ በመጎተት አስነሳቸው። ሴትዮዋ ከቤታቸው ሌባ የገባ መስሎአቸው ደንግጠው ቢነሱ ውሻው እየጮኸ ቀድሞአቸው ይመራ ጀመር። ወይዘሮዋ ተከትለውት ከሳሎን ሲገቡ ከመሬት ከወደቀ ከጌታው ፎቶ ግራፍ ላይ ውሻው ያንቃርር ጀመር። የፎቶ ግራፉ ማቀፊያ መስተዋት ተሰባብሯል። ፎቶ ግራፉ ተቦጫጭሯል። የቤቱ ባለቤት ባለፎቶ ግራፉ ሰው ከጆሃንስበርግ 250 ማይል ርቆ ከሚገኘው ቦታ ለሥራ ጉዳይ ሔደዋል። ሴትዮዋ ለሥራ ጉዳይ ከቤት በወጡት ባላቸው ፎቶ ግራፍ አጠገብ ሆነው ሲተክዙና ፎቶ ግራፉ የተሰበረበትን ምክንያት ሲያጣሩ ስልክ ተደወለላቸው። ስልኩ የተደወለው ከጆሃንስበርግ ፖሊሶች ነበር። ሴትዮዋ ስልኩን አንስተው ሀሎ ቢሉ «እናዝናለን እሜትዬ! ባለቤትዎ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት በመኪና አደጋ ሞቱ» አሏቸው።

በጀርመን አገር ደግሞ ዱልሶልዶርፍ በተባለ አምባ በ1964 ዓ.ም አቶ ጳውሎስ ኬኡን የተባለ ሰው ለድመቱ ምግብ ለመስጠት ወደ ወጥ ቤት ገባ። ድመቲቱ እየጮኸች ጌታዋን ተከትላ ከወጥ ቤቱ ገባችና ልብሱን በጥፍርዋ ይዛ ወደ ውጭ ትጎትተው ጀመር። ቡጥጫውና ጉተታው ቢበዛበት አቶ ጳውሎስ ድመትዋን ተከትሎ ከወጥ ቤቱ ወጣ። ልክ እሱ እንደወጣ የወጣ የወጥ ቤቱ ጣሪያ ፈርሶ ከጣሪያው ላይ የነበረው ትልቅ ብረት አቶ ጳውሎስ ቆሞ ከነበረበት ከአቶ ላይ አረፈ። የጀርመን ፖሊሶች እንደገለጹት ያ ብረት ከአቶ ጳውሎስ ላይ አርፎ ቢሆን ኖሮ አጥንቱ በወረንጦ እየተለቀመ ይነሳ ነበር።

በ1955 ዓ.ም ጀይታ የተባሉ ሰው ከሳሞአ ግዛት ከአፒያ በጀልባ ተሳፍረው ማይና ወደተባለው ሃያ ማይል ወደምትርቅ አገር ከድመታቸው ጋር ለመሔድ ተነሱ። ከጀልባው አጠገብ ሲደርሱ ድመቱ ከጌታው እጅ አምልጦ ሸሸ። ጌትየው ድመቱን ትተው በጀልባው ተሳፍረው ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ጀልባይቱ ዕለቱኑ መጥፋትዋ ተነገረ። በተደረገው ፍለጋ ከሁለት ወር በኋላ ጀልባይቱ ተሰባብራ አንድ ሕይወት ያለው ፍጡር ሳይገኝበት ስብርባሪዋ ብቻ ከፊጂ በስተሰሜን በኩል ተገኘ።

በቤልጂግ አገር በአንድ ፋብሪካ ውስጥ የሚሠራ ሰው ሁልጊዜ ወደ ሥራው ሲሄድ ውሻውን እያስከተለ ነበር። አንድ ቀን በ1963 ዓ.ም እንደተለመደው ጌትዮው ከውሻው ጋር ወደ ፋብሪካ ሥራው ሔደ። ውሻው ከፋብሪካው ዋና በር ሲደርስ እንደ ወትሮው ወደ ውስጥ መግባቱን ትቶ ከዋናው በር ላይ ከጌታው ፊት ተቀመጠ። ጌትዮው ቸኩሎ ነበርና አላስገባ ያለውን ውሻ እንደምንም አልፎ ከሥራው ገባ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሰውየው በስልክ ተፈለገ። የደወለችለት ሚስቱ «ውሻው ከቤት መጥቶ ከአልጋ ሥር ተኝቶ በጭንቀት ይጮሃልና ሐኪም ይዘህ ቶሎ ድረስ» አለችው። ሰውየው ከሥራው ወጥቶ ወደ ቤቱ ስሄድ ከቤት ለመድረስ ግማሽ መንገድ ሲቀረው ይሠራበት የነበረው ፋብሪካ ተቃጠለ። ከሠራተኞቹም ብዙዎቹ በቃጠሎው ሞቱ።

አቶ ዊልያም ፍራንክላንድ የተባሉ ሰው በ1966 ዓ.ም በሰኔ ወር ሚስታቸውንና ሁለት ሴቶች ልጆቻቸውን ይዘው ከሚኖሩበት ከኬንት ከተማ ወደ ለንደን ለሽርሽር ለመሄድ ቤተሰቦቻቸውን በመኪና ጭነው ወደ አይሮፕላን ጣቢያ ሊሄዱ ተነሱ። ከአቶ ዊልያም ሚስት እናት ጋር ከቤት እንዲቀር የተደረገው ውሻ ገና ዕቃው ሲቀረቀብ ጀምሮ እየጮኸ ዕቃውን እንዳያዘጋጁ ሲያስቸግር ነበር። በመጨረሻው ቤተሰቦቹ ከመኪና ውስጥ ገብተው ሊሄዱ ሲሉ ውሻው ከመኪናዋ ፊት ከመንገዱ ዳር ሆኖ ያላዝን ጀመር። መኪናዋን እንደምንም ለማሳለፍ ሞክረው ሊሄዱ ሲሉ ውሻው ዘሎ ከመኪናው ውስጥ ያለችውን የአንደኛዋን ሴት ልጅ እጅ ነከሰ፡ ንክሻው ከባድ አልነበረም። ቢሆንም ልጅቷ መታከም ስላለባት ለሕክምና በወሰድዋት ጊዜ ሊሄዱበት የነበረው አይሮፕላን አመለጣቸው። ከዚያ በኋላ ወደ ቤት ተመልሰው ዕቃቸውን ሲያራግፉ ውሻው ከጩኸቱ ዝም አለ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ አቶ ዊልያም ሊሄዱበት የነበረውና ያመለጣቸው አይሮፕላን ከሊስቦን ከተማ ውጪ ከተራራ ጋር መጋጨቱ ተነገረ። በውስጡም ከነበሩት ተሳፋሪዎች አንድም በሕይወት የተረፈ የለም።

***

# አሮጊቷ

በእንግሊ አገር በደቡባዊ ምዕራብ ክፍለ አገር ከሰሜረስት አምባ አልፎ ሚንዲፕ በተባለ አምባ ተራራ ላይ ይኖሩ የነበሩ አቶ ቤርናንድ ኩሊንስ የሚከተለውን ጽፈዋል።

«በ1980 ዓ.ም በጥቅምት ወር ከቤቴ ቁጭ ብዬ በመስኮት ከውጭ የሚዘንበውን ዝናብ ስመለከት አንዲት አሮጊት በቤቴ አጠገብ እየተንቀረፈፉ ሲያልፍ አየሁ። የዘጠኝ ዓመት ልጄን ትሬቨር የተባለውን ልኬ አሮጊቷን ከዝናቡ ውስጥ ወደ ቤት እንዲገቡ አደረግሁ። አሮጊቷ ከቤት እንደ ገቡ ከምድጃው አጠገብ አስቀምጠናቸው እሳት እንዲሞቁና ልብሳቸውን እንዲያደርቁ አደርግናቸው። ምግብም ሰጠናቸው፤ ሻይም እንዲጠጡ አደረግን።

«አሮጊቷ ከምድጃው አጠገብ እንደ ተቀመጡ የሚያሳዝነውን የሕይወት ታሪካቸውን ይነግሩ ጀመር። ሥራ ነበረኝ ከሥራዬም ቦታ አረጀሽ ብለው አባረሩኝ። ከወንድ ልጄና ከሚስቱ ጋር እኖራለሁ። እነሱም ምንም የሌላቸው መናጢ ድሆች ናቸው። ስለዚህ እንደዚህ እንደዞኩ እውላለሁ አሉን።

«በዕለቱ ይጥል የነበረው ዝናብ ከባድ በመሆኑ አሮጊቷን ከቤታቸው አሳድረን በነጋታው ከልጃቸው ቤት ድረስ፤ በጋሪ ይዤአቸው ሔድሁ።

«ይህ በሆነ በዓመቱ ለገበያ ወደ ከተማ በጋሪ ሔድሁ ከዚያም ስሸቃቅል ቆይቼ ሚስቴ እንዳትሰጋ በጊዜ ወደ ቤቴ ለመመለስ ጋሪዬን ጫንኩ። ከከተማው እንደወጣሁ ኃይለኛ ዝናብ መጣል ጀመረ። መብረቅና ነጐድጓዱም ከመጠን በላይ በመሆኑ በጣም ፈርቼ ነበር። ሆኖም ሚስቴ እንዳትሰጋ በአቋራጩ መንገድ ፈጥቼ ለመድረስ በማለት ዋናውን መንገድ ትቼ በአቋራጭ ተጓዝሁ።

«በአቋራጩ መንገድ ጥቂት እንደ ተጓዝሁ እኒያን ከዝናብ አስጠለልናቸው የነበሩትን አሮጊት በዚያ ዝናብ መሐል ከቁጥቋጦው ውስጥ ቆመው አየኋቸው። ወዲያው ጋሪዬን አቁሜ ኑ ጥቂት ልሸኝዎት ብያቸው ከጋሪው ላይ ወጥተው ከአጠገቤ ተቀመጡ።

«መንገድ እንደ ጀመርን ከዚያ ቁጥቋጦ ውስጥ ቆመው ምን ያደርጉ ነበር? ብላቸው ወደ ከተማ መሔድህን ስለማውቅ ከከተማ እስትመለስ ድረስ አንተኑ እጠብቅህ ነበር አሉኝ። ይህን እየተነጋገርን ስንጓዝ ከዋናው መንገድ ገባን። ዋናውን መንገድ አልፌ በአቋራጩ መንገድ ልሔድ ስል አሮጊቷ አይሆንም ልጄ፤ በዚሁ በዋናው መንገድ ሂድ፤ አሉኝ ቸኩያለሁ፤ እቤትም ቶሎ ለመድረስ እፈልጋለሁና በዚሁ በአቋራጩ ነው የምሄደው ብላቸው ጋሪውን የሚጎትቱን ፈረሶቹን የልጓም ጠፍር

ጨበጥ አድርገው ግድ የለህም ልጄ፤ ለኔ ስትል በዚህ በረጅሙ በዋናው ጎዳና ሂድ አሉኝ።

«እኔም የአሮጊቷን ፈቃድ ለመሙላት ብዬ አቋራጩን መንገድ ትቼ በሩቅ በዋናው ጎዳና ጋሪዬን እነዳ ጀመር። ከቤቴ አጠገብ ስደርስ አሮጊቷ እንደ እንቅልፍ ቢጤ ሸለብ አድርጓቸው አየሁ። ብዙ ዝናብ መትቶን ስለነበረ፤ አሮጊቷ ከጋሪው ለመውረድ ከተቀመጡበት ቢነሱ ብርዱ ይብስባቸዋል ብዬ አሮጊቷ ለብሰው የሚወርዱትን ልብስ ላመጣ ወደ ቤት ገባሁ።

«ለሚስቴ፤ ለአሮጊቷ የሚሆን ልብስ ስጪኝ አልኳት። የቷ አሮጊት አለችኝ። ከዓመት በፊት ከቤታችን አድረው የነበሩት ከኔ ጋር መጥተው ከጋሪው ላይ ተቀምጠዋልና ለብሰው ከጋሪው ላይ የሚወርዱበትን ልብስ ነው የምፈልገው አልኳት።

«ሚስቴ ደነገጠች። ምን እንዳስደነገጣት ብጠይቃት፤ የአሮጊቷ ልጅ ሚስት አሁን ከዚህ መጥታ ልክ አንተ ልትመጣ አቅራቢያ ነው የሔደችው። እስዋም የኀዘን ልብስ ለብሳ ነበርና ምን ሆንሽ? ብላት የባለቤቴ እናት እኒያ አሮጊት የዛሬ አስራ አምስት ቀን ሞተው ነው ብላኛለችና አንተ እንዴት አሮጊቷን ይዤአቸው መጣሁ ትላለህ? አለችኝ።

«ሚስቴ ስለተጠራጠረችኝ አሮጊቷን ላሳያት ከቤት ይዣት ወጣሁና እኛውልሽ ጋሪው ላይ ብዬ ላሳያት ጋሪው ባዶውን ቆሞ አየሁት። በሰው ድጋፍ ከጋሪ ላይ የሚወጡትና የሚወርዱት አሮጊት እምጥ ይግቡ ስምጥ ከየት እንደገቡ አጣኋቸው።

«ያ ወደ ቤቴ ስመለስ ልሄድበት የነበረው አቋራጭ መንገድ ያንድ ወንዝ ድልድይ ፈርሶ የወንዙ ውሃ ብዙ ጉዳት ማድረሱን ሰማን። ለካስ አሮጊቷ ከመንገድ የጠበቁኝ በዚያ አደጋ በደረሰበት ሥፍራ እንዳልሄድ ኖርዋል። ምናልባትም ከነጋሪዬ በውሀው ተወስጄ እቀር ነበር።»

***

# ልጅቷ

የደቡብ አፍሪካን ሳይንቲስቶ ሲያስቸግር የምየው የጆይ ሐርቬይ የማስታወስ ጉዳይ ነበር። ጆይ 12 ዓመት ዕድሜ ያላት ተማሪ ነች። ጆይ የምትናገረው ነገር ሁሉ ሕዝቡ በታሪክ ተጽፎ ያነበበውን ከመቶ ዓመታት በፊት ግድም የሆነውን ጉዳይ ነው።

ጆይ አንድ ቀን የሰማንያ ዓመት አሮጊት አይታ «ይቺ ሴትዮ እኮ የእኔ ልጅ ነች» አለች። የአሥራ ሁለት ዓመትዋ ልጅ እንዲህ የመሳሰለውን ጥንታዊ ነገር ነበርኩበት እያለች ስለምታወራ ወላጆችዋ ወደ ሐኪም ቤት ወስዱዋት ሐኪሞቹም እንዲያማክሩዋቸው ጠየቁ።

የዊት ወተር ሳንድ ዩኒቨርሲቲ የሳይንስ ሊቃውንት በዶክተር አርዘር ብላክስሌይ ሰብሳቢነት ተሰብስበው የጆይን ሁኔታ ማጥናት ጀመሩ።

ዶክተር ብላክስሌይ «እንዴት እንዲህ ሆንሽ?» አሏት። «......አንድ በጣም ትልቅ የሆነ አውሬ ያባርረኝ ጀመር አውሬው ሊበላኝ ፈልጎ ነበርና በታም ሮጠሁ። ግን ደረሰብኝና በእግሩ ደፍጥጦ ገደለኝ» አለች። «አውሬው እንዴት ያለ ነው?» ቢሏት «ትልቅ ነው፤ ቤት ያህላል፤ አሁን እንኳ በተማሪ ቤት አንዳንድ ልጆች መጽሐፍ ላይ ስዕሉን አየዋለሁ። እኔም አውሬውን መሳል እችላለሁና ቆይ ስዬ ላሳያችሁ» ብላ የአውሬውን ስዕል በወረቀት ላይ ሳለችው። ሊቃውንቶቹ ስዕሉን ቢያዩት ዛሬ ከምድረ ገጽ የጠፋው ዲኖሳኡርስ የተባለው አውሬ ሆነ።

ይቺ የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ፤ ናት የምትላትን የሰማንያ ዓመት አሮጊት ሴት አቅርበው ጆይን «.....አንቺ የሰማንያ ዓመት አሮጊት ወለድኳት ትያለሽ?» አሏት። ጆይ ተከዝ አለችና «ጉዳዩ ረጅም ነው። እኔ እሷን የወለድኳት በአይርላንድ ውስጥ ኬልኪል በተባለ ቀበሌ ነው። በተወለደች ማግስት አባትዋ አሣ ሊያጠምድ በጀልባው ሂዶ ማዕበል በመነሳቱ ሰጥሞ ሞተ። ከዚያም ጥቂት ወራት እንደቆየች ወደ ለንደን ሂዳ አደገችና በመጨረሻው አንድ መምህር አገባች......» ብላ ስትናገር አሮጊቷ አደንግጠው «በቃኝ፤ ነገሩ ሁሉ ልክ ነው» እያሉ ጮሁ።

# ድንክዬዎች

የዛሬውን ተማሪ እንጃ እንጂ በኛ ተማሪነት ጊዜ ቶም ተምብ የሚባል አጭር ሰው እንደ ነበረ እንደተረትም እንደእውነትም እያደረጉ ይነግሩን ነበር። አውራ ጣቱ የሚል ቅጥል ያገኘው ቶም ወላጆቹ ያወጡለት እውነተኛ ስሙ ቻርልስ ስትራተን ነው። እውነተኛ ስሙን እንተወውና በዓለም ላይ በታወቀበት በሌላ ስሙ ቶም እያልኩ ላውራላችሁና ቶም በእርግጥ አጭር ሰው ነበር።

ቶም፤ ብሪጅፖርት በተባለ ሥፍራ በ1832 ዓ.ም ጥር 11 ቀን ተወለደ። በተወለደ በአምስት ወር ዕድሜው ማደጉን አቆመ። በዚያን ጊዜ ቁመቱ 53 ሳ. ሜ ነበር። በዚያው ርዝማኔው ቀረ። ቶም ይህንን ቁመቱን ለማሳየት በብዙ አገሮች እየተዘዋወረ ብዙ ገንዘብ አግኝቷል። በተለይ በእንግሊዝ አገር ብዙ ጊዜ ሠርቷል። በመሐከለኛው ጊዜ በረጅም ታሪኮች ሰው ታሪኮች ውስጥ ካነበባችሁት ከአንጉስ ጋር

ተሻርከው ቶም ከአንጉስ መዳፍ ላይ ይቆምና ጭፈራ በማሳየት፤ ብዙ ገቢ ገንዘእብ አግኝተዋል። ቶም አንዲት በቁመት የምትመሳሰለውን ወይዘሮ ላቪኒያ ዋረን የተባለችውን ሴት አግብቶ በሰላም ይኖር ነበር። በኋላም የአሜሪካ ፕሬዝዳንት የነበሩት ፕሬዝዳንት ሊንከንና ባለቤታቸው በዋይት ኃውስ ቤተ መንግሥት ውስጥ በታላቅ ደስታ ያኖሩዋቸው ነበር። ቶም ሐምሌ 15 ቀን 1883 ዓ.ም ሞተ።

ሌላው አጭር ሰው ሮበርት ስኪነር የተባለው ነበር። በ1742 ዓ.ም በእንግሊዝ አገር በለንደን ከተማ ቢጤውን አግብቶ ነበር። ባገባበት ጊዜ የጋብቻውን ሥርዓት የሚያካሂዱት ቄስ እንደ ቆሙ ቁልቁል መውረድ አቅቷቸው መሬት ላይ ተቀመጡ የጋብቻን ስርዓት አስፈጸምሙ። የሮበርትና የሚስቱ ቁመት 76 ሳ.ሜ ነበር። አጃቢና ሚዜ የሆኑዋቸው በቁመታቸው ተመሳሳይ የሆኑ ሕጻናት ነበሩ። እነዚህ ባልና ሚስት ልጆች ወልደው ነበር። ልጆቹ እንደወላጆቻቸው ድንክዬዎች አልነበሩም። እንደማንኛውም ሰው ነበሩ። በየተወልዱ በየአራት ዓመት ቁመታቸው ከወላጆቻቸው እኩል ይሆን ነበር ።

ሌላው አጭር ሰው ደግሞ ጂኦፍሪ ሁድሰን ይባላል። ጂኦፍሪ የስምንት ዓመት ልጅ በነበረ ጊዜ ቁመቱ ከ35 ሳ. ሜ ያነሰ ነበር። ጂኦፍሪ እንዲህ ያለ ፍጡር በመሆኑ ለእንግሊዙ ንጉሥ ለቀዳማዊ ቻርልስ እንደ ስጦታ ተደርጎ ተሰተ። ጆኦፍሪ የስልሳ ዓመት ጐልማሳ በሆነ ጊዜ ቁመቱ 46 ሳ. ሜ ነበር።

እቴጌይቱ ጂኦፍሪን በጣም ይወዱት ነበርና ሚስት እንዲያገባ ወደ ፈረንሳይ አገር ላኩት። በፈረንሳይ አገር በነበረበት ጊዜ አንድ በአገሩ የተከበሩ ታላቅ ሰው አጫጭሮችን የሚንቁና የሚያዋርዱ ነበሩና ጆኦፍሪን ሰድበው አዋረዱት። ጆኦፍሪም ተናደው እኒያን ታላቅ ሰው ሽቅብ እያየ «......እኔ መሳደብ አላውቅም፤ ጎበዝ ከሆኑ ተኩስ (ዱ) እንጋጠም......» አላቸው። እኒያም እሺ ብለው ከመታኮሻ ቦታ እንዲሄዱ ጆኦፍሪ አነጣጥሮ በአንድ ተኩስ ጣላቸው።

ጆኦፍሪ ሌላም ሥራ ሠርቷል። ረጃጅሞች አጫጭሮችን መናቅና ማዋረድ ይወዳሉና አንድ ጊዜ በእንግሊዝ አገር እንዳለ አንድ በግዙፍነቱና በታጋይነቱ የታወቀ ሰው በአገሩም የተፈራና የተከበረ የቱርክ ሰው ጂኦፍሪን «ምሳዬን ሰርቀህ በልተህብኛልና ሌባ ነህ» ብሎ ሰደበው። በዚህምጠብ ተፈጠረ። ያ ግዙፍ ሰው እንደ ወፍ የቀለለውን ጆኦፍሪን በአንድ እጁ ከመሬት አንስቶ ከራሱ በላይ አወጣው እንደገና ወደ መሬት ሊመልሰው ሲል ጆኦፍሪ ከዚያ ግዙፍ አንገት አረደው። ግዙፉ ቱርካዊም ወዲያው ሞተ፡

ሌላው አጭር የፖላንዱ ተወላጅ አቶ ጆሴፍ ቦሩውላስኪ ነበሩ። አቶ ጆሴፍ በኅዳር ወር 1739 ዓ.ም ተወለደ። ሲወለድ ርዝመቱ ሃያ ሳንቲ ሜትር ነበር። ዕድሜው አንድ ዓመት ሲሞላው ቁመቱም እንደ ገና 36 ሳንቲ ሜትር ሆነ። እንዲህ መዘርዘሩን

ልተውና በሃያ አምስት ዓመት ዕድሜው የቁመቱ ዝርማኔ 99 ሳንቲ ሜትር ደረሰ። ከዚያ በኋላ ማደጉን አቆመ አቶ ጆሴፍ እንደሌላዎቹ ድንክዬዎች ቶሎ አልሞተም። ዕድሜ ጠግቦ በተወለደ 97 ዓመቱ በ1837 ዓ.ም መስከረም 5 ቀን በእንግሊዝ አገር በዱርሃም ሞተ።

ይቺ በፎቶ ግራፉ የምታዩዋት በ1863 ዓ.ም በሜክሲኮ የተወለደችው ዙቺያ ዛራቴ፤ የተባለችው ሴት ልጅ ከሴቶች የታወቀች አጭርና ቀላል ነበረች ስትወለድ ክብደቷ አንድ ኪሎ ብቻ ነበር ሃያኛ ዓመት ዕድሜዋን ስታከብር 67 ሳንቲ ሜትር ሲሆን ክብደቷ ደግሞ አምስት ኪሎ ከአምሳ ግራም ነበር። ዙቺያ በሃያ ስድስት ዓመት ዕድሜዋ በ1889 ዓመተ ምህረት ሞተች።

ኢጣሊያዊቷ ልጃገረድ ካሮሊና ክራንቻሚ የተባለችው ሲሲሊ ውስጥ ፓሌርሞ በተባለ ሥፍራ በ1815 ዓ.ም ተወልዳ በዘጠኝ ዓመት ዕድሜዋ በለንደን ከተማ በ1824 ዓ.ም ስትሞት የነበራት ቁመት አምሳ አንድ ሳንቲ ሜትር ነበር። እይዚች ልጅ አጽም አሁን በለንደን ከተማ ሮያል ኮሌጅ ኦፍ ሰርጂን በተባለው ትምህርት ቤት ውስጥ ተቀምጧል። አሁን አጽምዋ ሲለካ ያለው ርዝማኔ 49 ሳንቲ ሜትር ነው።

በማሳቹሴትስ ውስጥ ብሪጅወተር በተባለው ቀበሌ ጥር 14 ቀን 1971 ዓ.ም ካልቪን ፊሊፕስ የተባለ ልጅ ተወልዶ ነበር። ሲወለድ የነበረው ክብደት አንድ ኪሎ የማይሞላ ነበር። በተወለደ በአምስት ዓመት ዕድሜው ማደጉን አቆመ። 19 ዓመት በሆነው ጊዜ የቁመቱ ርዝማኔ 67 ሳንቲ ሜትር ነበር። በዚህ ቁመቱ ከነልብሱ በሚዛን ተመዝኖ ጠቅላላ ክብደቱ አራት ኪሎ ከስምንት ግራም ሆንዋል። ካልቪን ፊልፕስ፤ በሚያዝያ ወር 1812 ዓ.ም ሞተ።

ዊልያም ኢ. ጃክሰን የተባለ የኒውዚላንድ ሰውም እንዲሁ አጭር ነበር። ዊልያም ጥቅምት 2 ቀን 1864 ዓ.ም ዱነዲን በተባለ ቦታ ተወለደ። ሲወለድ ሃያ ሦስት ሳንቲ ሜትር ዝርመት ነበረው። በኅዳር ወር 1880 ዓ.ም የነበረው ቁመት ተለክቶ 53 ሳንቲ ሜትር ሲሆን ክብደቱ ደግሞ ሦስት ኪሎ፤ ከ150 ግራም ነበር። ዊልያም ታኅሣሥ 9 ቀን 1900 ዓ.ም በኒውዮርክ ከተማ ሲሞት የነበረው የቁመት ርዝማኔ 69 ሳንቲ ሜትር ነበር።

በፎቶግራፉ ላይ በስተግራ ከጠረጴዛው ላይ ቆማ የምታዩዋት አሻንጉሊት አትምሰላችሁ። ሰው ነች። ፓውሊን (አንዳንዴ ልዕልት ፓውሊኒ ይሏታል) የደች ተወላጅ ነች። በ1876 ዓ.ም የካቲት 6 ቀን አሴንደርች በተባለ ቦታ ተወለደች። ስትወለድ የነበራት ርዝማኔ 30 ሳንቲ ሜትር ነበር። በአራት ዓመት ዕድሜዋ የነበራት ቁመት 38 ሳንቲ ሜትር ነበር። በዘጠኝ ዓመት ዕድሜዋ የነበራት ቁመት 54 ሳንቲ ሜትር ሲደርስ ክብደቷ ደግሞ አንድ ኪሎ ከሩብ ያህል ነበር። በ1895 ዓ.ም መጋቢት አንድ ቀን በያዛት የብርድ በሽታ (ኒሞኒያ) ሰበብ በኒውዮርክ ከተማ በተወለደች፤ በ19

ዓመቷ ሞተች። በሞተች ጊዜ የነበራት ቁመት 58 ሳንቲ ሜትር ብቻ ነበር። አንድ ክንድ ማለት ነው።

ነገሥታቶች በእንዲህ ያሉ ፍጡሮች መጫወት ደስ ስለሚላቸው ከሰው የተለዩ ሰዎችን መሰብሰብ ይወዱ ነበር። በተለይ የሮማ ነገሥታት በዚህ አሰባሰብ የታወቁ ነበሩ። በታሪክ ላይ እንደሚገኘው ካርዲናል ቪቴሌ በ1566 ዓ.ም በሮማ ከተማ ውስጥ 34 ድንክዮችን ሰብስበው ነበር። ታላቁ ጴጥሮስም የሰበሰቡዋቸውና በቤተ መንግሥታቸው ውስጥ አጫዋች እንዲሆኑ ያደረጓቸው ድንክዬዎች በ1710 ዓ.ም 72 ደርሰው ነበር።

በረጃጅሞች ታሪክ ውስጥ እንደነገርኮት ሁሉ በዓለም ላይ ካሉ ሰዎች በአጭርነታቸው የታወቁ ጎሳዎችም አሉ። ኔግሪቶ ኦንጌ የተባለው ጎሣ ሰዎች አጭር የበዛባቸዋል። በ1956 ዓ.ም በግንቦት ወር በተደረገው ጥናት የኔግሪቶ ኦንጌ ጎሣ ሰዎች ቁመታቸው ከአንድ ሜትር ከሃያ ሳንቲ ሜትር አይበልጥም። የዚህ ጎሣ ሰዎች የሚገኙት በሕንድ ውቅያኖስ ትንሿ እንዳማን በተባለች ደሴት ላይ ነው።

በ1936 ዓ.ም በሰኔ ወር በወጣው የጥናት መግለጫ በቻይና አገር ሁፔህ በተባለ ቦታ ቁመታቸው ከአንድ ሜትር ከሃያ ያነሰ 800 ሰዎች መኖራቸውን ይናገራል።

ትንባሆ አጫሽ ነዎት? ትንባሆ እንዴት ያስቀጣ እንደነበር ሰምተዋል። ጥቂት ላውራሎት። ከ1623 እስከ 1640 ዓ.ም በቱርክ ሡልጣን የነበሩት ሙራድ አንድ ቀን ማታ ሲንሸራሸሩ ትንባሆ የሚያጤሱ ሰዎች አዩ። በማግስቱ ሰዎቹን በአደባባይ አስገድለው ሀብታቸው በሙሉ እንዲወረስ አስደረጉ።

በ1633 ዓ፣ም ኮንስታንቲኖፕል የተቃጠለ ጊዜ የትንባሆ አጫሾች መዘዝ ነው ተብሎ በሺ የሚቆጠሩ ትንባሆ አጫሾች ተገድለዋል።

በሩሲያ ታላቁ ጴጥሮስ እስከተነሱበትና እስከ አገዱበት እስከ 1697 ዓ.ም ድረስ ትንባሆ አጫሾች አፍንጫቸውን ይኖነኑ (ይቆረጡ) ነበር።

# አስደናቂ ጠንቋይ

ማውሪውስ ወድወርፍ ይባላል። የልጅነቱን ዘመን ያሳለፈው ወይም ያደገው በለንደን ከተማ ነው። ውድወርፍ ሲናገር «በልጅነቴ እንደ ልጆች ኁሉ ዓይኔን ሲበላኝ የማከው ወይም ከእንቅልፌ ስነሳ የማሸው ግንባሬ ላይ ያለችውን ሦስተኛዋን ዓይኔን

ነበር። ከሌሎቹ የተለየ እርስዋ ትበላኝ ነበርና ነው። በምተኛበትም ጊዜ ከራሴ ላይ ያለውን ጠጉር ስቤ ሦስተኛዋን ዓይኔን አልብሼ እተኛለሁ» ይላል

የውድውርፍ ሦስተኛ ዓይን እንደ ሌሎቹ ዓይኖቹ ሁሉ ታይለታለች። ብዙ ጊዜ ድረስም በዚች በሦስተኛ ዓይኑ አያፍርባትም ነበር። ውድወርፍ አሁን ጥሩ ጠንቋይ ነው። በዚህ በጥንቆላ ተግባሩም ሮልስሮይ መኪናውን ከብር አሠርቷል። ውድወርፍ በአንድ ዓመት ሰላሳ ሺህ ማይል ከአንድ ወዳንዱ አገር ይዟዟራል። ይህም የሚጓዘው ያሉትን የአንድ ሺ አምስት መቶ ደንበኞቹን ፍላጎት በጥንቆላ ለማርካትና ወደፊት ምን እንደሚሆን ለመንገር ነው።

አሁን 52 ዓመት ዕድሜ ያለው ውድወርፍ ብዙ ጊዜ የሚጠነቁላቸው ጥንቆላዎች ይይዙለታል። በተለይ የውድወርፍ ጥንቆላ የሚያስደንቀው የተረገዘን ልጅ ጾታ ለይቶ መናገሩ ነው። ልክ እሱ እንደሚናገረው ይወለዳል። ከዚህም ሌላ ፕሬዚደንት ኬኔዲና አንዳንድ ትልልቅ ሰዎች የሚሞቱበን ቀን ጭምር ተናግሮ ስለ ነበር ልክ እንደተናገረው ተፈጽሟል እ.ኤ.አ 1968 ዓ.ም ለጋዜጠኞች በሰጠው መግለጫ «በቪየትናም ጦርነት ማንም ማንንም አያሸንፍም፤ ጦርነቱ እየቀዘቀዘ ይሄዳል። ፕሬዚደንት ጆንሰን በዚህ ዓመት መጨረሻ በሰላም ሥልጣናቸውን ይለቃሉ። ከዚያ በኋላ ለምን ጊዜውም ከዋይት ሐውስ አይገቡም» ብሎ ተናግሯል።

ውድወርፍ ለአንድ ሰው የሚጠነቁለው 45 ደቂቃ ነው ለዚህም አንድ ጊዜ ጥንቆላው በኢትዮጵያ ብር ሂሳብ ሲመነዘር $ 125 ይቀበላል። በአንድ ቀን የሚጠነቁለውም ለሦስት ሰዎች ብቻ ነው። በዚህ ምክንያት እየተመዘገበ ተራውን የሚጠብቀው ሕዝብ እየበዛ ሄድዋል። ለምን በየቀኑ ለብዙ ሰዎች እንደሚጠነቁል ተጠይቆ «ድሮ ለአሥራ ሁለት ሰዎች እጠነቁል ነበር። ግን እየደከመኝና እየሰለቸኝም ጥንቆላው መልካም ስላልሆነልኝ በቀን ለሦስት ሰዎች ብቻ እንድጠነቁል ወሰንኩ። በተረፈው ጊዜዬ በየቦታው እየሄድሁ እደሰታለሁ» ብሏል።

***

# የዝንቧ ጣጣ

ሉዊ ፎክስ የተባለው አሜሪካዊ በዘመኑ በቢልያርድ (በከረንቦላ) ጨዋታ ተወዳዳሪ ያልነበረው ሰው ነበር። የቢልያርድ ግጥሚያ ለማድረግ በሚፈልግበት ጊዜ የክት ልብሶቹን ባርኔጣውን ካጠለቀ በኋላ በላዩ ላይ ከሐር የተሠራውን ካባ ይደርብበታል። ከዚያ በኋላ ተወዳዳሪዎቹን አንድ በአንድ ያሸንፍ ነበር። እንዳጋጣሚ ሆነና መስከረም 7 ቀን 1865 ዓ.ም ጆን ዲሪ የተባለ ሌላ አሜሪካዊ ከሉፎክስ ጋር

ቢሊያርድ ለመግጠም ወደ ኒውዮርክ ከተማ ተጓዘ። የግጥሚያው አዘጋጅ ኮሚቴ ለአሸናፊው ሰው 140.000 የኢትዮጵያ ብር የሚገመት ሽልማት አደራጅቶ ስለነበር ይህን አስደናቂ ውድድር ለመመልከት ሕዝቡ ሮቸስተር ወዳለው ወደው ዋሽንግተን አዳራሽ መጉረፍ ጀመረ።

የቢልያርዱ ግጥሚያ በሉዊ ፎክስ እንደተጀመረ ከየት እንደመጣ ያልታወቀ ግዙፍ ሰማያዊ ዝንብ ድምፁን እያሰማ በድብልብሊቱ የቢልያርድ ድንጋይ ላይ አረፈ። ዝንቡ በቢልያርዱ ድንጋይ ላይ ያረፈበት ጊዜ ሉዊ የአሸናፊነቱን ጨዋታ ሊያሳይ የተቃረበበት ጊዜ ስለ ነበረ ተመልካቹ ሕዝብ ዓይኑን በዝንቡ ላይ አሳረፈ። ሉዊ ነገሩን ችላ በማለት ዝንቡን አባረረ። ሆኖም ዝንቡ በአዳራሹ ከዞረ በኋላ ተመልሶ በድንጋዩ ላይ አረፈ። ይህን ሲያይ ፈገግታ አሳየና እንደ ገና ዝንቡን አባረረ። ዝንቡ እንደገና ሁለት ጊዜ ጠረጴዛውን ከዞረ በኋላ በዚያችው ድቡልቡል ድንጋይ ላይ ለማረፍ መጣ። በዚህ ጊዜ ሉዊ ፎክስ ተበሳጨና ዝንቡን ሊገድል እጁን ሲያነሳ ተመልካቹ ሁሉ ሳቀበት። ሳቁ ጋብ እንዳለ ሉዊ ኳሷን መታ። የማሸነፊያው ነጥብ ሳይመጣለት ስለ ቀረ ተራውን ለጆን ዲሪ ሰጠ። ጆንዲሪ ከመሸነፍ ያዳነውን ዝንብ እያመሰገነ ድንጋዩን ለመምታት የመጫወቻ ዘንጉን አስተካከለ። ኳሷን መትቶ የአሸናፊነት ነጥቡንም አገኘ።

ሉዊፎክስ አንድም ነገር ሳይናገር ከመጋጠሚያው ሥፍራ ወጣ። ይህንን ያዩ ጓደኞቹ ሊያጽናኑት ከቤቱ ቢሄዱ አጡት። በማግስቱ የሉዊ ሬሳ ከወንዝ ላይ ሲንሳፈፍ በመታየቱ በከተማው ሕዝብ ዘንድ ወሬው ተስፋፋ። ሕዝቡም ሬሳውን ለማየት ወደ ሥፍራው አመራ። የሉዊ አሟሟት ምስጢሩ ሳይታወቅ አስከሬኑ ተቀበረ።

***

# ደማሚቱ ልጅ

በእኛ ዘመን አቆጣጠር ከመጋቢት 17 ቀን 1964 ዓ.ም ጀምሮ በካሊፎርኒያ ግዛት ኦክላንድ በተባለች አምባ አንዲት የአሥር ዓመት ጥቁር አሜሪካዊት ተማሪ የእግርና የእጅዋ መዳፎች እንዲሁም ቀኝ ጎንዋ ምንም የመቁሰል አደጋ ሳይደርስባቸው ደም ማውጣት በመጀመራቸው ነገሩ ለአሜሪካ ሐኪሞች እጅግ አስደናቂ ሆንዋል።

የዚች ጎንና እጅዋ የሚደማባት ልጅ የሚደማበት ጊዜ በፈረንጆች ፋሲካ ሰሞን ነበር። ክሎሪታ ሮቢንሰን የተባለችው ይህቺ የአሥር ዓመት ልጅ በአሜሪካ ሐኪሞች ተመርምራ ነበር። ውጤቱ ግን ከተአምርነት ሌላ ምክንያት ሊሰጠው አልቻለም። ክሎሪታ የሁለት እጆችዋ መዳፍ፤ ከሁለት እግሮችዋ የውስጥ አካል (መርገጫዋ)፤ ከቀኝ ጎንዋ ላይ ቁስል ሳይኖር ትኩስ ደም የሚወጣ መሆንዋን

ሐኪሞች፤ አስተማሪዎችና ነርሶች አይተው ተደንቀዋል። ደሙ ሲጠርጉት እንደገና የሚወጣ መሆኑንም እነኚሁ ያዩት ሰዎች ተናግረዋል።

የአሜሪካ ቀሳውስት እንደገሙቱት ደሙ የሚወጣበት ክፍል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚስማር የተቸነከረባቸውን የእጅና የእግር መዳፎች፤ በጦር የተወጋበትን የቀኝ ጎኑን የሚያመለክቱ ናቸው። የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ስቅለት መታሰቢያ የሚከበርበት ጊዜ የኢየሱስ በወጣትዋ ላይ ይህ ተአምር መታየቱ እጅግ በጣም አስደናቂ ነገር መሆኑን ብዙ የአሜሪካ ሊቃውንት ተናግረዋል።

እነዚህ የሚደሙት የክሎሪታ ሮቢንሰን የአካል ክፍሎች ያለምንም ጉዳት መድማት ከጀመሩ በኋላ ለጥቂት ቀናት አቋርጠው እንደ ገና ደግሞ ከአሥር ቀናት በኋላ መድማት ጀምረዋል። የዚችን ልጅ ሁኔታ ዶክተር ሎሬታ የተባሉ ሐኪም ከመረመሩ በኋላ ትርጉም ወይም ፍቺ ለመስጠት የሚያስቸግር አጋጣሚ ነው ብለዋል። ክሎሪታ ሮቢንሰን አዘውትራ ቤተ ክርስቲያን መሔድና በዚያ መዋል የምትወድ ልጅ ነበረች። ግን ያለ ምንም እንከን ደሙ እንዴት ሊወጣ ቻለ?

***

በምዕራብ ጀርመን ውስጥ በ208 ሙዚቀኝኖች ላይ ሙዚቃ ምን ሊያደርስ እንደሚችል ምርምርና ጥናት ተደርጎ ነበር። በተገኘው ውጤት ለስላሳ ሙዚቃ አዘውትረው የሚጫወቱት ምንም ለውጥ የሌላቸው ሲሆኑ ዘመናዊ ሙዚቃ የሚጫወቱት ግን የወፈፌነት ጠባይ የሚያድርባቸው ሆነው ተገኝተዋል።

# ዝሆን

ዛሬ በምድር ላይ ከሚኖሩት አራዊት ሁሉ ዝሆንን የሚያህል ትልቅ አውሬ ዓለም። ዝሆን ለመጀመሪያ ጊዜ የገኘው በአፍሪካ ምድረ ዓለም እንደሆነ ሊቃውንት ይናገራሉ የዝሆንን የአመጣጡንና የአፈጣጠሩን ታሪክ ትተን ስለዝሆን ታላቅነት፤ ጥቂት እንጫወት ዝሆን ከምድር፤ አራዊቶች የሚለይበት ብዙ ተፈጥሮ አለው። ከአራዊት ሁሉ አራት ጉልበቶች ያሉት ዝሆን ብቻ ነው። ዝሆን የማይቸኩል ረጋ ያለ የማይደነብር ፍጥረት ነው። አንድ ዝሆን በአንድ ሰዓት ውስጥ ሮጦ የሚችለው ከ24 እስከ 32 ኪሎ ሜትር ድረስ ነው። ዝሆን፤ በምድር ላይ እየተራመደ ከመሔድ በውሀ ውስጥ መዋኘቱ ይቀለዋል።

ዝሆን መታጠብን የሚወድ ፍጡር ነው። የሚታጠበውም ውሀ በኩንቢው ቀድቶ ገላው ላይ በማፍሰስ ነው። የዝሆን ኩንቢ፤ አርባ ሺ ጡንቻዎች ስላሉት እጅግ በጣም ኃይለኛ መሣሪያ ነው። አንድን ዛፍ ከነሥሩ በኩንቢው መንቀል ይችላል። በኩንቢው ጉድጓድ ይቆፍርበታል። በዝሆን አፈጣጠር ውስጥ ከሚያስንቁት ታሪኮች አንዱ ግዙፍና ኃለይኛ በሆነው ኩንቢው ከመሬት መርፌ ማንሳት መቻሉ ነው።

የዝሆን ቆዳ ውፍረቱ አንድ ኢንች ተኩል ስለሆነ ለብርድ ግድ የለውም። በመቧጠጥም ሆነ በሌላ ነገር ገላው ቢቆስልበት በኩባንያው ከመሬት ጭቃ አንስቶ በቁስሉ ላይ በመለጠፍ ቆዳውን ያክማል።

ዝሆን ከሚደነቅባቸው ነገሮች አንዱ ጥርሱ ነው። የዝሆንን የሚያህል ጥርስ ያላቸው ፍጥረታት በዚህ ዓለም የሉም። የዝሆን ጥርስ ታዳጊ ነው። ማንኛውም ዝሆን አምሳ ኪሎ ያህል ክብደት ያለው ጥርስ አለው። እስካሁን ድረስ በዝሆን ታሪክ ውስጥ በጥርስ ትልቅነት ሪከርድ የያዘው በሱዳን አገር የተገደለው ያንድ ዝሆን ጥርስ ነው። የያዘው በሱዳን አገር የተገደለው ያንድ ዝሆን ጥርስ ነው። የዚያ ዝሆን 150 ኪሎ ክብደት ሲኖረው ርዝመቱ ስምንት ክንድ ነበር። የዝሆን ጥርስ በያይነቱ ነው ወፍራም፤ አጭርና ረጅም ናቸው። የዝሆን ጥርስ ጠንካራ በመሆኑ የቢልያርድ (የከረንቦላ) መጫወቻ ኳስ (ድንጋይ) የሚሠራው ከዝሆን ጥርስ ነው። የዝሆን ጥርስ ቀለም ነጭ ብቻ አይደለም። ቡናማ ቀይ፤ ጽጌረዳማና ጥቁር ጥርሶች ያሏቸው ዝሆኖች አሉ።

ዝሆን በገላው ላይ ጠጉር የሌለው ፍጥረት ነው። በዚያች በአጭር ጭራው ላይ ብቻ ጥቂት ጠጉሮች አሉ። በእግሩ ላይ ባሉት ዱሽ ጣቶቹ ላይ የሚበቅሉት ጥፍሮች ከባዶች ናቸው።

ዝሆን ተረግዞ የሚወለድ ፍጡር ነው። እናቲቱ ዝሆን፤ የእርግዝናዋ ጊዜ እስከ 22 ወር ይደርሳል። እናቲቱ ዝሆን ልጅዋን ከሃያ ወር በላይ አርግዛ ስትወልድ አዲስ ይወለደችው ግልገል ቁመቷ አንድ ሜትር ይረዝማል። የዚች አዲስ የተወለደች ግልገል ክብደትም አንድ መቶ ኪሎ ድረስ ይመዝናል። የዝሆን ግልገል ሁለት ዓመት ሙሉ ከእናትዋ ሳትለይ በእናትዋ ሞግዚትነት ታድጋለች። አንዲት ዝሆን በዕድሜዋ ከአራትና ከአምስት በላይ አትወልድም።

ዝሆን በአበላሉ የታወቀ ኀበዝ ነው። ዝሆን በአንድ ቀን እስከ መቶ ኪሎ የሚመዝን ምግብ ይበላል። በቀን የሚጠጣው ውሃ 250 ሊትር ያህል ነው። የዝሆን ምግቡ ቅጠላ ቅጠል፤ ፍሬ የዛፍ ቅርፊት፤ ፍራፍሬ መብላት ይወዳል። ምንም ዓይነት ዛፍ ቢሆን ዛፉን በመነቅነቅ ፍሬዎቹን አራግፎ ይመገባል። ዝሆን ለከባድ ሥራና ለመከራ ጊዜ የሚመረጥ ጠንካራና ኃይለኛ ፍጡር ነው። ከክርስቶስ ልደት በፊት በ218 ዓመተ ዓለም አኒባል ወታደሮቹን እየመራ የአልፐን ተራራ ማለፍ የቻለው በዝሆኖቹ ኃይል ነው።

***

# የማየት ኃይል

የካቲት 3 ቀን በ1866 ዓ.ም ሞሊ ከእናትዋ ጋር ሆና ስቲቨንከርት በሚገኘው ቤታቸው ከወጥ ቤት ስትሠራ በድንገት ወደቀች። እናቲቱ ለልጅዋ የምታውቀውን ያህል ርዳታ አደረገችላት። ልጅቱ ሳይሻላት በመቅረቱ የዚያ ቤተሰብ ሐኪም የሆኑት የብሮክላይኑ ዶክተር ሣሙኤል ኤፍ ስፒር ተጠርተው መጡ። ሐኪሙ ምንም የሕመም ምልክት ስላጡባት «ምንም አይላት ነገ ጧት ይሽላታል» ብለው ሄዱ። በነጋታው ሳይሻላት ቀረ። ሳምንት ወርም፤ ብትጠብቅ ምንም አልተሻላትም።

ብዙ ሐኪሞች እየተሰበሰቡ እንዲመረምሩዋት ተደረገ። ሞሊ ግን አካልዋ ቀዝቅዞ፤ የልብ አመታትዋ ዝቅ ብሎ፤ ትንፋሽዋ አጥሮ ምንም ለውጥ የማታሳይ ሆነች። ሐኪሞቹም በየተራ እያዩዋት ራሳቸውን እየነቀነቁ መውጣት ሆነ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሞሊ ዘጠኝ ዓመት ኖረች። በዚህም ዘተኝ ዓመት ውስጥ አንዳችም ምግብ አትቀምስም ነበር።

የሞሊን ሁኔታ ይከታተሉ የነበሩት ዶክተር ስፒር በ1875 ዓ.ም አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ በአካባቢያቸው ያሉት ሐኪሞች ሁሉ ከቢሮአቸው እንዲሰበሰቡ አደረጉ። ከዚያም በሐኪሞቹ ጉባኤ ላይ «ክቡራን ሆይ፤ ለዚህች ልጅ በሽታ ብዙ ደክመን፤ ምንም ያገኘነው ውጤት የለም። አሁን ግን ልጅቱ አንድ የተፈጥሮ ችሎታ ወይም ኃይል ማግኘትዋን አረጋግጫለሁ» ተናገሩ።

የቦስተኑ ሐኪም ዶክተር ሮበርት አርሚስተን «ምንድነው ኃይሉ? ይሄንንስ ኃይል የምትለውን ነገር ልናውቀው እንችላለን ወይ?» ብለው ጠየቁ።

ዶክተር ስፒርም «ራሳችሁ ይህን ነገር ለማረጋገጥ እንድትችሉ ቀጠሮ አድርገን ከልጅቱ ዘንድ እንገናኝ» ብለው ጉባኤውን በተኑ።

በቀጠሮው ቀን ስለልጅቱ ሁኔታ ያጠኑ የነበሩት ዶክተሮች ብቻ ሳይሆኑ ለእማኝነት የከዋክብት ሊቅ የሆኑት ዶክተር ሪቻርድ ፓርከርስት የኒውዮርክ ኒዮሮሎጂስት ዶክተር ዊላርድ ፓርከርና ሌሎችም ሐኪሞች እንዲገኙ ተደረገ። መጀመሪያ የልጅቱ ፖልስ (የደም መዘዋወር) እንዲለካ ተደረገ። እጅግ በጣም ደካማ ሆኖ ተገኘ። የትንፋሽዋ ማነስና የአካልዋ መቀዝቀዝ በሞትና በሕይወት መሐል መሆንዋን አረጋገጠ። በዚህ ሐኪሞቹ ሁሉ ተስማሙ።

ከዚያ በኋላ ዶክተር ፒርስ «ወዳጆጆቼ ሆይ፤ ይቺ ልጅ በሙቶ ማይል ርቀት ያለ ሰው የለበሰውን ልብስና ሁኔታ ሁሉ ዘርዝራ መናገር ትችላለች። ከዚያም ሌላ ደግሞ እጥፍጥፍ ብሎ የታሸገ ደብዳቤ በዚያው ባለበት ሁኔታ እንደሆነ፤ ሳትገልጠው ማንበብ ትችላለች» ብለው ተናገሩ።

ዶክተር ፓርከርስት እና ዶክተር ፓርከር ልጅቱ ካለችበት ክፍል ወጥተው ተማከሩ። በምክራቸውም መሠረት አንድ ደብዳቤ ጽፈው በሦስት እንቬሎፕ ውስጥ አሽገው ዶክተር ፒርስ ቢሮ ሕመምተኛዋ ሞሊ ካለችበት ካለችበት ስምንት ኪሎ ሜትር ይርቃል። ይህንስ ቢሮ ውስጥ ያለው እኛ የላክነው ደብዳቤ ምን ይላል» አሉዋት። ሞሊ ጥቂት ተንፍሳ በደከመ ድምፅ «ወደ ዶክተር ፒርስ የላካችሁት ደብዳቤ በሦስት ኢንቬሎፕ ውስጥ የታሸገ ነው። የሦስቱ ኢንቨሎፖች ውስጥ ባለው ቁራጭ ወረቀት፤ ላይ የተጻፈው ጽሑፍ አብርሃም ሊንከን በአንድ ወፈፌ አክተር ተገደለ የሚል ነው» አለቻቸው።

ከዚህ በኋላ ሐኪሞቹ ሁሉ በአንድነት ወደ ዶክተር ፒርስ ቢሮ ሄዱ። ከዚያም ኢንቬሎፖቹን ቀደው ደብዳቤውን ቢመለከቱ ጽሑፉ ልክ ልጅቱ እንዳለችው ሆነ። በዚህ በኩል ዶክተር ፒርስ ለሊቃውንቱ ጉባኤ የተናገሩት ቃል ትክክል መሆኑ ተረጋገጠ። አሁን የቀረው የሩቅ ሰው የለበሰውን ልብስ ሁሉ ትናገራለች የተባለው ነው።

ሊቃውንቱ ወደሞሌ ዘንድ ሂደው «በሩቅ ያሉ ሰዎች፤ ሁሉ ይታዩሻል። የአቶ ጴጥሮስ ግራሃም ወንድም ኒውዮርክ ከተማ ያለው ፍራንክ አሁን እንዴት ሆኖ ይታይሻል?» አሉዋት። ሞሊ ሁኔታዋን በዝርዝር ነገረቻቸው። ከሌላው ዝርዝር አልፋ «ከቀኝ እጁ የኮት እጅጌ ላይ አንዷ ቁልፍ ተበጥሳ ጠፍታበታለች። አቶ ፍራንክ ግርሃም እንደተለመደው ጧት ራስ ምታቱ ስለተነሳበት ከሥራው ተመልሶ ወደ ቤቱ ሄድዋል» አለቻቸው።

ይሄ ነገር ልክ መሆኑን ለማወቅ ሊቃውንቱ ወዲያውኑ በቴሌግራም የአቶ ፍራንክን ሁኔታ ጠየቁ። ሁሉም ነገር ልክ ሆኖ ራስ ምታቱ ስለተነሳበት ሥራውን ትቶ መሄዱ ሁሉ ተነገራቸው። ሊቃውንቶቹ ይህ ከሳይንስ እውቀት የተለየ የእግዚአብሔር ተአምር ነው ብለው ተለያዩ።

ሞሊ ከዚህ ሁኔታ እንዳለች 46 ዓመት ሙሉ ተኛች። ወላጆችዋም ቀድመዋት ሞቱ። ሁኔታዋን ይከታተሉ የነበሩት ዶክተር ፒርስም ከሞሊ ቀድመው በ1912 ዓ.ም ሞቱ። ሞሊ ግን በሰባ ሦስት ዓመት ዕድሜዋ በመጋቢት ወር 1915 ዓ.ም ሞተች።

***

# ያፏጨው ሬሳ

ኩልቫ የተባለች መርከብ በጥቅምት ወር 1952 ዓ.ም ወደ ሆንክ ኮንግ በምታመራበት ጊዜ እግረ መንገድዋን ከፎርሞዛ ደርሳ ነበር። መርከቢቱ ከፎርሞዛ ወደብ እንደለቀቀች በመርከቢቱ ላይ ተጭኖ የነበረው ሬሳ ድምፅ ማሰማት ጀመረ።

ሬሳውን ያስጫነው ሊንግ ኩክ የተባለ ሰው ነው። ሊንግ ኩክ ያስጫነው ሬሳ የመንትያ ወንድሙ የያሜዳቬ ሬሳ ነበር። ያሜዳቬ በአደጋ ምክንያት ቆስሎ ስለሞተ ወንድምየው የወንድሙን ሬሳ ከተወለደበት አገሩ በሆንግ ኮንግ ማስቀበር ይዞት መሔዱ ነበር።

እኩለ ለሊት ላይ ሊንግ ኩክ በመርከቡ በረንዳ ላይ ሆን ወደ ባሕሩ እየተመለከተ ስለመንትያ ወንድሙ ሞት በሚያዝንበት ጊዜ አንድ ድምፅ ሰማ። በመጀመሪያ ጊዜ የሰማው የፉጨት ድምፅ ከመርከቡ ሞተር የሚወጣ መስሎት ነበር። ፉጨቱ በመደጋገሙ ወንድሙ በሕይወት በነበረበት ጊዜ ያፏጭለት የነበረው ፉጨት መሆኑን አወቀ። እንባው ይወርድ ጀመር። ጥቂት ቆይቶም የፉጨቱ ሁኔታ በተለየ ስልት ተለወጠ።

ሊንግ ኩክ ወደ መርከቧ አዛዥ ቢሮ ሮጦ ገብቶ ለመርከብዋ አዛዥ ለካፒቴን ኬለር «የሚያፏጨው ወንድሜ ነው ወንድሜ ያማዴቭ አልሞተም። ሳትዘገይ ቶሎ ብለህ የወንድሜ ሬሳ ያለበትን ሳጥን ክፈትልኝ» አለው። አቶ ሊንግ ኩክ ወንድሙ ሲቆስል አይቶታል። ሲሞትም አይቶ ሬሳውን ታቅፎ አልቅሷል። ሬሳው በሳጥን ውስጥ ሲከተትም ለመጨረሻ ጊዜ የወንድሙን ሬሳ ስሞ ተሰናብቶታል። ታድያ አሁን እንዴት ወንድሜ አልሞተም ይላል?

ካፒቴን ኬለር በአቶ ሊንግ ኩክ ጥያቄ ግራ ገባው። ከክፍሉ ወጥቶ ከመርከቡ ወለል ላይ ሲቆም ያን ፉጨት እንደገና ሰማው። በመርከቢቱ ውስጥ ያሉ መንገደኞችና የመርከቧ ሠራተኞችም በፉጨቱ ተረበሹ። ሊንግ ኩክ «የሚያፏጨው ወንድሜ ያማዴቭ ነው። ይህ ፉቸት ወንድሜ በሕይወት በነበረ ጊዜ የሚያፏጭልኝ ፉጨት ነው። ይህም ፉጨት የግል ሚስጢር እንድረዳው ሲፈልግ የሚያፏጭልኝ በዚህ በአሁኑ ፉቸት ወይንድሜ ያሜዴቫ ርዳኝ ማለቱ ነው። ስለዚህ ሬሳውን ያለበትን ሳጥን ክፈቱልኝ» አለ።

ከዚህ በኋላ ካፒቴን ኬለር የመርከቧ ሠራተኞች ሬሳው ያለበትን ሳጥን ከመርከቧ ፓትኛ ክፍል አውጥተው እነሱ ካሉበት ከመርከቧ ሜዳ ላይ እንዲያደርጉት አዘዘ። ሬሳው ያለበት ሳጥን ከመርከቧ ታችኛ ክፍል ወጥቶ ከሜዳው ላይ እስኪደረግ ድረስ ፉጨቱ አላቋረጠም። ብዙዎቹ መንገደኞችም ከፉጨቱ ጩኸት የተነሳ የጆሮ ከረቦአቸው አደጋ እንዳይደርስበት ጆሮአቸውን በእጃቸው እየደፈኑ ሬሳውን ከያዘውና

ከሚያፏጨው ሳጥን ዙርያ ተሰበሰቡ። ካፒቴን ኬለር ሬሳውን የያዘው ሳጥን እንዲከፈት አዘዘ። ተከፈተ። መብራት መጥቶ ሬሳው ላይ በራ። በመርከቧ ላይ ያለው ሕዝብ ዙርያውን ከቦ ሲመለከት ሬሳው በእርግጥ ሬሳ ነበር። ትንፋሽ የለውም ልቡም ቆሞ ደም በአካሉ አይመላለስም። ዓይኑም እንደ ተጨፈነ ነበር። እንዲህ እየመረመሩ ጥቂት እንደቆዩ የሬሳው ዓይን መከፈት ጀመረ። ቀስ እያለ የተከፈተው የሬሳው ዓይን ወንድሙን ሊንግ ሉክን ይፈልግ ጀመር ከዚያም ከወንድሙ ጋር ሲተያዩ ሳጥኑ የተደጋገመው የያሜዴቫ ሬሳ «ጃን» ብሎ ተናገረ ዓይኑን ጨፈነ። እንደገናም ሞተ።

የወንድሙን ጥሪ የሰማው ሊንግ ኩክ ልቡ ቆመ። ወዲያውም ሞተ። የሁለቱም የወንድማማቾች ሬሳ ሆንግ ኮንግ ተወስዶ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበት «የደስታ ሸለቆ» በተባለው የመቃብር ሥፍራ በአንድነት ተቀበሩ።

# ጡንቻ

የጡንቻ ኃይል ካላቸው ሰዎች አንዱ እንግሊዛዊው ቤቲ ሰግሪ ነበር። ቤቲ ባለ ፎቅ የሆነው አውቶብስ በጥርሱ እየሳበ በለንደን ከተማ በደብሊን መንገድ ላይ ለሕዝብ አሳይቷል። በለንደ ከተማ ውስጥ አድሚራል ኒልሰን የቤቲን ዝና ሰምተው አላምን ቢሉና ሰምተው አላምን ቢሉ ከቢሮአቸው ድረስ አስመጥተው አድሚራሉ ወንበራቸው ላይ እንደተቀመጡ ከነወንበራቸው በጥርሱ አንስቷቸዋል። ጋዜጠኞችም ለሚያደርጉለት ጥያቄም መልሱን ከነወንበራቸው በጥርሱ በማንሳት ይነግራቸው ነበር።

አንድ ጊዜ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበት ቦታ አንዲት ሞተር ብስክሌት ላይ አንድ ወጣት ከተቀመጠ። ሞተር ብስክሌትዋ ከኋላዋ በገመድ ታበተችና የገመዱን ጫፍ ቤቲ በጥርሱ ነክሶ ያዘ። ከዚያ በኋላ ሞተር ብስክሌትዋ ሞተርዋ ተነስቶ እንድትነዳ ተደረገ። በምንም ዓይነት ኃይል ቢሞክር ቤቲ በጥርሱ በያዘው ገመድ ሞተር ቢስክሌቷን አላስነቃንቅ አለ። እንዲያውም የሞተሩን ኃይል በጥርሱ በያዘው ገመድ ጎትቶ ሞተር ብስሌቷን ወደ ኋላ አንፏቀቃት።

ቤቲ በ1968 ዓ.ም በዘጠና ዓመት ዕድሜው በለንደን ከተማ በቅዱስ ፍራንሲስ ሆስፒታል ውስጥ ሞቷል። ቤቲ ከመሞቱ በፊት በ85 ዓመት ዕድሜው በወንበር ላይ በቀን አምሳ ጊዜ ይዘል ነበር። በዚያው ዕድሜው ሁለት እግሮቹ ተጋጥመው ታስረው በጠረጴዛ ላይ ያለማቋረጥ አንድ መቶ ጊዜ መዝለል ይችል ነበር።

አንድ ጊዜ በሶቪየት ውስጥ በሌኒንግራድ ከተማ ብዙ ሺ ሕዝብ በተሰበሰበተ ሁለት ፈረሶች ግራና ቀኝ በጠንካራ ጠፍር ታስረው ቀረቡ። ቤቲ ደግሞ ፊቱን ወደ ፈረሶቹ አድርጎ ከመሐከላቸው ባለው ጠፍር ላይ ደረቱን አጋደመ። ከዚያ በኋላ ፈረሶቹ

እንዲጋልቡ ይገረፉ ጀመር። ቤቲ ግን በደረቱ ወጥሮ በያዘው ጠፍር ፈረሶቹን ንቅንቅ ሊያስደርጋቸው አልቻለም። በመጨረሻም ፈረሶቹ ደከመው ሲወድቁ የትርኢቱ ፍጻሜ ሆነ። ይህ «የሩሲያ አንበሳ» የሚል ቅጽል የወጣለት ቤቲ በሰው ልጆች የጡንቻ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ የያዘ ነው።

እንዲህ ያለ የጡንቻ ኃይል ያላቸው ሰዎች ጥቂት ነበሩ። የጎሌው ነዋሪ ፍሬደሪክ ጀንሰን በገመድ ጉተታ አሥር ኃይለኛ ሰዎች ተመርጠው በአንድ በኩል ሆነው እሱን ብቻውን እንዲጎትቱት ተደርጎ አሥሩ ሰዎች ፍሬደሪክን ከቆመበት ሊያነቃንቁት አልቻሉም። ይህ በሆነ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ፍሬደሪክ በዚያው ዘመን ጠንቅ ሞተ።

በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቢል ጂሲ የተባለ ጠንካራ ሰው በጭንቅላቱ የኮከናት ፍሬ መስበት ይችል ነበር። ቢልጂሲ ሌላም ነገር ይሠራ ነበር። 127 ኪሎ ግራም ክብደት ያለውን ሰው በጥርሱ አንጠልጥሎ ማንሳት ይችል ነበር። ይህም ብቻ አይደለም። የፈረስ (ብረቱን) በሁለት ጣቶቹ የብረቱን ጫፍና ጫፍ ማጋጠም ይችል ነበር። ይሄ ሁሉ ሥራው የቢል ጆሲን ዝና አላገነነለትም ነበር። አንድ ቀን አንድ ፈረስ ተሸክሞ አምስት ሜትር ያህል ርዝመት ካለው መሰላል ተሸክሞ አምስት ሜትር ያህል ርዝመት ካለው መሰላል ላይ ወጣ። ከዚያ በኋላ ሳልሳዊ ንጉሥ ዊልያም ጠርተው በኬንሲግተን ቤተ መንግሥት ውስጥ ምን ኃይለኛ ሰው ነህ?» ቢሉት «ግርማዊ ሆይ፤ እንደ ፈረስ የጠእንከርኩ ሰው ነኝ - ብሎ መለሰላቸው። ንጉሡ መጠንከሩን ሊፈትኑት ፈለጉ። ወፍራም ገመድ እንዲመጣ ንጉሠ አዘዙ። መጣ። የገመዱ አንዱ ጫፍ በጆሲ ወገብ ላይ ታሠረ። ሌላው ጫፍ ደግሞ በኃይለኛ ፈረስ ወገብ ላይ ታስሮ ፈረሱ ጆሲን እንዲስበው ይገረፍ ጀመር። ጆሲና ፈረሱ ሃያ ደቂቃ ያህል ከተጓተቱ በኋላ ፈረሱ ደክሞት ወደቀ። ከዚያ በኋላ ጆሴ የተጓተተበትን ገመድ በጣጥሶ ከንጉሡ ፊት ጣለው። ይህን ጉድ ያዩ ንጉሥ ዊልያም፤ ጆሲን ሸልመው በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ካሉት ሌሎች አጫዋቾቻቸው ጋር እንዲኖር አደረጉት፡

በ1860 ዓ.ም የተነሳው ፓዲ ኦርሌይ የተባለ ሰው 95 ኪሎ ክብደት ያለውን ሰው በጥርሱ አንጠልጥሎ ከመሬት አንስቶ ከፈረሱ ላይ አስቀምጦታል። በምሥራቅ ፕርሺያ ተነስቶ የነበረው ኢንግ ሳንዶው የተባለው ጡንቸኛ ሰው ሰው የእንግሊዝ የሙዚቀኞች ማኅበር ተከራይቶት ለትርኢት ሲያቀርበው በደረቱ ላይ ሳንቃ ተደረገ በሳንቃው ላይ ትልቅ ፒያኖ ተቀመጠ፤ ከፒያኖው ጋር በዚያ ሳንቃ ላይ ስምንት ሰዎች ወጥተው የሙዚቃ ትርኢት ለሕዝብ አሳዩ። ይህ ሁሉ ሲሆን ኢግን ሳንዶው ምንም የድካም ስሜት አላሳየም ነበር። ኢግን ሳንዳዎ በ1925 ዓ.ም በተወለደ በ58 ዓ.ም ዕድሜው በመኪና አደጋ ሞተ።

ይሄ በዓለም ላይ የተሠራ ረጅም ብስክሊት ነው። የዚህ ብስክሌት ርዝመት አሥራ ሁለት ሜትር ያህል ሲሆን ሃያ አንድ ሰዎችን መሸከም ይችላል። እነዚህ ሃያ አንድ ሰዎች በብስክሌቱ ላይ በየመቀመጫቸው ከተቀመጡ በኋላ ሃያ አንዱም ያላቸውን ፔዳል ማዞር ይጀምራሉ። ከዚያም ብስክሌቱ በሰዎቹ ጉልበት እየተነዳ ይሄዳል።

# በመቃብር ውስጥ የሞተች ሴት

በኢጣልያ አገር በካሜሪኖ ዩኒቨርስቲ ውስጥ በታኅሣሥ ወር በ1950 ዓ.ም ዶክተር ጁሴፔ እስቶፖሊኖ በልዩ የማጥኒያ ክፍላቸው ሆነው ስለ ሰው ተፈጥሮ ኃይል ከጓደኞቻቸው ጋር ሆኖ የሚረዳቸው አቶ ማርዮ ባኮ እንደ ተቀመጠ ዓይኑ ፈጠጠ። ሽፋሎቹ ፍርሃት እንደያዘው ሰው ሽቅብ ተጎተቱ። ያንቀጥቅጠውም ጀመር።

በክፍሉ ውስጥ ያሉት ሰዎች በማርዮ ዙርያ ከበቡ። ዶክተር ጁሴፔም ብዙ ጊዜ አብሯቸው የሠራው ማርዮ ከዚያ በፊት እንዲያ ሆኖ አያውቅም ነበርና ምን እንደሆነ ለመመርመር ጀመሩ። የሚጥል በሽታም እንደሌለበት አጣርተው ያውቃሉ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ የማርዮ ባኮ ከንፈሮች መንቀሳቀስ ጀመሩ። ማርዮ ባኮ ይናገር ጀመር። የሚናገረው በራሱ ድምፅ ሳይሆን በሴት ድምፅ ነበር። ለዚያውም ደግሞ በሚያውቀው በደንበኛው የኢጣልያንኛ ቋንቋ ሳይሆን በሲሲሊያኖች ያነጋገር ዘይቤ ነበር።

ዶክተር ጁሴፔ ቶሎ ብለው ቴፕሬከርድ ከፍተው የማርዮን ንግግር ይቀዱ ጀመር። «.....እኔ ሮዛ ማንቺሊ እባላለሁ። ሳልሞት ከነሕይወቴ በሳጥን ውስጥ ከተው የቀበሩኝ ሴት ነኝ። የተቀበርኩትም ከሜሪኖ የመቀበሪያ ቦታ ነው። እናንተ በዚህ ላቦራቶሪ ውስጥ የምታጠኑ ወይም የምትመራመሩ ሰዎች ከነሕይወቴ ለመቀበሬ ሂዱና ሬሳዬን አውጥታችሁ እዩ።...... ሞታለች ብለው የቀበሩኝ ልክ በዚሁ በታኅሣሥ ወር ሲሆን ዘመኑ ግን በ1939 ዓ.ም ነው።...... የልቤን አመታት መቆም አይተው ሞታለች ብለው ቀበሩኝ። እኔ ግን አልሞትኩም ነበር። እርግጥ ደክሜ እንደሞተ ዓይነት ሆኜ ነበር፡ የመረመረኝ ሐኪም ያልሞትኩትን ሴትዮ ሞታለች ብሎ ስለተናገረ ቀበሩኝ።..... ሲቀብሩኝ አንዳንድ ነገሮች ይሰሙኝ ነበር ከሩቅ የቀሳውስትን ድምፅ እሰማ ነበር። ሳጥኑን ቁልቁል ሲያወርዱትም እሰማ ነበር። በሳጥኑ ላይ ብዙ ነገሮች ሲያንኳኩም እሰማ ነበር። ግን ለመውጣት ወይም ለመናገር አቅም አጣሁ። ለመውጣት ለፍቼ ለፍቼ ስላቃተኝ አሁን ሞቻለሁ ሂዱና አጼምን እዩ።......» አለች። ከዚያ በኋላ ማርዮ ነቃ።

ዶክተር ጁሴፔ እስቶፖሊኖ ይህን በቴፒ የቀዱትን ንግግር ደጋግመው ካዳመጡ በኋላ ወደ መቃብሩ ቦታ ሄደው ከዚያ ያሉትን የመቃብር ቦታ አላፊዎች

ወይዘሮ ሮዛ ማንቼሊ በ1939 ዓ.ም ማለት ከአሥራ አንድ ዓመት በፊት ሞታ የተቀበረችበትን ቦታ እንዲያሳዩዋቸው ጠየቁ። የመቃብሩ ቦታ አላፊዎች መዝገባቸውን አይተው እንዲያ ያለ ስም ያላት ሴት በዚያ የመቃብር ሥፍራ ያለመቀበርዋን ነግሯቸው።

ዶክተር ጁሴፔ ተናደዱ። ማርዮ ባኮ ሲቀልድ ያሾፈባቸው መስሏቸው ተበሳጩ። ወሬው እየተራባ በመሔዱ ከዩኒቨርስቲው ተማሪዎች ዘንድ ደረሰ። ወሬው ከዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች አንዱ ሮዛ ሚንቺሊ የተባለች አክስት እንደነበረችውና ሞታም የተቀበረችውም በ1939 ዓ.ም በታኅሣሥ ወር እንደነበር ተናገረ። የተቀበረችውም በካሜሪኖ የመቀበሪያ ቦታ ሲሆን ስምዋ ግን የተመዘገበው በጋብቻ ስምዋ ሮዛ እስፖዶኒ ተብሎ መሆኑን አስረዳ።

ከዚያ በኋላ ዶክተር ጁሴፔ ከሕዝብ ጤና ጥበቃው ክፍል የመቃብሩን ማስቆፈሪያ ፈቃድ ተቀበሉ። ከአገሩ ታላላቅ ባለሥልጣኖች፣ ከዶክተሮች ከጋዜጠኞችና ከፎቶ ግራፍ አንሺዎች ጋር ሆነው ከመቃብሩ ሥፍራ ሂደው የሮዛ መቃብር ተቆለፈ። ሳጥኑም ወጣ። ተከፈተ። በውስጡ ያለው አጽም እንደተቀበረበት ሁኔታ ሳይሆን ተገኘ።

የሮዛ አጽም ተገለባብጧል። ወገቧ ጎብጦ ከሳጥኑ መከደኛ ጋር ተጋጥሟል። ይህም ሳጥኑን በጀርባዋ ገፍታ ለመከፈት ያደረገችው ሙከራ መሆኑ ተረጋገጠ። አንድ እጅዋ የሳጥኑን ጎን ወጥሮ ይዞታል። ይህም ሳጥኑን በእጅዋ ገፍታ ለመከፈት ያደረገችው ሙከራ ነበር። ጠጉርዋ ተነጫጭቶ በአንድ እጅዋ አጠገብ ተገኘ። ይህም ሳጥኑን ለመከፈት ባለመቻልዋ ተናዳ ጠጉርዋን ነጭታ እንደነበረ ተረጋገጠ። በመጨረሻው ሐኪሞቹና ባለሥልጣኖቹ በሰጡት መግለጫ ሮዛ ሳትሞት ከነሕይወቷ ተቀብራ በመቃብር ውስጥ ታፍና የሞተች መሆንዋን አረጋገጡ።

***

# እባብ

በዚህ ዓለም ላይ አለ ተብሎ የሚገመተው የእባብ ዓይነት ሁለት ሺ ያህል ነው። እባብ በመላው ዓለም የታወቀ ዝነኛ ፍጡር ነው። በክርስትናም ሆነ በእስልምና ሃይማኖቶች ተከታዮች ዘንድ የመጀመሪያዪቱን ሴት ሄዋንን አሳሳተ ስለሚባል የእባብ ታሪክ ከሃይማኖት ታሪክም ጋር አብሮ የሚጓዝ ነው። እባብ ለዓይኑ መከደኛና ጆሮ የሌለው ፍጡር ነው። እባብ መስማት የሚችለው በምላሱ ነው። አንድን ነገር ለማወቅ ወይም አቅጣጫውን ወዴት እንደሆነ ለመለየት በሚፈልግበት ጊዜ ምላሱን ከውጪ

አውጥቶ ያወዛውዛል። ያን ለመስማት የሚፈልገው ነገርም አቅጣጫውን በቀላሉ ያውቀዋል።

እባብ መርዝ ያለውና መርዝም የሌለው ፍጡር ነው። መርዛሞቹ እባቦች በመርዛቸው አንድን ነገር ቶሎ መግደል ሲችሉ መርዝ የሌላቸው እባቦች ግን ለመግደል የሚፈልጉትን ነገር በመዋጥ ይገድሉታል። የእባብ ጥርስ እንደሌላው ጥርስ በአንድ ቦታ የተተከለ ሳይሆን ወደኋላና ወደ ፊት መመላለስ ስለሚችል በሚውጥበት ጊዜ ጥርሱ ወደኋላና ወደ ፊት በማለት እንደመንጠቆ ይስብለታል። ይህም ያን የሚውጠውን ነገር ራሱን ጨርሶ እስቲውጠው ድረስ መግደል አይችልም።

እባብ ምንም ዓይነት ድምፅ የሌለው ፍጡር ነው። ብዙ ሰዎች እባቦች አንድ ሲጢጥ የሚል ድምፅ ወይም እንደ ፉጨት ያለ ድምፅ የሚመጣው እንደማንኛውም ፍጡር ከድምፅ ሳጥን ውስጥ ሳይሆን ከሳንባው ውስጥ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ድምፅ የሚያሰሙ እባቦች ሳንባቸውን እባቦች ሳንባቸውን በአየር ብዛት በኃይል ያስሞሉና በአንድ ጊዜ በኃይል ገፍተው ለማስወጣት እያሉ የፉጨት ድምፅ ያሰማሉ።

እንቁላል የሚጥሉ እባቦችና እንዲሁም ከነነፍሳቸው የሚወለዱ እባቦች አሉ። እንቁላል የሚጥሉ እባቦችና ከነሱ መሰል ዘሮች መሐል አንዳንዶቹ እንቁላሉን የጣለችው እናት እንቁላልዋን ታቅፋ በማሞቅ የምታስፈለፍል ስትሆን አንዳንዶቹ ደግሞ እንቁላላቸውን ሞቃት አየር ካለበት ቦታ ይጥሉና እንቁላሉ በአየር ሙቀት አውቆ ይፈለፈላል።

የእባብ ዘር ሁሉ መርዛም አይደለም። ከእባብ ዘር ወይም ዓይነት ሁሉ መርዝ ያላቸው በጣም ጥቂቶች ናቸው። ኮርባ የሚባለው የእባብ ዘር በመርዘኛነቱ የታወቀና ኃይለኛም ነው። በተለይ ከእባብ ዘር ውስጥ በእርዝማኔና በእምርዘኛነቱ የታወቀ ሐማድርያድ የሚባለው እባብ ነው። የዚህ እባብ ርዝመት ስድስት ሜትር ያህል ይሆናል። ይህ እባብ በመርዘኛነቱ የታወቀ ይሁን እንጂ የእባብ ዘር ሁሉ በእርዝማኔው የሚበልጠው ፈረንጆቹ ፒተር የሚሉት እባብ ነው። የዚህ እባብ ዘር አሥራ ሜትር ያህል ይረዝማል። ይህም እባብ የሚገኘው በማልያ፤ በበርማና፤ በኢንዶቻይና ነው። ከእባብ ዘር ሁሉ በአጭርነቱ የታወቀው በደቡብ አሜሪካ ይገኛል። የዚያም እባብ ርዝመት አሥር ሳንቲ ሜትር ያህል ነው።

ከባድ ሚዛን የሚመዝኑ እባቦችም የሚገኙት በዚያው በደቡብ አሜሪካ ነው። ለምሳሌ አናኮዳ የሚባለው እስከ አንድ መቶ አምሳ ኪሎ ድረስ ይመዝናል። የእባብ ዕድሜ ቢበዛ ከ25 ዓመት አያልፍም እስካሁን ድረስ በእባብ ታሪክ ውስጥ ረጅም ዕድሜ ያገኘው አንድ ከአፍሪካ የተወሰደ የእባብ ዘር ነው። ይህ የእባብ ባላንዲያን ከተማ የአራዊት ማከማቻ ውስጥ ጥቅምት 1 ቀን 1928 ዓ.ም ተፈልፍሎ በ29 ዓመት ከ22 ቀን ዕድሜው በ1957 ዓ.ም ኅዳር 12 ቀን ሞተ።

ማምባ የሚባለው ጥቁር እባብ ፈጣንና ተወርዋሪ ነው። በጉዞው ላይ በአንድ ሰዓት 12 ኪሎ ሜትር ያህል ይሄዳል በአጭር ርቀት ለመወርወር ወይም ለመጓዝ ከፈለገ በሰዓት 25 ኪሎ ሜትር ይወረወራል። የእባብ መርዝ ለሰው ልጅ ጉዳት ብቻ ሳይሆን ጥቅምም ይሰጣል። አብዛኛዎቹ ለሰው ልጅ መዳኛ የሆኑ መድኃኒቶች የሚሠሩት ከእባብ መርዝ ነው። በዚህ ምክንያት ልምድ ያላቸው ሰዎች መርዛም እባቦችን እያረቡ መርዙን በመሸጥ ብዙ ትርፍ ያገኛሉ።

***

የዛሬውን አሜሪካ ኤሮፓውይኖች ይካፈሉት በነበረ ጊዜ እንግሊዛዊው ሰር ዎልተር ራሌህ የዛሬዋን ቪርጂኒያን ለእንግሊዝ ግዛትነት አደላደሏትና ወደ አገራቸው ወደ እንግሊዝ አገር ተመለሱ። ከዚያም ንግሥት ኤልሳቤጥ ራት እንዲጋብዙላቸው ለምነው ብዙ ዓይነት ምግብ ከተበላ በኋላ ከወርቅ ሰሃን ላይ የተቀቀለ ድንች ለንግሥቲቱ አቀረቡ። የምን ድንጋይ አቀረቡ ብለው ንግሥቲቱም መኳንንቱም ደነገጡ። ዎልተር ግን «ንግሥት ሆይ፤ የአዲሱ የቪርጂኒያ ግዛትዎ ሕዝብ የሚበላው ምግብ ነውና ይቅመሱት» አሏቸው። ንግሥቲቱም ቀምሰው ወደዱትና ተባዝቶ ለሁልጊዜ ምግባቸው እንዲሆን አዘዙ። ከዚያም ድንች በእንግሊዝ አገር ታወቀ። እኚሁ ሰር ዎልተር ትንባሆ ማጤስንም ካሜሪካ ያመጡ እሳቸው ነበሩና አንድ ቀን ከክፍላቸው ሆነው ትንባሆውን ከብር ሳጥናቸው አውጥተው በፒፓ ሲያጨሱ ጁልየስ የተባለ አሽከራቸው በቀዳዳ ጭስ አይቶ ቀስ ብሎ ከዎልተር ክፍል ቢገባ ከወልተር አፍ ጭስ ሲወጣና ከፒፓው እሳት ስላየ ጌታዬ ተቃጠሉ ብሎ በማሰሮ ውሃ አምጥቶ አፈሰሰባቸው።

***

አሣ ነባሪ በውሃ ውስጥ ከሃያ ደቂቃ የበለጠ ሊቆይ አይችልም። ስለዚህ የሚተነፍሰውን አየር ፍለጋ በየሃያ ደቂቃ ጊዜ ውስጥ ከውሀው ወደ ውጪ ብቅ ማለት አለበት።

***

በአሜሪካ አገር፤ በካምብሪጅ ውስጥ አንድ ጊዜ በከተማዋ በጎርፍ ተጥለቅልቃ ነበር። በዚህ ግርግር መሐል ሱቆች እንዳይሰረቁ በየበሩ ሆነው ከሚጠብቁት ፖሊሶች መሐል አንዱ ውሀው ከወገቡ እስቲደስ ድረስ ከታዘዘበት ቦታ አልተነቃነቀም።

***

# ሹፌር ነዎት?

ዓይንዎን ጨፍነው መኪና መንዳት ይችላሉ? ቀስ እያሉ ጥቂት መንገድ ሚንፏቀቅ ይችላሉ። ግን በሰዓት 50 ኪሎ ሜትር እያበረሩ ዓይንዎን ጨፍነው መንዳት ይችላሉ? አልችልም ካሉ እውነተኛ ሰው ነዎት።

ይችላሉ። እንዲያውም ነድተዋል። መንዳትዎን ልንገርዎት የዓይንዎ ርግብግቢት ወይም መክደኛው በመሐከለኛ አስተሳሰብ በየሦስቱ ሰከንድ ዓይንዎን በሚጨፍንበት ጊዜ ከአንድ ሰከንድ ውስጥ አንድ አምስተኛውን ዘግቶ ይቆያል።

እንግዲህ እርስዎ ሾፌር ነዎት። 250 ኪሎ ሜትር ርቀት ያለውን መንገድ መኪናዎን በሰዓት 50 ኪሎ ሜትር እየነዱ ቢጓዙ ካሰቡበት ቦታ ለመድረስ አምስት ሰዓት ይጓዛሉ። በዚህ ጊዜ ውስጥ ሃያውን ደቂቃ ወይም አሥራ ስድስቱን ኪሎ ሜትር የተጓዙት ዓይንዎን ጨፍንረው ነው።

ለመሆኑ የዓይንዎን ርግብግቢት ወይም መክደኛውን ሳይዘጉ ምን ያህል ጊዜ ለመቆየት ይችላሉ? ይሞክሩ። ማርያን ኩርስቲ የተባለች ታይፒስት በ1948 ዓ.ም በኒውዮርክ ከተማ 23 ሰዓት ከአሥራ ስምንት ደቂቃ የአንድ ዓይንዋን መክደኛ ሳትዘጋ በመቆየቷ የዓለምን ክብረ ወሰን (ሬከርድ) ይዛለች።

***

በኢትዮጵያ ውስጥ የሰገሌ ጦርነት ከመደረጉ በፊት ንጉሥ ሚካኤል ለልጅ ልጃቸው ለኢያሱ አግዘው የኢያሱ ተቃዋሚዎች ወዳሉበት ወደ ሸዋ ለመዝመት ወሎ ላይ ጦራቸውን አስከተቱ። ይህን ነገር ሸዋዎች ሰምተው ከባድ አሳብ ያዛቸው። የዘመኑ ጦር ሚኒስቴር የነበሩት ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ለንጉሥ ሚካኤል የሸዋን ገባሪነት የሚገልጽ ደብዳቤ ስፈው ለገባሪነታቸው ምልክት በጣም ብዙ ጥይት በአጋሰሶች አስጭነው ላኩ። ንጉሥ ሚካኤል በዚህ ተደስተው እንደተቀመጡ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ጦራቸውን በሚገባ አደራጅተው ሚካኤልንና ኢያሱን ለማጥፋት ተነሱ። ሚካኤልም «ሸዋን በላከው ጥይት እፈጀዋለሁ» ብለው ፎክረው የሰገሌው ጦርነት ተጀመረ ከሸዋ የተላከው ጥይት በሰገሌ ቢሞከር ከሸፈ። ተከፍቶ ቢታይ ባሩዱ እየወጣ አሸዋ የተሞላ ጥይት ሆኖ ተገኘ።

***

አይጣል ይበላ አይጣል ይሏል እንጂ እንዲህ ያለ የመኪና አደጋ ይደርሳል። 33 ዓመት ዕድሜ ያለው አቶ ሮበርት ባክማን ሚስቱን ወይዘሮ ጊሴላን ይዞ በሙኒክ ከተማ ውስጥ ከሥራ ወደ ቤት ይሄዳሉ።

ግዙፍ የሆነው የወታደር መኪና ሲመጣ አቶ ሮበርት የሚነዳትን መኪና ዞር አድርጎ ለግዙፉ መኪና መንገድ ለቀቀ። የግዙፉ መኪና ሹፌር ያቺን መንገድ የለቀቀችለትን መኪና አላያትም። አቶ ሮበርት ሚስቱ ወይዘሮ ጊሴላ በመኪናቸው ውስጥ እንዳሉ ያ ግዙፍ መኪና ትንሹና መኪና በፎቶ ግራፉ እንደምታዩት ደፍጥጥዋት አለፈ።

ሮበርትና ሚስቱ የደረሰባቸው ጥቂት የአጥንት ስብራትና ቡጥጫ ለመታከም ሆስፒታል ገብተ ከተሻላቸው በኋላ ይህን ፎቶ ግራፍ ተነሱ። የመኪናቸውን አደፈጣጠጥ ስታዩ ከውስጡ ሰው ተፎ የሚውጣበት ይመስላችኋል?

***

# ነብዩ ሮበርት

በ1935 ዓ.ም ጥቅምት 18 ቀን በአሜሪካ አገር በሚልዋኡኪ የሚኖረው የሰባ ዓመቱ ሽማግሌ አርዝር ሮእብርት ወደ ከተማው ፖሊስ ጽሕፈት ቤት ሄዶ «በዚች ከተማ በቅርቡ ብዙ ቦምቦችና ዲማሚቶች ይፈነዳሉ፤ በዚሁም የተነሳ ሁለት ባንክ ቤቶችም የከተማው አዳራሽ ሲፈራርሱ ይታየኛል፤ አንድ ፖሊስ ጣቢያም ይፈርሳል፤ በመጨረሻው ከወንዙ በስተ ደቡብ አንድ ትልቅ ፈንጂ ትልቅ ጉዳት ያደርስና የመጨረሻው ይሆናል።» ብሎ ተናገረ።

የከተማው ፖሊሶች ሰላዮችና ጠባቂዎችን በየቦታው አሠማሩ። ይፈነዳባቸዋል በተባሉት ቦታዎች ሁሉ ጠባቂ ተደረገ ሮበርት በተናገረው በስምንተኛው ቀን የመጀመሪያው ፈንጂ ፈነዳ። ይህም የፈነዳ ዲማሚት የከተማውን አዳራሽ ፈጽሞ ደመሰሰው። በዚህም አደጋ ሁለት ልጆች ሲሞቱ ጥቂት ሰዎች ቆሰሉ።

ይህ አደጋ በደረሰ በማግስቱ ጥቅምት 27 ቀን ልክ ሮበርት እንደ ተናገረው የከተማው ሁለት ባንኮች በዲማሚት ፈረሱ። ሁለት የፖሊስ ጣቢያዎችም በቦምብ ተቃጠሉ። ይህ ሁሉ ሲሆን የከተማው ፖሊሶችና ሌሎችም ሆነው ይህን አደጋ የሚያደርሱትን ሰዎች በመፈለግ ላይ ነበሩ። ግን ምንም ፍንጭ ለማግኘት አልቻሉም። በዚህ ምክንያት ለዚያች ከተማ ጥፋት ምንም ርዳታ ለማድረስ ስላልቻሉ ሮበርት እንደተናገረው የከተማዋን የመጨረሻ ፈንጂ ይጠባበቁ ጀመር።

ይህን በቅጽል ስሙ ዶክ እየተባለ የሚጠራውንና መጪው ነገር የሚታየውን አርዝር ሮበርትን ፖሊሶች አስቀርበው ሌላ ደግሞ ምን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባቸውና የመጨረሻው ፈንጂ የትና መቼ እንደሚፈነዳ ጠየቁት። ሮበርትም «እሑድ ኅዳር 4 ቀን ከሜኖምኒ በስተ ደቡብ አንድ ትልቅ ፈንጂ ይፍነዳል፤ ከዚያ በኋላ የመጨረሻው ይሆናል» አላቸው።

የሚልዋኡኪ ፖሊሶች አደጋው ይደርሳል ወደ ተባለበት ቦታ ወደ ሞኖሞኒ ቀበሌ በጦር ትጥቅ የተደራጁ ወታደሮችን ላኩ። በዚያም ቀበሌ ሕዝቡ ሁሉ እንዲፈተሽና መንገደኛው ሁሉ ሳይበረበር እንዳይተላለፍ ተደረገ። ለፖሊሶች አልቆም ብሎ የሚሸሽ ቢገኝም በጥይት እንዲመታ ለወታደሮቹ ሙሉ ሥልጣን ተሰጣቸው። ይህ መደረጉ ቦምብ የሚጥሉ ሰዎች ቢኖሩ አላማቸውን ለማጨናገፍ ተብሎ ነው።

ሮበርት የተናገርበት የኅዳር 4 ቀኑ እሑድ ደረሰ። ጥበቃው እጅግ በጣም የጠበቀ ሆነ። ግማሽ ቀን ድረስ ማንም ሰው እንዳይላወስ ተደርጎ በሰላም ዋለ። ከተሰያት በኋላ ግን ከፍተኛ የሆነ ፈንጂ ፈነዳ። የፈንጂውን ድምፅ የሰሙ ከአሥራ ሦስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ያሉ ሰዎች ሁሉ ሁኔታውን ለማየት መጡ። ፈንጂውም ብዙ ሕንፃዎችን ሲያፈራርስ በሥራ ላይ ከተሰማሩት ወታደሮችም ጥቂቶቹን አቆሰለ።

ሮበርት እንዴት ሊያውቅ ቻለ? በጥንቆላ ወይስ በተአምር? በእግዚአብሔር ታምራዊ አፈጣጠር ነው። ሮበርት በ1866 ዓ.ም በዌልስ ውስጥ ደንቢ በተባለ ቦታ ተወለደ። አንደበቱ መናገር ቢችል የጠፉ ሰዎችንና ዕቃዎችን ያሉበትን ቦታ ይጠቁም ጀመር። ሮበርት ጥቂት እንኳ አልተማረም። ምክንያቱንም ሲገልጽ የተማርኩ እንደ ሆነ ይሄ ታላቅ ስጦታዬ ይጠፋብኛል ብዬ ነው ይላል። በቤቱ ውስጥ አንዲት ትንሽ ቢሮ ከፍቶ ምንም ነገር የጠፋባቸውና የሚፈልጉ ሰዎች እየመጡ እንዲያነጋግሩት አደረገ። በዚህም ሥስራ አምሳ ዓመት ሙሉ ሲያገለግል ኖረ።

አንድ ጊዜ በ1905 ዓ.ም በሐምሌ ወር ዱንካን ማክሪጎር የተባሉ በዊስኮንስኪ የፔስቲያን ነዋሪ የነበሩትና የታወቁት ታላቅ ሰው የደረሱበት ሳይታወቅ ጠፉ። በየቦታው ከፍተኛ ፍለጋ ተደርጎ የደረሱበት ጠፋ። አንድ ቀን የእኚሁ ታላቅ ሰው ሚስት ወደ ሮበርት ዘንድ ሄዱ። ገና ከቤቱ በር ሲደርሱ ሮበርት ብቅ ብሎ «ስላባልዎ ጉዳይ እንድነግርዎ ከፈለጉ ከሰዓት በኋላ ይመለሱ» አላቸው። ከቀትር በኋላ ሲመለሱ «ባለቤትዎ ተገድለዋል፤ ለእሳቸውም ሞት አላፊው ማን እንደሆነ ከሜኖሚኒ ወንዝ ረግረጉ ወስጥ ያገኙታል» አላቸው። ይሄው ነገር ለፖሊስ ተነግሮ ፖሊሶች ከረግረጉ ቢሔዱ የጠፉት ሰው ሬሳ ከረግረጉ ውስጥ ተወሽቆ ተገኘ።

አንድ ጊዜ ደግሞ አቶ ጂ. ዴ. ለሮይ የተባሉ የቺጋጎ ታላቅ ነጋዴ ወደ ሮበርት ዘንድ ሂደው «ወንድሜ ወደ አልቡክሪክ እሔዳለሁ ብሎ ሔዶ ነበር። ከሔደም ስድስት ወር ሆነው እስካሁን ድረስ የት እንደደረሰ አይታወቅምና፤ የት ይገኛል» ብለው ጠየቁ።

ሮበርትም «ወንድምዎ ተገድሏል፤ ገዳዮቹም ገድለው ሬሳውይን በአሪዞና ውስጥ ዴቪል ካንየን ከተባለው ቦታ ጥለውታል ከዚያ ያገኙታል» አላቸው። ለሮይም የወንድማቸውን ሬሳ ፍለጋ ከተነገራቸው ሥፍራ ቢሄዱ ልክ ሮበርት ካለበት ቦታ የወንድማቸውን ሬሳ አገኙ።

አንድ ጊዜ ደግሞ ሮበርት፤ ፈንድ ደ ላክ በሚባል በሆቴል በረንዳ ላይ ተቀምጦ ሳለ የፖሊስ ባለሥልጣኖች መጥተው አንድ ሰው የገደለ ሰው ከጠፋባቸው ሁለት ዓመት መሆኑንና ሊያገኙትም ያለመቻላቸውን ገለጹለት። ሮበርት ጥቂት ጊዜ ዓይኑን ጨፈን አድርጎ ከተቀመጠበት ተወዛዋዥ ወንበር ላይ እየተወዛወዘ «እስቲ ነገር እነግራችኋለሁ» አላቸው። በማግስቱ ወደ ፖሊስ ጣቢያው ሄዶ በዚያ ያሉትን ፎቶ ግራፎች ሁሉ እንዲሰጡት ጠየቀ። በተሰጡትም ፎቶ ግራፎች ላይ ጣቱን እያሳረፈ መመርመር ጀመረ። አንደኛው ፎቶ ግራፍ ላይ ሲደርስ አገኘሁት ብሎ ጮኸ። «ይሄ ነው ገዳዩ፤ እሱም በብሪትሽ ኮሎምቢያ ፈረሰኛ ፖሊስ ሆኖ ይሠራልና ከዚያ ብትሄዱ ታገኙታላችሁ» አላቸው። ፖሊሶቹም ከዚያ ከተባለው ቦታ ቢሔዱ ወንጀለኛውን አገኙት። ቢጠየቅም መግደሉን በትክክል አመነ።

በዚህ ዓይነት ብዙ ጊዜ ከፖሊሶች ጋር ሲሠራ ከኖረ በኋላ በ73 ዓመት ዕድሜው በ1935 ዓ.ም ለዚህ ሽማግሌ ክብር ተብሎ ብዙ ባለሥልጣኖች ባሉበት ታላቅ ግብዣ ተደረገለት። በግብዣው አጋማሽ ላይ ሮበርት ተነስቶ «ስላደረጋችሁልኝ ታላቅ ግብዣ በጣም አመሰግናለሁ፤ እስከዚህ ዕድሜዬ ድረስ እግዚአብሔር በሰጠኝ ጥበብ እናንተንና ሌሎችንም ሳገለግል ኖሬአለሁ፤ አሁንም ቢሆን እስከ ጥር 2 ቀን 1940 ዓ.ም ድረስ አብረን እንሠራለን፤ ከዚያ በኋላ ግን የለሁም አላቸው። ልክ ሮበርት እንደተናገረው ጥር 2 ቀን 1940 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።

አሁን በሚልዋኩኪ ከተማ ሮበርት ይኖርበ በነበረው ቤቱ ውስጥ የሠራቸው ሥራዎች ታሪኮች በፋይል እየተደረጉ ተቀምጠው ጎብኚዎች እንዲያነቡዋቸው ተደርገዋል። የሮበርት እውቀት በብዙ ሐኪሞች ተመርምሮ ውጤቱ የእግዚአብሔር ታምር በሚሉ ቃላት ተዘግቷል።

***

ከጥንታዊ የግሪክ ታሪክ ውስጥ የቴአጄኒስ ታሪክ ይገኛል። ቴአጄኒስ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ484 እስከ 462 ዓ.ዓ ድረስ የኖረ ሰው ነው። ቦክሰኛ ነበር። 2502 ጊዜ የቦክስ ግጥሚያ አድርጓል። በነዚህ ግጥሚያዎች ውስጥ 1083 ሰዎች ወይም ተጋጣሚዎቹን ገድሏል። በግጥሚያው በሙሉ ተሸንፎ አያውቅም ነበር።

***

# የውሀ ጠብታ

የውሃዋ አንዲት ጠብታ ውሃ ላይ ስወድቅ። ወድቃ ተንቦራጨቀች። የውሃዋ ጠብታ ውሃ ላይ ልወድቅ ነው። እንደ ገና ሽቅብ ወጣች። ቁልቁል መመለስ ጀመረች። በማረፍ ላይ ነች። የውሃ ጠብታ ውሀ ላይ ስትወድቅ እንዲህ ያለ መልክ እንደሚኖራት ያውቁ ኖሯል?

# ታምረኛው ቀዳጅ

ፍሪዝ አሪጎ በብራዚል ውስጥ አንድ ተራ ገበሬ ነው አልተማረምና አያነብም። አይጽፍም። አንድ ሰው በታመመ ጊዜ ግን ማንኛውንም በሽታ ኦፕሬሽን በማድረግ በሽታውን ያወጣል። አሪጎ በዚህ ሞያው በአገር ቤቱ ነዋሪ ዘንድ የተወደደና የተከበረ ሰው ነበር።

ዝናው ተዛምቶ ከተማ ደረሰ። የከተማ ሰዎችም ለሕክምና እያሉ ከዚያ ምንም ከማያውቅ ተራ ገበሬ ዘንድ ይሰበሰቡ ጀመር። ዝናው በመግነኑ በላቲን አሜሪካ ውስጥ ያሉ፤ ታዋቂ ሐኪሞች ሁሉ ተሰብስበው አሪጎንን ሊፈትኑት ተነሱ።

አንዲት የጡት ካንሰር የያዛትን ሴት አቀረቡ። ሴቲቱ በዘመናዊ ሕክምና ጥበብ ለመዳን የማትችል መሆንዋ ተረጋግጦ ሐኪሞቹ አይቻልም ብለው የወሰኑላትና የሞት ጊዜዋን የምትጠብቅ ነበረች። የሰበሰቡት ሐኪሞች «በል እስቲ ይቺን ሴት አድናትና ጥበብህን አሳየን» አሉት። አሪጎ ሴትዮዋን አግዳሚ ወንበር ላይ እንድትተኛ አደረገ። አንዳችም የማደንዘዣ መድሐኒት ሳያደርግላት ከጉያው አንድ ሽንኩርት መክተፊያ የመሰለ ቢላዋ አወጣና የሴትዮዋን ጡት ለሁለት ሸረከተው። ደሙ ተንቧለለ። አሪጎ በሚደማው ቦታ ላይ መዳፉን ሲጭን ደሙ በሙሉ ቀጥ አለ። ከዚያ በኋላ አሪጎ አንድ ቁራጭ ሥጋ ከጡትዋ ውስጥ አውጥቶ ዙሪያውን ከበው ለሚመለከቱት ሐኪሞች ሰጠ። በሽታው እሱ ነበር።

ከዚያ በኋላ አሪጎ ተራ መርፌ ከኪሱ አውቶ የሰነጠቀው ጡት መግጠም ጀመረ። ሲጨርስ ሴትዮዋን «በይ ተነሺና ወደ ቤትሽ ሂጂ» ብሎ አሰናበታት። ይህ ሁሉ ሥራ የተከናወነው በጥቂት ደቂቃዎች ነበር።

አሪጎ ከሴትዮዋ ጡት አውጥቶ የሰጣቸውን ሥጋ ሐኪሞቹ መርምረው በካንሰር በሽታ የተወረረ ሆኖ አገኙት። የሴትዮዋንም ደምና ሌላም ምርመራ እንዳጋጣሚ እርጉዝ ነበረችና «ልጅዋን በምትወልድበት ጊዜ ይህ ኦፕሬሽን የሆነው ጡት ወተት አይሠራም» ብለው ሐኪሞቹ አመኑ። የሴትዮዋን የመውለጃ ጊዜም ተጠባብቀው ሴትዮዋ ስትወድ ያ በአሪጎ ቢለዋ የተበተበተው ጡት እንደማንኛውም

ጤነኛ ሴት ጡት ወተት ሠርቶ አወጣ። በአንድ ተራና ባልተማረ ገበሬ የተደረገውን አፕሬሽን ሐኪሞችና ሳይንቲስቶቹ ሁሉ አደነቁ።

በብራዚል ዋና ከተማ በሳንፓውሎ የሕክምና ትምህርት ቤት ቃለ ትምህርት ሰጪ (ሌክቸረር) የሆኑት ዶክተር ሌክስ እንደ ገና የአሪጎን አፕሬሽን ለመፈተን ተነሱ።

አንድ በተፈጥሮው ዓይኑ የተበላሸበትና የታወረ ልጅ አለ። ልጁ ለፍሬዝ አሪጎ ቀረበ። አሪጎ ልጁን ጠረጴዛ ላይ አንጋለለውና ምንም ማደንዘዣ ሳያደርግ ከኪሱ እንደ መቀስ የተሠሩ ሚስማሮች አውጥቶ የልጁን ዓይን በስተኋላው ሸቅሽቆ ወጋውና ዓይኑን ጎለጎለው። ከልጁ ዓይን ደም በብዛት ወጣ። አሪጎ ከአጠገቡ ጥጥ አንስቶ ደሙን በጥጡ ሲነካው፤ ደሙ ቀጥ አለ። ከዚያ በኋላ አሪጎ ሚስማሩን ሲነቅልለት ልጁ አየ። ወዲያውም ተንሥቶ እየሮጠ ወደ አባቱ ጎተራ ዘንድ ሔደ። ይህ ሁሉ ሲሆን የልጁን ራስ ይዘው የነበሩት ዶክተር ሌክስ በጻፉት ሪፖርት «የገረመኝ አፕሬሽኑ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ማለቁ ነው» ብለዋል። የልጁም ዓይን ምርመራ ተደርጎለት መቶ በመቶ ትክክለኛ መሆኑ ሐኪሞች አረጋገጡ።

***

# መሬት ውስጥ ምን አለ?

በዘመናዊ ጥበብ ታሪክ ውስጥ ብዙ ሳይንቲስቶችን ግራ ካጋቡት የሰው ዘር ታሪኮች ውስጥ አንዱ የጂ ራኡል ደሪስ የርስ ነገር ነው። የረስየርስ መሬት ላይ ቆሞ መሬት ውስጥ ያለውን ነገር ማየት ይችል ነበር።

በ1940 ዓ.ም የደረስየስ ከታች አገጩ አካባቢ ክፉኛ ታሞ ለመታከም ወደ ሐኪም ቤት ሄደ። ከዚያም በሕመሙ ይሰቃይ ስለ ነበረ ሕመሙን እንዲረሳ ተብሎ የእንቅልፍ መድሐኒት ተሰጠው። በሽታው እያሰቃየው ስላስቸገረው ደረስየርስ አንድ ወር ሙሉ የእንቅልፍ መድሐኒት እየዋጠ ኖረ። ሕመሙ ጥቂት እንደተሻለው የአንድ ዘመዱን እርሻ ለመጎብኘት ወደ ኩቤክ ሄደ። ከዚያ ከዘመዱ ጋር ሆኖ በእርሻው ውስጥ እየተዘዋወሩ ሲጎበኙ «እርሻዬስ ደህና ነበር። ግን ለከብቶችና ለመስኖም የሚሆን ውሀ ስለሌለ ብዙ ችግር አለብኝ» ብሎ ባለ እርሻው ዘመዱ አጫወተው።

እንዲህ እየተጫወቱ ሲጓዙ ደረስየስ በድንገት አገጩን ታመመ። ወዲያውንም ለዚያ ዘመዱ «እንዴት አወቅህ ብለህ አትጠይቀኝ፤ እንዲህ ላለው ጥያቄ እኔም መልስ መስጠት አልችልም። ግን ከዚህ ከቆምኩበት መሬት ሥር ውሀ አለ። ውሀው ንጹህና በጣም ጥሩ ነው። ውሀው የሚገኘው ከሃያ ሦስት ሜትር በታች ነው። የሚፈሰውም በጥቁር አለት ድንጋይ ላይ ነው በሚቆፈርበት ጊዜ ጥቁሩ አለት ድንጋይ እንዳይነካ

ተእጥንቀቁ። አለቱ ትንሽ ከተሰበረ ውሀውን ታጣለህ» አለው። ከሦስት ሳምንት በኋላ ልክ ደረስዮስ ካመለከተበት ቦታ ላይ የጉድጓዱ ቁፋሮ ተጀምሮ ውሀው ወጣ። የጉድጓዱ ጥልቀትም ደረስዮስ ከተናገረው ጥልቅት አንድ ጫማ ብቻ ረዝሞ ተገኘ። ደረስዮስ እንዳለው አለቱ ድንጋይ ስለተገኘ እንዳይሰበር በጥንቃቄ እየተቆፈረ የጉድጓዱ ውሀ በሰፊው እንዲወጣ ተደረገ።

የደረስዮስ ዝና ገነነ። የጉድጓድ ውሀ የሚፈልጉ ሰዎች ሁሉ ጥሪ ስላብዙለት መልካም ሥራ አገኘ። በጠቆመውም ሥፍራ ሁሉ ያለመሳሳት ስድስት መቶ ጉድጓዶች ተቆፍረው ውሀ ወጣ የካናዳ መንግሥት ባዘዘው መሠረት ያገሩ ታላላቅ ሳይንቲስቶች ሁኔታውን እንዲያጠኑ ተደረገ። ግን አንድም ውጤት ሊያገኙ አልቻሉም።

በደቡብ ሕንድ በባንጋሎር ይኖሩ የነበሩ አቶ ጃባር የተባሉም ሰው ውሀ ያለበትን ቦታ ያውቁ ነበር። እኚህ ስልሳ ዓመት ዕድሜ ያላቸው አዛውንት ውሀ በማግኘት ተግባር ሰላሳ አምስት ዓመታ ሙሉ አገልግለዋል። በሺ የሚቆጠሩ ጉድጓዶችም ተቆፍረው በጥቅም ላይ ውለዋል። ሽማግሌው ውሀ ከሚፈለግበት ቦታ ይሄዱና በሥፍራው ይዘዋወራሉ። ውሀ ካለበት መሬት ሲደርሱ ይንዘፈዘፋሉ። በዚህ ጊዜ ቶሎ ብለው ወንበር ያቀርቡላቸውና ያስቀምጧቸዋል። በዚያች ቦታ ላይም ተቀምጠው ጥቂት ሕክምና ይደረግላቸዋል። ለሕክምናው የተያዙላቸው ወፋፍራም ጨርቆች ውሀ ውስጥ እየተነከሩ ግንባራቸውና ማጅራታቸው ላይ ይደረጉላቸዋል። ቀጥለውም ጥቂት ትኩስ ሻይ ከጠጡ በኋላ ጤናቸው ይመለስና ተነስተው ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ። አቶ ጃባር ይህን ተግባር የሚፈጽሙት በነፃ ነበር እንጂ አንድ ጊዜም ለውሀ ማግኘት ሥራቸው ገንዘብ ተቀብለው አያውቁም። ስለዚሁም ጉዳይ ሲናገሩ «አላህ ለሰጠኝ ጥበብ እንዴት አድርጌ ገንዘብ እቀበላለሁ? አላህ በነፃ የሰጠኝን እውቀት እኔ ደግሞ በነፃ መስጠትና ማገልገል አለብኝ» ይላሉ።

ቤጂ ቤከር የተባለ ሰውም የውሀ ማግኘት ችሎታ ነበረው። በ1951 ዓ.ም የጄኔራልስ ሞተር ኩባንያ በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ሪፖርት ኤልሳቤጥ በሚባለው የወደብ ከተማ ፋብሪካ አቋቋመ። ግን በአገሪቱ የውሃ እጥረት ስላለ ለፋብሪካው ችግር እንደሚፈጥር ታውቆ ጉድጓዶች እየተቆፈሩ ውሃ እንዲፈለግ ተደረገ። ሊቃውንት በምርመራ ውሃ ይገኝበታል የሚሉ ቦታ ሁሉ በብዙ ውጪ እየተቆፈረ ውሃ ይታጣ ጀመር። የኩባንያው መሐንዲሶች ተስፋ ባለመቁረጥ በየቦታው ሲቆፍሩ ከአንደኛው ጉድጓድ ዘንድ ቀርቦ «አሁን ከዚህ ከምትቆፍሩት ጉድጓድ አምሳ ሜትር ያህል ከቆፈራችሁ በኋላ ጥቂት ውሃ ታገኛላችሁ፤ ግን ውሃው በጨው ውሃ ነውና አይጥቅማችሁም» አላቸው። እውነትም አምሳ ሜትር ያህል ከቆፈሩ በኋላ ውሃ ተገኘ። ግን የተገኘው ውሃ ቤከር እንዳለው የጨው ውሃ ሆነ።

የኩባንያው ሹማምንት ተሰብስበው «ቤከር ከመሬት ውስጥ ያለው ውሃ ጨው መሆኑን ማወቅ ከቻለ ጥሩ ውሃ ያለበትን ለምን አይጠቁመንም?» ብለው መከሩ። ወዲያው በእሱ መሪነት እሱ ከሚያዝበት ቦታ ጉድጓድ ለመቆፈር መወሰናቸውን ነገሩት።

ቤከርም እንግዲያውስ በሉ እንሂድ ብሎ ውሃ ፍለጋ ጉዞ ጀመሩ። ባለሥልጣኖቹ እየእከተሉት፤ እሱ እየመራ ሲሄድ ቤከር በድንገት ቆሞ ጥርሱን ያንገጫግጭ ጀመር። አካሉ ሁሉ ተንዘፈዘፈ። ወዲያው «ከዚች ከቆምኩባት ሥር ጥሩ ውሃ አለ፤ ውሃውም ብዙ ስለሆነ ለሥራችን በቂ ነው» ብሎ ተናገረ። የኩባንያው ሹማምንት አላመኑም። «እንዴት አንድ ደደብ ገጠሬ በነገረን ተማምነን ብዙ ገንዘብ በመክሰር ጉድጓድ እንቆፍራለን?» አሉ። ብዙ ከተከራከሩ በኋላ የቤከርን ትንቢት ለማረጋገጥ ብለው ቤከር እንዳያይ ዓይኑን አሥረው እንደገና ምርመራውን እንዲጀምር ነገሩት። ቤከርም እሺ እንዳላችሁት ብሎ ተስማማ።

ቤከር ዓይኑን ታስሮ ወደ ሌላ ሥፍራ ተወሰደና በጭፍኑ ውሃው የሚገኝበትን ቦታ እንዲፈለግ ነገሩት። ቤከር ጉዞውን ቀጥሎ ከዚያች በፊቱኑ ካሳያቸው ቦታ ላይ ሲደርስ ቆሞ «ይሄው ከዚች ቦታ ሥር ነው ውሃ ያለው» አላቸው። ከዚያ በኋላ ከጉድጓዱ መቆፈር ተጀመረ። ቁፋሮው ሲያልቅ፤ ውሃው ወጣ። ለኩባንያው በቂ ከመሆን አልፎም ለአካባቢዎቹ ገበሬዎች ሰብልና አትክልት ሁሉ ለማጠጣት በቂ በመሆኑ፤ ያ ሠፈር ከበረሃነት ወደ አረንጓዴነት ተለወጠ።

የጄኔራል ሞተርስ ኩባንያ ሠራተኞች በመጽሔታቸው ላይ በ1951 ዓ.ም በጥቅምት ወር እትም የቤከርን ታሪክ አትመውት ነበር። ቤከር ለመጽሔቱ አዘጋጅ በሰጠው ሐተታ «በአንድ እጄ ከብር የተሠራ ቤሳ፤ በአንድ እጄ ደግሞ ከመዳብ የተሠራ ቤሳ ይዤ ስሔድ ጥሩ ውሃ ካለበት ቦታ ስደርስ የብሩ ቤሳ በእጄ ውስጥ እንዳለ ይንቀጠቀጣል። ውሃው ጨው ያለበት የሆነ እንደሆነ የመዳቡ ቤሳ ይንቀጠቀጣል። ይሄ እንግዲህ እንዴት እንደሆነ አላውቅም» ብሏል።

***

በአቴን ከተማ አንድ ጥንታዊ የሆነ ቤተ ክርስቲያን አለ። ከተማዋ በዘመናዊነት እያደገች ስትሔድ ያ ቤተ ክርስቲያን ባለበት ሥፍራ ታላቅ ሥፍራ ለመሥራት ታሰበ። ቤተ ክርስቲያኑን ለማፍረስ ጥንታዊና ታሪካዊ በመሆኑ አጓጓ። በሕንጻው ግን ሕንጻ መሥራት በግድ አስፈላጊ ስለሆነ ቤተ ክርስቲያኑ ባለበት እንደ ሆነ ግዙፉ ሕንጻ በላዩ ላይ ተሠራ። የቤተ ክርስቲያኑ በር ከሕንጻው ውጪ በመሆኑ ተሳላሚዎችና ጎብኚዎች ያለ ችግር መግባትና መውጣት ይችላሉ።

***

# ሌላዎቹ ፍጡራን

በሰሜናዊ እንግላንድ ካርልስ በሚባል ቦታ የምትኖር ጂም ቶምፒልተን የምትባል ልጅ ሰኔ 4 ቀን 1964 ዓ.ም ከአባትዋ ጋር ሆና ለሽርሽር ባህር ካለበት ቦታ ሄዱ። በዚያ በባህሩ ቦታ ሲጫወቱ አባትዮው ልጅነቱን ፎቶ ግራፍ አነሱዋት። ፎቶ ግራፉ ሲታጠብ፤ ሌላ ስዕል ተደርቦበት ታየ። ልጅቱ ፎቶ ግራፉን በተነሳች ጊዜ በዚያ አካባቢ ከልጅቱና ከአባትዋ በቀር አንድም ሰው አልነበረምና ይሄ የሌላ ሰው ስዕል ከየት እንደመጣ አስደነቀ። ይህም ፎቶ ግራፍዎች ከተመረመረ በኋላ አብረው የተነሱት ነገሮች ማርስ ከምትባለው ፕላኔት የመጡ ናቸው የሚል ጥርጣሬ አሳደረ።

እነዚህ ከማርስ ላይ የመጡ አንቸው የተባሉት ነገሮች ልጅና አባት ከባህሩ አጠገብ በነበሩበት ጊዜ ፈጽሞ አላዩዋቸውም ነበር። ፍጥረቶቹ የማይታዩ ሆነው እንደሚወርዱም መርማሪዎቹ አረጋገጡ።

ሌላም ታሪኮች አሉ። በሚቀጥሉት ገጾች ላይ ደግሞ ሌላ ሌላዎቹን ታሪኮች ያነባሉ።

ባርኒ ኤንድ ቤቲ ሄል የተባሉ ባልና ሚስት የሆኑ ሰዎች በአሜሪካ አገር ፖርት ስሙዝ በተባለ ቀበሌ ይኖሩ ነበር። መስከረም 19 ቀን 61 ዓ.ም ወደ ቤታቸው ሲሄዱ አንድ ቀይ መብራት ያለው ነገር ወደ እነሱ አቅጣጫ ሲመጣ አዩ። ወዲያው ይሄ መንኮራኩር ከእነሱ ዘንድ ደርሶ ይዞአቸው ሄደ። እነዚህ ባልና ሚስት ከሄዱበት ቦታ ከተመለሱ ያዩትን ነገር ሁሉ ለባለሥልጣኖች አሳወቁ። ባለሥልጣኖቹ ጉዳዩን አናምንም ስላሉ እነዚያን ሄደን መጣን ያሉትን ሰዎች በማፍዘዣ አፍዘው በልባቸው ውስጥ ያለውን ነገር እንዲናገሩ አደረጉዋቸው።

እነዚህም ሰዎች ከፈዘዙ በኋላ ያንኑ መጀመሪያ የተናገሩትን «ዲስኩ ቀይ መብራት እያበራ ወደ እኛ መታ፤ ከዚያም በዚያም ከሄድንበት ዓለም ውጪ ሄድን ከዚያም ከሄድንበት ዓለም ከጥሩ ማረፊያ ቦታ አሳርፈውን እንደገና ወደዚሁ ወደ መሬት መልሰው አመጡን።» በማለት አንድ ባንድ ዘርዝረው ተናገሩ። እንዲያውም መንኮራኮሩ ውስጥ ያለውን መሣሪያ እንዴት አድርጎ በአውቶማቲክ እንደሚሠራ ሁሉ ዘርዝረው አስረዱ።

አቶ ጆርጅ አደምስ በሁፎሎጂያ ትምህርት የበሰለ እውቀት ያላቸው ከሰማይ በወረደ መንኮራኩር ውስጥ ገብተው ወደማያውቁት ዓለም ተወስደው ተመልሰዋል።

እኚህ ሊቅ ሲናገሩ «መንኮራኩሩ ወደኔ አቅጣጫ ሲመጣ አይቼ ፎቶ ግራፍ አነሳሁት። ከዚያም በመንኮራኩሩ ውስጥ አስገብተውኝ ወደማላውቀው ዓለም ወስደው መለሱኝ።» ሲሉ አስረድተዋል። «የሄዱበት ዲስክ ምን መሣይ ነው?» የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸዋ «ይሄውላችሁ ያነሳሁት ፎቶ ግራፍ ብለው በመኮራኮርዋ ከመሄዳቸው በፊት ያነሱትን የመኮራኩር ፎቶ ግራፍ አሳይተዋል። እኚህ ሊቅ ስለዚሁ ወደማያውቁት ዓለም ስለወሰዳቸው መንኮራኮር ታሪክ ሦስት ዓይነት መጽሐፍ ጽፈዋል። አንዱ መጽሐፋቸው ስሙ «ተሽከርካሪው መሬት አረፈ» የሚባል ሲሆን የሁለተኛው መጽሐፋቸው ስም ደግሞ «በአንድ መንኮራኩር ውስጥ» የሚባል ነው። የሦስተኛው መጽሐፋቸው ስም «ደህና ሁኑ መንኮራኩርዋ ተሽከረከረች» የሚባል ነው።

እኚህ ሊቅ ከሌላ ዓለም መጥተው ስለወሰዱዋቸው ሰዎች አስተያየት ሲሰጡ «እነዚህ ሰዎች ከሌላ ዓለም እየመጡ መመለሳቸው የታወቀ ነገር ነው፤ ይቺን የኛ ዓለም የሆነችው መሬት ለእነሱ እንደሽርሽር መሄጃቸው ቦታ አድርገዋታል» ብለዋል።

እነኚህ ከመሬት ውጭ ከሆነ ዓለም ይመጣሉ እይሚባሉት ሰዎች አንድ ጊዜ በአሜሪካ አገር በሜክሲኮ ተይዘው ነበር። በሜክሲኮ እስቴክ በተባለ ቀበሌ በ1949 ዓ.ም በመንኮራኩር ሆነው ከሌላ ዓለም የመጡ ሰዎች ተያዙ። እንደተያዙ አንደኛው አመለጠ። አንደኛው ግን ፖሊሶች የተያዘውን ፍጡርና መንኮራኩሩን በካሚዮን ጭነው ወስደው በሚስጢር ከአንድ ከማይታወቅ ቦታ ቀበሩዋቸው። ለምን እንዲያ እንዳደረጉም ሲናገሩ፤ «ይሄ ከላይ የወረደ እየግዜር ቁጣ ስለሆነ ሰው የሰማ እንደሆነ ይደነግጣል፤ ወይም ይሸበራል ብለን ማንም ሳያየው በሚስጢር ቀበርነው» ብለዋል። ፎቶ ግራፉ ላይ የምታዩት ከመሬት ውጪ ከሆነ ዓለም እይመጣው ሰው በሚስጢር በፖሊሶች ተይዞ ነው። የተያዘው ሰው ፖሊስቹ ግራና ቀኝ ሆነው እጅና እጁን የያዙት ነው፡

እንዲህ ዓይነቱ ነገር እየደጋገመ በመሄዱና ሔደን ተመለስን የሚሉም የመሬት ሰዎች ስለበዙ በአሜሪካ አገር ይህን ነገር የሚከታተሉ ብዙ ድርጅቶች ተቋቋሙ። በነዚያም ድርጅቶች ውስጥ ከሰላሳ ሚሊዮን የሚበልጡ ሰዎች አባል ሆነዋል። ይሄን ነገር ለማጥናትና ለመመራመር እያሉ ለድርጅቱ በየወሩ አምስት አምስት የአሜሪካ ብር እየከፈሉ ነገሩን የሚያጠኑ ሰዎችም አሉ። ከእነኚህ አባሎች ውስጥም አንድ ሺ አምስት መቶ የሚሆኑት ሰዎች ከሌላ ዓለም በመጣ መንኮራኩር ወደ ሌላ ዓለም ሄደው የተመለሱ ናቸው።

እነኚህ ከመሬት ወደ ሌላ ዓለም ሄደው የተመለሱ ሰዎች ስለወሰዱዋቸውና ስለመለሱዋቸው ሰዎች ሁኔታ ብዙ ነገሮችን ይናገራሉ። የወሰዱዋቸው ሰዎች መልክ ምን ይመስላል? ሲሏቸው ስዕል እየሳሉ የወሰዱዋቸውንና የሄዱበትንም ዓለም

የሚኖሩበትን ሰዎች መልክና ሁኔታ ያስረዳሉ እየሳሉ ካሳዩዋቸው ስዕሎች መካከል ጥቂቶችን አውጥቻቸዋለሁ። ሰዎቹ ስዕሎቹን የሳሉዋቸው በልዩ ልዩ ቀለም ነው። በዚህ የታተመው ግን በጥቁር ብቻ በአንድ ቀለም ስለሆነ ውበት ቀንሰዋል።

እንዲህ ያለው ነገር ብዙ አገሮችን እንዳጣላና ብዙ ሊቃውንትም ለብዙ ጊዜ አከራክርዋል። አሁንም ቢሆን ብዙ ሊቃውንት እንደሌለ አድርገውም ይከራከራሉ። ግን ብዙ ጊዜ የሚታዩት በራሪ ዲስኮች ከየት ይመጣሉ? ለሚለው ጥያቄ መልስ አይሰጡም። በአሜሪካ አገር ግን ufo የተባለው ድርጅት ነገሩን በሰፊው በመከታተል ላይ ነው። ምን እንደሆኑና ከየት እንደሚመጡ ያልታወቁና እስካሁን ሊቃውንትን በአሳብና በምርምር ብዙ እንዲህ ያሉ ነገሮች አሉ። የኛ አገር አንባቢዎች ነገሩን እንዲያውቁት ያህል ታሪኩን ሳላበዛ ባጫጭሩ ጥቂት ላውራ።

የታላቁን አሌክሳንደር ታሪክ ስናነብ «.....ጦረኛው ዝሆኑም ፈረሱም እግረኛው ወታደር ሁሉ ወንዙን ለመሻገር አቃተው ምክንያቱም ከወንዙ ወዲያ ማዶ የብር ጋሻ የመሰለ አብረቅራቂ ነገር በሰማዩ ላይ ይታይ ስለ ነበር ፈተው ነው። ያ በአየር ላይ የነበረው ተንሳፋፊ አብረቅራቂ ነገር በዙርያ ክቡ ባሉ ቀዳዳዎች እሳት ይተፋል። ..... ይህ ከሰማይ ወጣ።......» የሚል አረፍተ ነገር አለ። ያ አብረቅራቂ ነገር ከየት መጣ?

በቴክሳስ ውስጥ ቦንሃም በተባለ ቦታ በ1873 ዓ.ም ገበሬዎች በጥጥ እርሻቸው ውስጥ ሲሠሩ የሚያብረቀርቅ ብርማ መልክ ያለው ነገር ከሰማይ በቀጥታ ወደ እነሱ ሲመጣ እዩ። እነሱ በመውረዱ በአካባቢው ያሉ ከብቶችና ፈረሶች ደንብረው ሸሹ። ጋሪ ይነዳ የነበረው ገበሬም ፈረሶች ደንብረው ጋሪው በመገልበጡ ጋሪ ነጂው ተጨፍልቆ ሞተ።

ይህ ነገር በሆነበት ቀን በዚያው በቴክሳስ ውስጥ ፎርት ሪሌይ በተባለ ቦታ ፈረሰኛ ጦር ሠራዊት በሠልፍ ሆኖ ልምምድ በሚያደርግበት ጊዜ ያው ነገር ከሰማይ በመውረዱና ከሠልፈኛው ፈረሰኛ አጠገብ በመድረሱ ፈረሶቹ በሙሉ ደንብረው የሠልፉ ዝግጅት መቋረጡን አዛዡ በጻፈው ሪፖርት ገልጿል።

ሚያዝያ 9 ቀን 1897 ዓ.ም በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሰዎች አንድ ከሰማይ የወረደ ነገር አይተዋል። ይህም ነገር ሰባት ቀንና ለሊት በአንድ ቦታ ሆኖ ቆይቷል። አጉልቶ በሚያሳይ መነጥር (በቴሌስኮፕ) የተመለከቱት ሊቃውንት እንደ ተናገሩት፤ ቅርጹ እይሲጋር (በትንባሆ የሚጠቀለለው ትንባሆ) ዓይነት ነው ብለዋል። ቅርጽ የሲጋራ ዓይነት ሆኖ በጎንና ጎኑ መለስተኛ ክንፎች ወይም ቅጥያዎች እንዳሉትም ተናግርዋል። ይህ ነገር ማታ ማታ አረንጓዴ፤ ቀይና ነጭ ብርሃን ያበራል። ሚያዝያ 16 ዴንቬር ድረስ ያሉ ሰዎች ያለ ምንም ችግር ቀንና ለሊት ይመለከቱት ነበር።

ይህ መሣሪያ ሚያዝያ 16 ቀን ወደመጣበት ተመልሶ ከምድረ ገጽ አልጠፋም። ሚያዝያ 19 ቀን በዚያው ዓመት ምሕረት በ1897 በአሜሪካ አገር በምዕራብ ቪርጂንያ ውስጥ ሲስተርስቫሌ በተባለው ከተማ ላይ ለሊት እያፏጨ አንዣቧል። ተኝተው የነበሩት የከተማዋ ሰዎች በፉጨቱ ምክንያት ተደናግጠው በየጎዳናው ላይ እየወጡ መሣሪያውን አይተውታል። መሣሪያውም በከተማዋ ላይ እያንዣበበ በዞረበት ጊዜ መሣሪያው ያበራው ብርሃን ጨለማውን ገፍፎ ልክ እኩለ ቀን አስመስሎት እንደ ነበር፤ ነዋሪዎቹ ተናግረዋል። በዚያች ከተማ ያዩት ሊቃውንት እንደተናገሩት የመሣሪያው ርዝመት ሰማንያ ሜትር ያህል ሆኖ በአረንጓዴና በቀይ መብራቶች የተከበበ ነው ብለዋል። ይህ መሣሪያ አሥር ደቂቃ ያህል በዚያች ከተማ ላይ ከቆየ በኋላ ከተማዋን በብርሃን ያጥለቀለቃትን ትልቁን ነጭ ብርሃን አጥፍቶ ጉዞውን ወደ ሰማይ ቀጠለ።

በ1910 ዓ.ም በየካቲት ወር ካታኖጋ በተባለች ከተማ የዚያው መሣሪያ ዓይነት ታይቷል። ይሄኛው መሣሪያ ቁመቱ አርባ ሜትር ያህል ሲሆን ቅርጹ ግን እንደዚያኛው ሲጋር መሣይ ነው። እንደዚያኛው ክንፍ እንደሌላውም ሊቃውንቱ ተናግረዋል።

አሁን በአሜሪካ አገር በኦሪጎን ውስጥ ማክሚንቫሌ በተባለ ቀበሌ ግንቦት 11 ቀን 1950 ዓ.ም አቶ ፓውል ትሬንት ከሚስታቸው ጋር ከቤት ተቀምጠው ነበር። ጊዜው መሸቶ ውሾች ሰዓት ተኩል ሆንዋል። በጓሯቸው ያሉዋቸውን ጥንቸሎች ውሾች ከቤታቸው እያወጡ ስለሚበሉባቸው ጫጫታ ነገር ሰሙና፤ አቶ ፓውል ጥንቸሎቹን እንደ ገና ውሾች የረበሹዋቸው መስሎአቸው ከቤት ወጡ። ከቤት እንደ ወጡ ካንድ ቦታ ቆመው ቀሩ። ጥንቸሎቹ ካሉበት በረት አለፍ ብሎ በመሐሉ አየር አይተው የማያቁትን ነገር አዩ። ድብልብል ነገር ነው። ከሥር ግን፤ ጠፍጣፋ ነው። ድምፅ የለውም። እንዲያው ብቻ ዝም ብሎ በባህር ላይ እንደሚዋዥቅ ጀልባ ካንድ ቦታ ቆሞ በአየርዋ ላይ ይዋዥቃል። ያ ነገር ከመሬት ቢያንስ ሰላሳ ሜትር ያህል ከፍ ያለ ነው።

ሚስቲቱ ባላቸው ሲቆዩ ጊዜ ምን ነካው ብለው ከቤት ወጣ አሉ። ባልዮውን እንደ ጅብራ ተገትረው አዩዋቸው። አሻግረው ቢመለከቱ ያን ነገር አዩት። ቶሎ ብለው ገብተው ፎቶ ግራፍ ማንሻቸውን ይዘው ወጡ። ሚስትዮዋ ፎቶ ግራፍ ማንሻቸውን ይዘው ሲወጡ ያ ድብልብል ነገር ለመሔድ ጉዞ ሲጀምር አዩት። ሆኖም ሳያመልጣቸው ቶሎ ብለው ፎቶ ግራፍ አነሱት። ታሪኩን ላሳጥርና ወይዘሮ ፓውል ያነሱትን ፎቶ ግራፍ ላይፍ የተባለው መጽሔት አወጣው። ከዚያ በኋላ በመላው ዓለም ጋዜጣና ቴሌቪዢኖች ፎቶ ግራፉ ታየ። የዚያን ዓይነት ነገር ፎቶ ግራፍ ካነሱ ሰዎች ሁሉ በሲቪል ደረጃ የወይዘሮ ፓውልን የሚወዳደር አልተገኘም።

ይህ ነገር ከሆነ የወይዘሮ ፓውልን የሚወዳደር አልተገኘም ዊልስ ስፐሬይ የተባሉ ከአሥራ ዘጠኝ ቀናት በኋላ ለካፐቴኑ ፐላን ከዋሽንግተን አይሮፕላን ነጂ ትልቁ D.C 6 አይሮፕላን ከዋሽንግተን አይሮፕላን ጣቢያ አስነስተው ወደ ቱልሳራል ጉዞ

ጀመሩ። ያ ግዙፍ አይሮፕላን በሰዓት 170 ማይልስ ይበራል። በቨርጂኒያ ውስጥ ማውንት ቬርኖን ከተባለው ቦታ ሲደርሱ ከፊታቸው አንድ ነገር መደንቀሩን አዩ። ካፒቴኑ ቶሎ በልው አይሮፕላኑን ዘቀዙና በዚያ ነገር ሥር አለፉ። ጥቂት እንደሔዱ ደብዘዝ ባለችው የጨረቃ ብርሃን ውስጥ ያ ግዙፍ ነገር ከአይሮፕላኑ ግራ በኩል ሆኖ ከአይሮፕላኑ ጎን ይጓዝ ጀመር።

ካፒቴኑ ወደ ዋሽንግተን መልእክት አስተላለፉ። «ብርሃን የሌለው ተዋጊ አይሮፕላን ነው? ወይስ ምንድነው?» ብለው ጠየቁ። በዋሽንግተን ያሉ ጠቢባን ያን ነገር ራዳር ተመልከቱ። ይህንንም ለካፒቴን ስፒሬይ ነገሩ። ራዳሩ ግን ያለማቋረጥ ያን ግዙፍ አይሮፕላንና ያን ግዙፍ ነገር እንዲከታተል አደረጉ። ያም ነገር የአይሮፕላኑ ዙርያ በክቡ ይዞረው ጀመር በዚህ ጊዜ የአይሮፕላአኑ ነጂዎች ያን ነገር በጥሩ ሁኔታ ለማየት ቻሉ። ካፒቴን ስፒሬይ ወደ ዋሽንግተን ዜናውን ሲያስተላልፉ «......ነገሩ አይሮፕላን አይደለም፤ ከዚህ በፊት አይቼውና ሰምቼው የማላውቀው ነገር ነው። እንደምናየው አነስተኛ የባሕር ውስጥ መርከብ (ሰብመሪን) ይመስላል።......» አሉ። ይህን መልእክት ባስተላለፉ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ያ ነገር ኃይለኛ ድምፅ አሰምቶ ከአይሮፕላኑ አጠገብ ጠፋ።

በ1955 ዓ.ም ነሐሴ 15 ቀን በአሜሪካ አገር ከኢንቱኪ ውስጥ ሆፕኪንስቫሌ በተባለ መንደር የምድር ሰዎች ከሌላ ፍጡራን ጋር ጦርነት ገጥመው ነበር። ገበሬው አቶ ቼቺሊ ሰተን ወደ ማታ ገደማ ወደ ከተማዋ ፖሊስ አዛዥ ዘንድ ሔደው ለፖሊሱ አዛዥ ለግሪንዌል ሲያመለክቱ «......አረንጓዴ መልክ ያላቸው ሰዎች መጥተው ተኩስ ገጠሙን። እኛም ለአንድ ሰዓት ያህል ተታኩሰን መለስናቸው» አሉ። የፖሊሱ አዛዥ መሣሪያ የያዙ ፖሊሶችንና ነገሩን የሚመረምሩ ሰዎች ይዘው ከሆፕኪንስቫሌ ዘጠኝ ማይል ያህል ወደምትርተው ኬሊ አምባ ሔዱ። በዚያም ምንም ነግር ስላላገኙ የፖሊሱ አዛዥ አቤቱታ የነገራቸው አቶ ሱተን ሰክሮ የቀባጠረ መሰላችው። ደግሞም አቶ ሱተን በዕድሜያቸው ሙሉ ከቡና በስተቀር አልኮልነት ያለው ነገር ቀምሶ እንደማያውቅ ያውቁ ነበርና ነገሩ ግራ ገባቸው። ጥቂት ሰዎችን ከአቶ ቺቺሊ ስተን ቤት ትተው ተመለሱ።

በአቶ ቼቺሊ ሰተን ቤት ሚስትዮዋ፤ ጠባቂዎቹና ሌሎች ጓደኞቻቸው የዚያኑ ዕለት ለሊት ተቀምጠው ሲጫወቱ አንድ በራሪ ነገር ከቤት ጥቂት እልፍ ብሎ ሲያርፍ አዩት። ከውስጡም አሥራ ሁለት ያህል የሚሆኑ አጫጭር ሰዎች መሣሪያ ይዘው ወጡ። ወደ ገበሬው ቤትም አመሩ። የነዚያ ከመሣሪያው ውስጥ የወጡ ሰዎች ቁመት ከአንድ ሜትር ከሩብ አይበልጥም። ዓይናቸው ድብልብል ነው፤ በጊዜው ከሩቅ ይታያል። እጆቻቸው ረጃጅሞች ናቸው። በጣቶቻቸው ላይ ያሉት ጥፍሮቻቸው ከጫፎቻቸው እንደ መርፌ የሾሉ ናቸው። ጆሮአቸው የድመት ጆሮ ይመስላል፡

እነዚህ ሰዎች ከመሣሪያው ውስጥ ወርደው ወደ አቶ ቼቺሊ ሰተን ቤት ሲያመሩ መጀመሪያ ያዩዋቸው ያቶ ቼቺሊ ሰተን ጓደኛ አቶ ቢሊ ቴለር ናቸው። አቶ ቴለር «መጡላችሁ» ብለው እንደ ተናገሩ ሰዎቹ ከቤቱ አጠገብ ደረሱ። በቤቱ ውስጥ ያሉ ሰዎች ሴቶች ቤቱን እንዲቆፉና ልጆችን ይዘው ከጓዳ እንዲከተቱ አዘዙ በየመስኮቱ ላይ ሆነው ከነኛ አዲስ መጤ ሰዎች ጋር ተኩስ ገጠሙ። አቶ ሰተን በመጀመሪያ አንዱን አጭር ፍጡር መትተው ወደ ኋላ ጣሉት። አቶ ሰተን ገደልኩ ብለው ሲደሰቱ ሌላው ፍጡር በጣሪያ ገብቶ የአቶ ሰተንን ጓደኛ የአቶ ቴለርን ጠጉር ይዞ በጣሪያ ሊያወጣቸው ሽቅብ ይጎትት ጀመር። ሰተን ቶሎ ብለው ተኩሰው ያን ፍጡር መቱት። ጥይቷ ግን በደረትይ ሾልካ ሔደች። ፍጡሮቹ በጥይት ሲመጡ ይወድቃሉ። ግን ወዲያውኑ ተነስተው ይቆማሉ።

ጦርነቱ ለሦስት ሰዓትታ ያህል ተካሄደ። የመሬት ሰዎች፤ እኛ የምናውቀውን ጥይት ይተኩሳሉ። እነኛ ከየት እንደመጡ የማይታወቁት ፍጥረቶች ደግሞ ብርሃን የሆነ ነገር ይተኩሳሉ። ከእነኛ ፍጡራን የሚተኮሰው ጨረር በመሬት ሰዎች ላይ ሲያርፍ ለጥቂት ግዚኤ ከማፍዘዝ በስተቀር አይጎዳም። ኍልቱም ወገኖች ያንዱ ሌላውን በማይጎዳ መሣሪያ ሲታኮሱ ከቆዩ በኋላ ጦርነቱ ጋብ አለ። በዚህ ጊዜ አቶ ቼቺሊ ሰተን ቶሎ ብለው መኪናቸውን አስነስተው ርዳታ ጥየቃ ወደ ከተማ ሔዱ።

ከአቶ ቼቺሊ ሰተን ጋር የፖሊሱ አዛዥ ግሪንዌልና ሌሎችም ሆነው ከቦታው ደረሱ። ግን ምንም ነገር ሊያገኙ አልቻሉም። ከቤት ሲገቡ ሴቶች በፍርሃት ሲንቀጠቀጡ፤ ሕፃናት ሲያለቅሱና ጠባቂዎቹ በቤቱ ዙርያ በየመስኮቱ ላይ ጠመንጃቸውን ደግነው ሲጠባበቁ መጤዎቹ ፖሊሶች ተመለከቱ። ከዚህ በኋላ ሁሉም ከዚያው ሲጠባበቁ አደሩ። አንዳንድ ጊዜ በሰማይ ላይ የሚዞር ብርሃን ወይም መብራት ከማየታቸው በስተቀር ሌላ ጦርነት ሳይጋጠሙ ነጋ። ነገሩ አስጊ በመሆኑም አቶ ቼቺሊ ሰተን ያን የእርሻ ቦታቸውን ትተው ተሳደዱ።

እነኛ ሰው መሣይ ፍጡራን ከየት መጡ? መልስ ያልተገኘለት የሊቃውንት ሁል ጥያቄ ነው።

***

ወይዘሮ ቪአሌት ስቴቨንስ ዓይናቸውን ከታወሩ ሃያ ዓመት አልፏቸዋል። ወይዘሮ ስቴቨንስ የታወሩት የአርባ ሰባት ዓመት ወይዘሮ ሲሆኑ ነው። እውር ከሆኑ ወዲህ ዓለም በሙሉ ጨልሞባቸው ነበር። ግን ጥሎ አይጥልምና ወይዘሮ ስቴቨንስ እውር እንደሆኑ ስዕል መሳል ተማሩ እውር ስዕል ሳይ በመሆናቸውም «አስደናቂይቱ እውር» ለመባል በቁ። ወይዘሮ ስቴቨንስ ስለራሳቸው ሲያወሩ «በታወርኩ ሰሞን ማገኛዎቹ እውሮች ጊዜያቸውን እንደሚያሳልፉበት ዶሚኖና የመሳሰሉትን በዳበሳ

የሚታወቁትን ጨዋታዎች እየተጫወትሁ ጊዜዬን አሳልፍ ነበር። ግን ለመኖር ያንን ብቻ በቂ ሆኖ አላገኘሁትም አንድ ቀን ቁጭ ብዬ ስለ ልጅነቴ ሳስብ ስዕል መሞጫጨር እወድ ነበር ትዝ አለኝ። ግን ስለ ስዕል በሕይወቴ ውስጥ ምንም ትምህርት አልተማርኩም ነበር። ቢሆንም ልጀምረው ብዬ መሞጫጨር ጀመርኩ። ሥዕል መሳሉ እየገባኝ ሲሄድም ዓይኔ ያይ በነበረ ጊዜ የማውቃቸውን ሰዎች ፊት መሳል ጀመርኩ።

«በመጀመሪያ የሳልኩት የልጅ ልጄን መልክ ነበር። ከዚያ በኋላ የወዳጆቼንና የጎረቤቶቼን መልክ ሁሉ ትዝ የሚለኝን እስል ጀመር። ዛሬ ግን የማላውቃቸውንም ሰዎች መልክ ለመሳል ችያለሁ።» ብለዋል። እውነትም ወይዘሮ ስቴቨንስ የሚስሉት ስዕል ከፎቶ ግራፍ ሲታያይ ልዩነት የሚታይበት በመጠኑ ነው። ለምሳሌ ከሳሉዋቸው ስዕሎች አንደኛው ይሄ ሲሆን ከጎኑ ያለው የእውነተኛው መልክ ፎቶ ግራፍ ነው።

እንዴት የማያውቁትን ሰው ፊት ለመሳል ይችላሉ? ሲባሉ «የምስለው ሰው መልክ ምን እንደሚመስል ገምቼ የማውቀው በድምፁ ነው። እርግጥ ብዙውን ነገር በድምፁ ለይቼ አላውቅም 72 ዓመት ዕድሜ ያለው ባሌ አቶ ዎሊ አንዳንድ ነገሮችን ይረዳኛል። የሚረዳኝም ስዕሉን በመሳል ሳይሆን የሰውየውን ጠጉር ቀለም፤ የሸፋሉን ቀለም፤ ከንፈሩ ወፍራም ወይም ቀጭን መሆኑን ይነግረኝና እነኢ እሠራዋለሁ።

«በስዕል ሥራዬ መሻሻል ወይም ያለመሻሻሌኒን አላውቅም ምክንያቱም አላየውምና ነው። የምስለው በለስላሳ ወረቀት ላይ ነው፤ በአንደኛው እጄ የፈለግሁትን ዓይነት ባለ ቀለም ርሳስ እይዝና በአንደኛው እጄ ወረቀቱን እየዳበስሁ እስላለሁ። ባለ ቀለም እርሳሶችን መለዋወጡም አይቸግረኝም። ከሁሉም ከሁሉም የጌታ የየሱስ ክርስቶስን ስዕል መሳል ደስ ይለኛል ብዙ ሰዎችም ስዕሌን ሲያደንቁ እየሰማሁ ዓይኔን አሳውሮ ይህን ጥበብ ያሳወቀኝን አምላክ አመሰግነዋለሁ» ብለዋል።

***

# የተጣበቁት ልጆች

በአሜሪካ አገር ኤልሳልቫዶር ውስጥ እነኚህ ልጆች ተወለዱ። ልጆቹ እንደምታዩዋቸው ከጎን የተጣበቁ ናቸው። ከወገብ በላይ ሁለት ሰዎች ሲሆኑ ከወገብ በታች ግን የአንድ ሰው አካል፤ አላቸው። እጆቻው አራት ሲሆኑ እግሮቻቸው ግን ሁለት ብቻ ናቸው። እነዚህ ልጆች ይህን ፎቶ ግራፍ ሲነሱ ዕድሜያቸው አሥራ አንድ ዓመት ነበር።

በግራ እብኩል የተፈጠረችው ስሟ ጁራቺ ሲሆን በቀኝ በኩል የተፈጠረችው ደግሞ ናዲር ተብላለች። እነዚህ ልጆች ይህን ዕድሜ እስቲያገኙ ድረስ የሚኖሩት

በሐኪም ቤት ውስጥ በሐኪሞች እየተመረመሩ ነበር። እነኚህን በአንድ አካል ውስጥ ሁለት ነፍስ ያላቸውን ፍጥረቶች ለማዳን ወይም ለማስተካከል ሐኪሞች እጅግ በጣም በመጣር ላይ ነበር። ፕሮፌሰር ጆዜ በተባሉት ፷፫ ዓመት ዕድሜ ባላቸው ታላቅ ሐኪም ሊቀመንበርነት የሚመራ የሐኪም ጓድ በሰጠው ማብራሪያ «ከእንግዲህ ወዲያ እነዚህን ልጆች ኑሮን እንዴት አድርገው መኖር እንደሚችሉ ከማስተማር በቀር በሌላው በኩል ያለው ጉዳይ አክትሟል። እንዲህ ዓይነቱ አፈጣጠር ሊደርስ የሚችለው በሁለት ሺ ሚሊዮን ዓመታት ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ነው» ብለዋል። እነዚህ ልጆች የሚኖሩት ክሊሜሪዮ ዲ አልቤራ በሚባለው ክሊኒክ ውስጥ ነው። በዚያውም ክሊኒክ ውስጥ ለእነዚህ ልጆች ጥናት የተመደቡት ሐኪሞች በሙሉ ከሌላ ሥራ ታግደው ሁልጊዜ ልጆቹን ይመረምራሉ። በየቀኑ የሚያጋጥማቸውንም የጥናት ውጬት በመዝገብ ያኖራሉ። እነዚህ ሐኪሞች እንደተናገሩት «እንደዚህ ዓይነቱ ፍጥረት በዓለም ለመጀመሪያ ጊዜ ሳይሆን አይቀርም ብለዋል። በመኝታ በኩል ችግር አለ ሁለቱም ልጆች በአንድነት በአንድ ጊዜ ለመተኛት አይችሉም። አንዲቱ ልጅ በምትተኛበት ጊዜ አንደኛይቱ ከላይ ሆና ያለማንቀላፋት አለባት አሁን በዚህ ፎቶ ግራፍ ላይ የምትመለከቱት አንዲቱ ልጅ ተኝታለች አንደኛዋ ግን እንደምታዩዋት ከላይ ድራብ ቢጤ ሆና ሳታንቀላፋ አጠገብዋ ባለው አሻንጉሊት ትጫወታለች። እንደገና ደግሞ ያቺ ተኝታ የነበረችው ትነቃና ከላይ በኩል ስትገለበጥ ያቺኛዋ እንድትተኛ ይደረጋል። አንዲቱ ልጅ የምታንቀላፋው ለሦስት ሰዓት ብቻ ነው። ከሦስት ሰዓት በኋላ ያቺ ተኝታ የነበረችው ትነቃና ያቺኛዋ ደግሞ ለሦስት ሰዓት እንድትተኛ ይደረጋል። ይህም በሐኪሞቹ ትእዛዝ የተደረገ ነው። ልጆቹም ይህን የፈረቃ መኝታ ለምደውት ምንም ዓይነት ችግር ወይም ሥቃይ አይሰማቸው።

ለልጆቹ ብዙ ዓይነት ጥበቃና መንከባከብ ይደረግላቸዋል ብዙ ዓይነት መጫወቻና አሻንጉሊቶች ሁሉ ቢኖራቸውም ልጆቹ ግን የሚወዱት ጨዋታ ዳንስ ነው። ሐኪሞቹ የጥናት ጊዜያቸውን ወይም በልጆቹ ላይ የሚያደርጉትን የጥናት ጊዜ ፈጽመው ልጆቹን ሲለቋቸው ወዲያውኑ ለሁለት አካል ባላቸው ሁለት እግር ሮጠው ሄደው ራዲዮ ይከፍታሉ። በራዲዮ በሚሰሙትም ሙዚቃ ለብዙ ጊዜ ይደንሳሉ።

ኑሮአቸው ሁሉ የደስታ ነው። ሁልጊዜ መሳቅና መጫወት ይወዳሉ። ተቃቅፈው መዋልና መሔድ ይወዳሉ። ብዙ ጊዜ ከሚተኙ ይልቅ ብዙ ጊዜ ቢደንሱ ደስ ይላቸዋል። እነዚህ እህትማማቾች የሚተያዩት እንደ እህትማማቾች ብቻ ሳይሆን እንደሚዋደዱ ጓደኞችም ጭምር ነው። ሐኪሞቹም ቢሆኑ እነዚህ ልጆች አምስት ዓመት ዕድሜ ሲኖራቸው ጀምረው ልጆቹን እንዴት እንደሚጫወቱ እንዴት እንደሚበሉና እንዴትስ እንደሚተኙ ሁሉ አስተምረዋቸው ስለ ነበር አሁን ካደጉ በኋላ በልጆቹ ላይ የሚታይ ምንም ዓይነት ችግር የለም።

እነዚህ እንደ እንጨት ባላ የተፈጠሩ ፍጥረቶች ሐኪሞችን አስቸግረው የነበሩት የአካሉ ጌታ ከማንኛዋ እንደሆነች ለማወቅ ነበር። ከብዙ ጥናት በኋላ በተገኘው ውጤት የአካሉ ጌታ ጁራቺ ናት። ጁራቺ የአካሉ ጌታ በመሆንዋ ከሌላው ፍጡር የተለየ ጠባይ አላት። ስትጽፍ፤ ስትናገር፤ ስትበላም ሆነ ስትሠራ ከተጣባቂ እህቷ ብቻ ሳይሆን በሷ ዕድሜ ካሉ ደህና የሰው ፍጥረቶች ሁሉ የበለጠች ናት። ቅጥያዋ ግን እምብዛም ነች ፈዛዛ ቢጤ ነች። ለመነጋገር እንኳን አትችልም። አብዛኛውን ጊዜ እህቷን አንድ አንድ ነገር ለማዘዝ ወይም ለመናገር ስትፈልግ በጣቷ ምልክት በመስጠት ነው። ለመናገር ስትጀምርም ኧኧኧ ማለት ስለምታበዛ ጁራቺ የንግግሩን አቅድ ትመራታለች። ሐኪሞቹ የዚችኛዋን የናዲርን ጉዳይ ሲናገሩ «የአንጎልዋ እድገት ከዚያችኛዋ የአንጎል እድገት አንድ ዓመት ወደ ኋላ የዘገየ ነው። የጁራቺ ግን ከሌላው ጤነኛ ሰው ሁሉ በበለጠ ፍጥነት ያድጋል» ብለዋል።

የነዚህ ልጆች ወላጆች አባትዮው ሄርናንዶ ሲባል እንናትዮዋ ደግሞ ወይዘሮ አምፓሮት ትባላለች። እነዚህ ወላጆች ሀብታሞች በመሆናቸው የልጆቹ እንክብካቤ በሚገባ የተያዘ ነው። እናቲቱ ስትናገር «እኛ በክርስትና ሃይማኖት ከሚያምኑ ቤተሰቦች የተወለድን ነን፤ እኛም ብንሆን በክርስቶስ የምናምን ክርስቲያኖች ነን። እግዚአብሔር ግን ለምን እንዲህ ያለ ጉድ እንዳመጣብኝ አላውቅም። ልጆቹን የወለድኳቸው ጊዜ አላየኋቸውም። ከወለድኳቸው በኋላም ሦስት ወር ሙሉ ፈጽሜ አላየኋቸውም ነበር። በኋላ አንድ ቀን የሚያበረታ መርፌ ወጉኝና ልጆቼን አሳዩኝ። መርፌ መወጋቴ ሊረዳኝ አልቻለም። ልጆቹን ልጆችሽ ናቸው ብለው ሲነግሩኝ አዞሮኝ ሕሊናዬን ስቼ ወደቅሁ። ለስምንት ቀንም ምንም አላውቅም ነበር። የዚያን ጊዜ ስነቃም አስበው የነበረው አሳብ መጥፎ ነበርና አሁን አሳቤን ለውጫለሁ።

«የዚያን ጊዜ አስብ የነበረው ለምን ልጆቹ እንደተወለዱ ጭንጋፍ ሆነው አልሞቱም ነበር እያልኩ አስብ ነበር። ለምን ኖሩ እያልኩም እበሽቅ ነበር። አሁን ግን ያን አሳቤን ትቻለሁ። እግዚአብሔር የሰጠኝን መቀበል አለብኝ ብላለች።

የእነዚያ ልጆች እናት ወይዘሮ አምፖሮ አዘውትራ ልጆቿ ወዳሉበት ክሊኒክ ትሄዳለች። ከዚያም ሲቻወቱ ይውላሉ ስለዚህም ስትናገር «አዎን ብዙ ጊዜ አብሬአቸው እጫወታለሁ፤ እንዲስቁም ለማድረግ እሞክራለሁ። ከእነሱ ፊት ሆኜም አላለቅስም። ምክንያቱም እምባዬ ሁሉ አልቋል» ብላለች።

በአሜሪካ አገር በኢንዲያና ውስጥ በፔትስበርግ ከተማ ታኅሣሥ 12 ቀን 1953 ዓ.ም ሁለት ራሶች ያሉት ልጅ ተወልዷል። አንደኛው ራስ ሙሉ ጤናማ ሲሆን ሁለተኛው ራስ ግን ከመብላትና ከማየት በስተቀር ደካማና ፈዛዛ ነበር። እነኚህ ሁለት ራሶች በአንድ ትከሻ ላይ የተተከሉ ናቸው። ከትከሻ በታች ያላቸው አካል የአንድ ሰው

ነው። ሁለቱ ራሶች፤ የሚበሉት፤ የሚያዩት፤ የሚተኙትና እይሚስቁት ግን ለየብቻ ነው።

አሁንም በኢንዲያና አውራጃ ቲፕተን በተባለ አምባ ሰኔ 24 ቀን 1889 ዓ.ም አንድ ልጅ ተወልዶ ነበር። ልጁ አንድ ራስ አለው። በዚያ አንድ ራስ ላይ ያለው ፊቱ ግን ሁለት ነው። ፊቶቹ ያሉት ጎን ለጎን አይደለም። አንዱ ከበፊት ሲሆን አንዱ ደግሞ ከኋላው ነው። ይህ ልጅ፤ ትርፍ የተፈጠረለት ፊቱ ብቻ አልነበረም። አራት የተጣበቁ እግሮችም ነበሩት። የተጣበቁት እግሮቹም አቀማመት እንደፊቱ ሁሉ ከኋላ እና ከወደፊት ሆነው ነው። እጆቹ ግን እንደማንኛውም ሰው ሁለት ብቻ ናቸው። ይህ ፍጡር አንድ ዓመት ሙሉ ለሕዝብ እንዲታይ ተደርጎ በየካቲት ወር 1891 ዓ.ም በኒውዮርክ ከተማ በሳንጆስ ሆቴል ውስጥ ሞተ።

በ1829 ዓ.ም በግንቦት ወር በኢጣልያ አገር በሳርዲና ውስጥ ሳሳሪ በተባለ ቀበሌ አንዲት የሰላሳ ሁለት ዓመት ሴት ከወገቡ በላይ ሁለት አካል ያለው ልጅ ወልዳ ነበር። ይህ ሁለት አካል ያለው ልጅ ከሆዱ ጀምሮ ወደ ታች የአንድ ሰው አካል ያለው ሲሆን ከሆዱ በላይ ግን የሁለት ሰዎች አካል ነበረው። እነኚህ ከሆዱ በላይ ሁለት የሆኑት ሰዎች አድራጎታቸው ሁሉ የተለያየ ነበር። ለየብቻ የብላሉ፤ ለየብቻ ይናገራሉ፤ ለየብቻ ያለቅሳሉ፤ ለየብቻ ይስቃሉ። እነዚህ ሰዎች በወላጆቻቸው አማካይነት በየአገሩ እየተዘዋወሩ ለሕዝብ ሲታዩ ቆይተው በፓሪስ ከተማ በብርድ በሽታ ሞቱ። አፅሙ አሁን በፓሪስ ከተማ ሙዚየም ውስጥ ተቀምጧል።

በ1854 ዓ.ም በወታው ቦስተን ሜዲካል ጁርናል በተባለው ጋዜጣ ላይ ዱሩርይ የተባሉ የእንግሊዝ ባለሥልጣን እንደጻፉት አራት ዓይኖች ስላሉት ሰውዬ ዝርዝረዋል። ሁለት ዓይኖቹ እንደማንኛውም ሰው ዓይኖች ሲሆኑ ሁለቱ ትርፍ ዓይኖቹ ከደንበኛ ዓይኖቹ በላይ በኩል ተተክለዋል። አራቱም ዓይኖቹ ተመሳሳይ መልክና ስፋት አላቸው። ዱሩርይ እንደጻፉት «ሰውዬው አራቱንም ዓይኖች እያንዳንዳቸውን ተራ በተራ መጨፈን፤ ወደ ግራ ወይም ወደ ቀኝ ማዘዋወር ይችላል» ብለዋል።

***

በአሜሪካ አገር በኒውዮርክ ከተማ የመኪና ማቆሚያ ቦታ ለማግኘት በጣም ችግር ነው።

በዚህ ፎቶ ግራፍ ላይ እንደምታዩት በመሬት ላይ መቆሚያ ያጣው ማርቸዲስ መኪና ከኋላው በኩል ፎቁ ላይ ተንጠልጥሎ ታዩታላችሁ መኪናው መጥጦ ከመሬት ሲቆም ወዲያውኑ በከባድ ዕቃ ማንሻ ተንጠልጥሎ ከፎቁ ውስጥ እንዲገባ ይደረጋል። አሁን የምታዩት ጨርሶ ሊገባ ጥቂት የቀረውን ማርቸዲስ መኪና ነው።

***

# ሌላዎቹ ተጣባቂዎች

በ1960 ዓ.ም በኢጣልያ አገር በሚላኖ አካባቢ አቶ ፎልያ ከሕግ ሚስታቸው ልጅ አስወለዱ። ልጆቹ መንታ ሲሆኑ ከዳሌያቸው ላይ ተጣብቀው አንድ አካል ያላቸው ነበሩ። እነዚህ ተጣብቀው የተወለዱት ሁለት ሴቶች ልጆች አንድ ሰሞን በኢጣልያ ጋዜጦችና መጽሔቶች ሰፋፊ አምድ እየተሰጣቸው ተአምሩ ሲወራ ከረመ።

በእርግጥም ተአምር ነበር። ሊቃውንት እንደሚሉት እንደዚህ ዓይነቱ ነገር ሊያጋጥም የሚችለው ከሦስት መቶ ሺ መወለድ ውስጥ አንድ ጊዜ ነው። በእንዲህ ያለ ሁኔታ ከሚወለዱትም መሐል በሕይወት ለመኖር ዕድል ያላቸው ከስድስት ሚሊዮን ውስጥ አንድ ብቻ ነው።

አሁን ወደ ልጆቹ ታሪክ እንመለስ። ዶሜኒካ የተባለው ጋዜጣ እንደገለጸው ልጆቹ እንደተጣበቁ የተወለዱት በሐኪም ቤት ውስጥ ነው። ልጆቹ እንደ ተወለዱ እናቲቱ ሳታያቸው ተደብቀው ተወሰዱ። አሥራ አስምት ቀን እስቲሆናቸው ድረስ ሐኪሞቹ ልጆቹ ከእናታቸው ጋር እንዲገናኙ አዘዙ። እናቲቱ ሁለቱን ልጆችዋን በክንዶችዋ ታቅፋ ደስ አላት። መንታ በመውለድዋ ታቅፋ ለመተኛት አሰበች። አንዱን ስታነሳ አንዷ ትጎተትባት ጀመር። ነገሩ ግራ ቢገባት አስታማሚ ጠርታ «ልጆቹ አልለያይ አሉኝ፤ ምን ነገር ይዟቸዋል?» ብላ ጠየቀች። አስታማሚቷ አዝና እንዳቀረቀረች በለሰለሰ አንደበት «ልጆቹኮ የተወለዱት ተጣብቀው ነው» አለቻ። እናቲቱ ደነገጠች። አመሰግናው የነበረውን እግዚአብሔርንም ባመሰገነው አንደበትዋ፤ መልሳ አማረረችው። በኋላም ለጋዜጠኞች በሰጠችው ቃል «በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ምን ባደርግህ ነው ይህን አሰቃቂ ነገር የምታሳየኝ? ብትዬ እንዲሞቱልኝ መመኘቴን አስታውሳለሁ» ብላለች።

ከተወለዱበት ጊዜ ጀምሮ ስድስት ዓመት እስኪሆናቸው ድረስ ልጆቹ ሆስፒታል ውስጥ ቆዩ። ሐኪሞቹ ልጆቹን ለማለያየት አይቻልም ብለው የሚጠበቀው የልጆቹ የመሞቻ ጊዜ ነበር። የልጆቹ ያለመሞት ሐኪሞቹን አሳሰበ። ለመለያየት እንዲሞክሩም ምርምር ጀመሩ። ከምርምሩ በኋላ ፕሮፌሰር ሶምና ቡድን ግንቦት 10 ቀን 1956 ዓ.ም ቀዶ ጥገና አድርገው ልጆቹን ለያዩዋቸው። እናቲቱ የዚያን ጊዜ «አሁን እንደገና የወለድኳቸው መሰለኝ። እናታቸው መሆኔም ተሰማኝ» ብላለች።

ልጆቹ በሆስፒታል ውስጥ ሰባት ዓመት ከቆዩ በኋላ ወጡ አንደኛይቱ ሳንቲና ስትባል አንዷ ደግሞ ጁሴፒና ተባለች። ቀዶ ጥገናውን ያከናወኑት ፕሮፌሰር ስላርዮ

ሲናገሩ «ኦፕራሲዮኑ በጥሩ ሁኔታ ተከናውኗል። ሳንቲናና ጁሴፒና አሁን እንደማንኛዎቹም መንትዮች መንታ ናቸው። አሁን ለየብቻቸው በአንዳንድ ወንበር ላይ መቀመጥ ችለዋል። እነዚህ ልጆች እንደ ሌሎች ልጆች ሁሉ በጨዋታና በፈንጠዝያ እንዲሁም በመሮጥ የሌሎችን ልጆች ሕይወት በሚጀምሩበት ጊዜ ያኔ የደስታ ቀን ይጀመራል» ብለው ነበር።

ጁዜፒና ከሳንቲና ትንሽ ረዘም ትላለች። በፈገግታዋና ጨዋታ በመውደድዋም ከእህትዋ ትለያለች። ሳንቲና ግን ከእህትዋ ለየት ያለችና በጠባይዋ ተቃራኒ ነች፡ ሁለቱ ልጆች አሁን እንደማንኛዎቹም ሁሉ ይሮጣሉ፤ ይጫወታሉ።

እናትዮዋ ስታወራ «እነሱን አርግዤ ሳለሁ አንድ ቀን በአንድ አትክልት ቦታ ስዘዋወር አንድ ዓይን ብቻ ያላት ጥንቸል አየሁ። ለብዙ ለሊቶችም በሕልሜ ያቺን ጥንቸል አይ ነበር። ልጆቼ ከተወለዱም በኋላ ቢሆን እንደዚያው እንደተጣበቁበት ሁኔታ እወዳቸው ነበር። ማንኛይቱም እናት ልጆችዋን እንደምትወደው ሁሉ እኔም ልጆቼን እወዳቸው ነበር። አሁን ክብሩ ይስፋ ለፈጣሪ ያ የችግር ጊዜ አልፏል» ብላለች።

***

ሌሎችም ተጣብቀው የተወለዱ ነበር። እነኚህኛዎቹ የተጣበቁት በራሳቸው በኩል ነበር። ራሳቸው ተጋጥሞ በመወለዳቸው ምክንያት ልጆቹ በሕይወት እንደማይኖሩ ተወስኖ ነበር። ግን በሐኪሞች ጥበብ ተላቀው ለማደግ በቅተዋል። በዚህ ፎቶ ግራፍ የምታዩዋቸው ከተላቀቁ በኋላ እናቲቱ ታቅፋቸው ነው። ዝርዝር ታሪኩን ላውጋችሁ እነዚህ ልጆች የተወለዱት በአሜሪካ አገር በቴኒሲ ውስት ማውንት ሲቲ በተባለው ከተማ በ1957 ዓ.ም ነው። ልጆቹ እንደተወለዱ ሐኪሞቹ «......ለሁለት አንድ አንጎል ብቻ ያላቸው ስለሆኑ ሊለያዩ አይችሉም......» ብለው ነበር።

እናቲቱ ወይዘሮ በንተን ይባላሉ። የልጆቹ አባት ሚስታቸው የስድስት ወር ነፍሰጡር ሆነው ሞተዋል። እናቲቱ ሲናገሩ «.....የተጣበቁትን ከመውለዴ ይልቅ በጣም አድርጎ ያበሳጨኝ የሆስፒታሉ ነርሶች ጉዳይ ነበር። ብዙዎቹ ነርሶች እየፈሩ ይሸሹዋቸዋል። ታቅፈው ለመያዝም ይቸገራል። ችግር እኔን እንዳስተማረኝ ነርሶቹ ተቸግረው ለመታቀፍ አይሞክሩም። ይህም በመሆኑ ምክንያት ከወለድኩበት ሐኪም ቤት ቶሎ ብዬ ለመውጣት ፈለግሁና ወጣሁ።.....» ብለዋል።

እናቲቱ ወይዘሮ ቦንተን በወለዱ በአሥረኛው ቀን ከሐኪም ቤቱ ወጥተው በሕይወት ይኖራሉ ብለው ተስፋ ያላደረጉባቸውን ሕፃናቶቻቸውን ይዘው ዘመዶቻቸው ወዳሉበት በዚያው በቴኒሲ ውስጥ በትለር ወደ ተባለ ቦታ ሔዱ። የተጣበቁት የሁለቱም ሕፃናት ክብደት ሦስት ኪሎ ነበር። ወይዘሮ በንተን ሁለቱንም

ሕፃናት በአንድ ጊዜ ለማጥባት አይችሉም ነበር። ጡጦ ለማጥባትም ቢሆን በሁለት እጆቻቸው ሁለት ጡጦ ይዘው ይመግቡ ነበር። ብዙውን ጊዜ ግን የብርቱካን ጭማቂና ቪታሚኖች ይመግቡዋቸው ነበር።

አንድ የእናቲቱ የቅርብ ዘመድ ሲናገሩ «......ከሁሉ የሚገርመኝ ነገር እናቲቱ ሕፃናቶቹን አትደብቃቸውም ነበር። ያለችበት ቤት በሕዝብ ብዛት ቢሞላም ሕፃናቶቹን ለማየት የመጡትን ሰዎች ያለ ምንም እፍረትና ጭንቀት በኩራት ሕፃናቶቹን በማሳየት ታስተናግዳለች።......» ብለዋል።

አንደኛዋ ሕፃን አንድ በሽታ ሲይዛት ወዲያውኑ መንትዮዋ ትያዛለች። ብዙ ጊዜም ሕፃናቱ ለመላቀቅ እያሉ ሲወራጩ አንዷ ሌላዋን ትመታታለች። እናትዮዋ ወይዘሮ በንተን አንድ ውሳኔ ወሰኑ። «እነዚህ ሕፃናት በዚህ ሁኔታ መኖር ስለማይችሉ ቢድኑም ቢሞቱም በኦፕሬሽን ጭንቅላታቸው ተላቆ ቁርጡ መታወቅ አለበ» ብለው ወሰኑ። አንደኛዋን ተጣባቂ ቴሬሳ፤ አጣባቂዋን ደግሞ ጂኒ ብለው ስም አወጡላቸው። ይህንኑ የሕፃናቱን መለያየት ሲያሰላስሉ አንድ ቀን አንደኛዋ አለቀሰች። ስለዚህ ሁኔታ እናትዮዋ ሲናገሩ «......ለቅሶው እንደተለመደው እርስ በርሳቸው ተቧጥጠው ይሆናል ብዬ ወደ አስተኛሁበት ክፍል ገባሁ። አንደኛዋ ስትነጫነጭ አንደኛዋ በሰላም ስታንቀላፋ አየሁ። ይሄን ጊዜ አንድ ነገር ተሰማኝ። አንደኛዋ ስታለቅስ ሌላዋን እንቅልፍ መውሰዱ የተለያየ አንጎል ቢኖራቸው ነው ብዬ አሰብሁ። ነገሩ እንዳሰብኩት በመሆኑ ጮሁህ። ወዲያው አባቴ ቄስ ማክክላውድ የጮኩት ሕፃናቱ የሞቱ መስሎት ሲሮጥ መጥቶ ከክፍሉ ውስጥ ገባ። ለአባቴም «ሕፃናቶቹ የተለያየ አንጎል አላቸው» አልኩት። አባቴም «እግዚአብሔርን ለማስመስገን የሚኖሩ ናቸው» ብሎ ነገረኝ.....» ብለዋል።

በሜሪላንድ ውስጥ ባለው ናሺናል ኢኒስቲቲውት ኦፍ ሔልዝ፤ ቤዝዳ በተባለው ሐኪም ቤት ውስጥ የቀዳዳ ሐኪም የሆኑት ባልድዊን ሕፃናቶቹን በኦፕሬሽን ለማላቀቅ ተስማሙ። ሁለት ጊዜ በተደረገው ኦፕሬሽን ሕፃናቶቹ ተላቀቁ። በዚያው ሐኪም ቤት ውስጥ ለአንድ ዓመት ከቆዩ በኋላ ሕፃናቶቹ በሰላም ወደ ቤታቸው ሄዱ።

ሕፃናቶቹ ተጣብቀው የነበሩበት የራሳቸው ቅል ሲላቀቅ ባዶ ሆኖ በመቅረቱ በፕላስቲክ ተደፍኗል። ጠጉራቸው አድጎ ከትከሻቸው ላይ በመውረዱ ያ ገጣባ ፕላስቲክ እንዳይታይ ሸፍኖላቸዋል። በየዓመቱም ከሐኪም ቤቱ እየሄዱ ይመረመራሉ። ምንም እንከን ሳይገኝባቸውም አድገዋል።

# ቅስና

በጃፓን አገር የቡዲስት ሃይማኖት ተከታዮች ቄሶቻቸውን የሚያቀስሱት በሕፃንነታቸው ወራት ነው። ቀሳውስት፤ ልጆቻቸውን ገና በሕፃንነታቸው ወራት ያቀስሳሉ። ቀሳውስቱ እንዴት እንደሚቀስሱ የያሷን ታሪክ እንይ።

ያሱኦ የቄስ ልጅ ነው። በልጅነቱ ቄስ መሆን ስላለበት ከጥንት ጀምሮ በመጣው በባህላቸው መሠረት የአምስት ዓመቱ ሕፃን ያሱኦ የእሳቱ ግለት አንድ መቶ ዲግሪ ፋራናይት ከሆነ ምድጃ አጠገብ ተቀምጦ ይፈተናል። ሌላውን ቀጥለው ይመልከቱ።

የበረዶ ውሃ የሚያረስ ፏፏቴ ምሥር ሆኖ በውሃው ራሱን በማስመታት ይቆያል።

ሕፃን ነውና በአባቱ ጀርባ ታዝሎ ሺ ዓመት ያህል ዕድሜ ካለው ካንሙሪዶከ በተባለው ተራራ ላይ ወዳለው ገዳም ይወጣል።

ቅስናው ተመስክሮ ከተረጋገጠ በኋላ በእንግድነት ከሚገባበት ቤት ሁሉ ይሰገድለታል።

ልጅ ነውና በጨዋታ ጊዜ እንደማንኛውም ልጅ ይጫወታል።

# የሟቹ አሻራ

ጥቅምት 28 ቀን 1975 ዓ.ም የወጣው ናሽናል እንኳይረር የተባለው ጋዜታ አንድ ታሪክ አውጥቶ ነበር። ታሪኩ የሚዘረዝረው የቶም ፊሽርን ነው። ቶም ፊሽር በአሜሪካ አገር በፔንስልቫኒያ ውስጥ ካርቦን በተባለው ከተማ ባለው ወህኒ ቤት ውስጥ ነበር። በዚያ ወህኒ ቤት አንድ ክፍል ግድግዳ ላይ አንድ የሰው እጅ አሻራ አለ። ያ አሻራ ወይም የሰው እጅ ማኅተም ከዚያ ብቶአ እንዲጠፉ ብዙ ጊዜ በቀለም ተቀብቷል። አልጠፋም። ብዙ ጊዜ ተፍቋል። ብዙ ጊዜ ተፍቋል፤ አልጠፋም ለጊዜው ይጠፋና ከጥቂት ቀናት በኋላ ይወጣል። ዛሬ ኑ በመቶ የሚቆጠሩ ጎብኚዎች ወደ ወህኒ ቤቱ እየሄዱ አሻራውን ያያሉ። ይህ አሻራ የቶም ፊሽር ነው። ታሪኩን የካርቦን ከተማ ዳኛ ሉዊስ ሊስላ ሲያወጉ «......ቶም ፊሽር የተባለ ወጣት ሰው ነበር። ይህ ወጣት ስወ መጋቢት 28 ቀን 1878 ዓ.ም በስቅላት እንዲቀጣ በተፈረደበት ፍርድ መሠረት ተሰቀለ። በማግሥቱ ሊሰቀል ማታውኑ ከታሠረበት ክፍል ውስጥ ሆኖ የቀኝ እጁን መዳፍ ከግድግዳው ላይ አድርጎ በአጠገቡ ለነበሩት እሥረኞች አንድ ኑዛዜ ተናዘዘ።


ኑዛዜውም ይህ በግድግዳ ላይ ያደረግሁት የእጄ ማኅተም ይህ ወህኒ ቤትና ክፍሉ እስካሉ ድረስ በዚህ ግድግዳ ላይ ይኖራል። የሚኖረውም ያለ ትክክለኛ ፍርድ በጫና መገደሌን ለመመስከር ነው።» ብሎ ተናገረ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይሄው በ97 ዓመት ሙሉ (አሁን አልፎታል) በቀለም ቢቀባም አልጠፋም ብሏል። እንዲያውም ባለፉት አራት ዓመታት ውስጥ ከባድ መርዝ በተቀላቀለበት ውፍረት ባለው አረንጓዴ ቀለም ተደጋግሞ ተቀባ። ግን ጥቂት ቀናት ይቆይና ቀለሙን አልፎ ይወጣል......» ብለዋል ይህን አልጠፋ ያለውን የእጅ አሻራ እንዲያጠኑ ከተደረጉ የሳይንስ ሊቃውንት መሐል ዶክተር ጀፍሪ ቲ ክሌን ሲናገሩ «......በግድግዳው ላይ ያለው የእጅ አሻራ ቀለሙ ጥቁር ነው በዚያ ከስሚንቶ (ኮንክሬት) ከተሠራው ግድግዳ ላይ የታተመ ነው። እንጂ ከግድግዳው ውስጥ ያለ አይደለም። ይህን ለማረጋገጥ የእጁን አሻራ ጥቂቱን ከግድግዳው ላይ ፍቄ አንስቼለት ነበር።.....ባደረግነው ብዙ ምርመራ ያ አሻራ ከግድግዳው ላይ ሊለጠፍ የቻለው ባልታወቀ ቅመም በተሠራ ዘይት ውስጥ በተነከረ እጅ ታትሞ ይሆናል ብለን ነበር። በልዩ ልዩ ታላላቅ የዘይት መመርመሪያዎች መዛሪያ መርምረን ምንም ዓይነት የዘይትነት ጠባይ አላገኘንበትም። ዘይት ከሌለበት ደግሞ ያ አሻራ እንዴት ሊኖር ቻለ? ለሚለው ጥያቄ እኛም ተቸግረን ነገሩን በማጤን ላይ ነን። ......» ብለዋል።

የወህኒ ቤቱ ወታደሮች አዛዥ ሪቻርድ ኮክራን ሲናገሩም «......እንዴት እንደሆነ ለማስረዳት አልችልም። የግድግዳውን አሻራ ለብዙ ጊዜ አጥንቼዋለሁ፤ ወታደሮችም ጥሩ አድርገው ፈግፍገው እንዲያጥቡት አድርጌአለሁ፤ ለብዙ ጊዜም በቀለም ቀብተነዋል፤ ነገር ግን ለጊዜው ይጠፋና ከጥቂት ቀናት በኋላ ተመልሶ ይወጣል። የማይጠፋበትንም ምክንያት የሚያስረዳን ሰው ሳናገኝ ይሄው መቶ ዓመት ሊሆነው ነው.....» ብለዋል።

በግድግዳው ላይ የጅ አሻራ ምልክቱ ለመቶ ዓመታት ያህል አልጠፋ ብሎ የቆየውና አሁንም ያለው ቶም ፊሽር በስቅላት የተገደለበት ምክንያት እንዴት ነበር? እንበል። ሞሊ ማጉሬስ እየተባለ የሚጠራ አንድ የከሰል ማዕድን ሠራተኞች የአድማ ቡድን ነበር። ይህ ቡድን ባስነሳው ረብሻ ሞርጋን ፖዌል የተባለ የከሰል ማዕድን ሠራተኞች አለቃ ተገደለ። ይህን ሰው የገደለው ቶም ፊሸር ነው ተብሎ ተያዘ። ቶም ፊሸር ፍርድ ቤት ቀርቦ በስቅላት እንዲቀጣ ተፈረደበት። እዚህ ላይ የአገሩ ዳኛ ሉዊስ ሊሴላ የኋላ ታሪኩን አምጥተው ሲያወጉ፤ «......ቶም ፊሸር እንደነገ ሊሰቀል ዛሬውኑ ወደ ማታ ገደማ የዚያ የበጥባጭ የስውር ገዳይ የሞሊ ማጉሬስ ቡድን የታወቁ አባሎች ከፈራጁ ዳኛ ዘንድ ቀርበው ቶም ፊሸር በግዳዩ ወንጀል ፈጽሞ እጁን ያላገባ መሆኑን አመልክተው ነበር። ዳኛውም ይህንኑ ጉዳይ ለበላዩ አስተዳዳሪ በአስቸኳይ ቢያመለክት የበላዩ አስተዳዳሪ ነገሩን ችላ ብለው እንደፈዘ ቆጠሩት ያች ለሊት ነው ቶም ፊሸር

በታሠረበት ክፍል ውስጥ ሆኖ ማዘን እጁን ከግድግዳው ላይ አስደግፎ በትካዜ ለእሥር ሚቹ ንጹህ ሰው መሆኑን አጫውቶ አሻራውን በግድግዳው ላይ ተወው......» ብለዋል።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY



# ስለደራሲው በጥቂቱ

ጳውሎስ ኞኞ ኅዳር 11 ቀን 1926 ዓ.ም ቁልቢ አካባቢ ተወልደው ድሬዳዋ ከተማ አደጉ። በጣሊያን ወረራ ምክንያት ትምህርታቸውን ከ4ኛ ክፍል በላይ ለመቀጠል አልቻሉም ነበር። ብልህ አዕምሮና የፈጠራ ችሎታ የነበራቸው ሰው ስለነበሩ፤ በልጅነታቸው የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ጣሊያንን ሲገድሉ ወይንም ሲማርኩ ሥዕል በመሣል ያሳዩ ነበር። ጳውሎስ ካላቸው የጽሑፍ ጥማት የተነሳ የ«ድምጽ ጋዜጣ» አዘጋጅ በመሆን የብዕር ድምጻቸውን ያሰሙ ነበር። ጋዜጦች ላይ ከጽሑፍ አቅራቢነት እስከ አዘጋጅነት ለበርካታ ዓመታት ሠርተዋል። በተለይ «አንድ ጥያቄ አለኝ» በሚለው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አምዳቸው ላይ ብዙ ታዋቂነትን አግኝተዋል። አቶ ጳውሎስ ኞኞ ከ1955 ዓ.ም ጀምሮ ለኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍ ዕድገት የነበራቸውን ተሰጥኦ በአግባቡ በሥራ ላይ ያዋሉ እውቅ ጋዜጠኛና ደራሲ ነበሩ። እኚህ ታዋቂ ሰው በተወለዱ በ58 ዓመታቸው አረፉ።

ከጋዜጠኝነታቸው ጎን ለጎን በድርሰትና በታሪክ ጸሐፊነታቸውም 19 መጻሕፍት የታተመላቸው ሲሆን ሁለቱ ካረፉ በኋላ የታተሙ ናቸ። ለሕዝብ የሚሆኑ ዕውቀት ተኮር መጻሕፍት በማቅረብ ይታወቁ የነበሩት አቶ ጳውሎስ ኞኞ ካረፉ ከ፳ ዓመታት በኋላ ዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ በሀገር ውስጥ የተጻጻፏቸውንና ወደውጭ አገር የላኳቸውን ደብዳቤዎች የሚያሳዩት ሁለት መጻሕፍት በአስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት አማካይነት ታትመዋል።

## የደራሲው ሥራዎች

1. ከሴቶቹ አምባ (**ልብወለድ**)
2. የአራዳው ታደሰ (**ልብወለድ**)
3. የጌታቸው ሚስቶች (**ልብወለድ**)
4. ድብልቅልቅ (**ልብወለድ**)
5. የኔዎቹ ገረዶች (**ልብወለድ**)
6. አጤ ቴዎድሮስ (**ታሪክ**)
7. አጤ ምኒልክ (**ታሪክ**)
8. የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት (**ታሪክ**)

9. አስደናቂ ታሪኮች (**ታሪክ**)
10. እውቀት (**ፍልስፍና**)

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY